


ማውጫ

ገፅ

ምዕራፍ አንድ:- ጋብቻና የእግዚአብሔር ዕቅድ.............................. 5
- ባህላዊና ዘመናዊ ጋብቻ.............................................. 7
- ክርስቲያናዊ ጋብቻና ሥርዓተ ተክሊል........................ 10
ጋብቻቸውን ያለሥርዓተ ተክሊል ለፈጸሙ........................ 17
ምዕራፍ ሁለት:- የትዳር አጋሬን እንዴት ልምረጥ?.................... 18
- ፍቅርን መመርመር ................................................ 18
- ለመንፈሳዊነትና ለሃይማኖት ማድላት........................ 20
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያን መከተል........................ 25
- ግፊቶችን መቋቋም ................................................ 28
- ለፈተና የሚያጋልጡ ሁኔታዎች
አለመኖራቸውን እርግጠኛ መሆን ................................ 30
ምዕራፍ ሦስት:- የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ...... 35
- በጋብቻ መሰረታዊ ሀሳቦች ማረጋገጥ ........................ 36
- በተመስጦ ጊዜ ማረጋገጥ ........................................ 38
- ነገሮችን በሒደት መመርመር .................................... 40
ምዕራፍ አራት:- የእጮኝነት ጊዜን በመልካም ሁኔታ ማሳለፍ .... 43
- ፍቅርን ንጹህ ማድረግ ............................................ 44
- ፍቅርን መንከባከብ .................................................. 48
- በተገቢው ጊዜ ጋብቻን መፈጸም ................................ 53
- ከጋብቻ በፊት ከሚፈጸም ሩካቤ ራስን መጠበቅ ....... 54
- ከጋብቻ በፊት ሩካቤ ላለመፈጸም ምን ላድርግ ......... 62
ምዕራፍ አምስት:- ሠርግና ጣጣው ................................................ 70
- በሙሽሮች፣ በቤተሰብና፣ በወዳጅ ዘመድ ላይ.........72-73
- በመንፈሳዊ ላይ ...................................................... 73
- ተጨማሪ ድካም ጥሎሽ፣መልስ፣ቅልቅል ................ 75
ምዕራፍ ስድስት:- ትዳር ከሠርግ በኋላ ........................................ 78
- ሩካቤ ................................................................ 78
➢ ፍላጐትን በግልጽ ማሳወቅ ........................................ 82
➢ ቅድመ ዝግጅትና ሙሉ በሙሉ ዝግጁ መሆን.........84-85
➢ የሥሜት መጠባበቅና ራስን አሳልፎ መስጠት ..... 85-87
- ቤተሰባዊ ሕይወት ................................................ 88
- ከሁሉ ጋር በሰላም መኖር ........................................ 97
ምዕራፍ ሰባት ኢ.ክርስቲያናዊ የሆነ ጾታዊ ክንውኖች ............ 102
- ግብረ ሶዶም .............................................................. 102
- ዝሙት .................................................................. 104
- ውርጃ .................................................................. 106
- ፍች .................................................................... 107
- Masturbation /ራስን በራስ በወሲብ ማርካት/ .. 111
- ማስተርቤሽን እንዴት ማቆም እችላለሁ ............. 118

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

ጋብቻን በተመለከተ ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ የሚጻፉ መጽሐፍት በብዛት አይታዩም:: በእርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለው ሁኔታ አበራታች በመሆኑ ለወደፊቱ ተሰጥኦው ያላቸው በዘርፍ ሰፊ ጥናትን አካሂደው ለህዝቡ የሚጠቅሙ ምክር አዘል መጻሕፍትን ያስነብቡናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: በተለይ በህዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ጾታዊ ጉዳዮችን የተመለከተ ግልጽ ውይይት ስለማይደረግና መምህራንም አስፈላጊውን ትኩረት ስለማይሰጡት የሚፈለገው ያህል አልዳበረም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ባህሪውን ከመግለጥ ጀምሮ ለሰው ልጅ ያለውን በጎ ሀሳብ በጋብቻ ውስጥ እንዳስቀመጠው መገንዘብ ይገባል በመሆኑም ለወደፊቱ ትኩረት የሚሰጠው አንገብጋቢ ርዕስ ጉዳይ ነው ብዬ አስባለሁ::

በዚህ መጽሐፍ ኦርቶዶክሳዊ ይዘቱን ሳይቀር ዘርዘር ባለ መልኩ፣ በግልጽ አቀራረብ ስለ ትዳር፣ሠርግ፣ሰለእጮኝነት ጊዜና ኢ-ክርስቲያናዊ ስለሆኑ ጾታዊ ክንውኖች ለመጠቆም ሞክሬያለሁ:: የሚያነበው ሁሉ ቁምነገር እንዲያገኝበት፣ ከጋብቻ በፊትና ከጋብቻ በኋላ ክርስቲያን ቤተሰብ የኑሮ ሂደቱን እንዴት መምራት እንዳለበት ግንዛቤን አግኝቶ ማንኛውም አንባቢ እኔን ይመለከታል ብሎ ትኩረት እንዲሰጠው ማዕከላዊ የሆኑ ሀሳቦች ተንፀባርቀውበታል::

በተለይም ለወጣት መንፈሳዊያን ጋብቻ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የኑሮ ውጣ ውረዱም አልጋ ባልጋ ነው ብሎ መጠበቅ የዋህነት በመሆኑ ለጋብቻ የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታ አስመልክቶ አታላይ ከሆኑ ስሜቶች እንዴት መጠበቅ እንደሚገባ አርቀው አስተዋይና የአላማ ሰዎች ይሆኑ ዘንድ ጠቃሚ ሀሳቦች ቀርበዋል የውስጥ ገፆችን በእርጋታ ቢያነቧቸው መልካም ምክርን ያገኛሉ የሚል የፀና እምነት አለኝ:: ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ጽሑፍ ማዘጋጀት ለሚያስቡ እንደመነሻ ሀሳብ ሊጠቀሙበት ቢፈልጉ የተወሰነ አስተዋጽኦ ሊያደርግላቸው ይችላል::

አዘጋጁ

ዲ/ን በሪሁን ወንድወሰን

www.ethiopianorthodox.org



# ምዕራፍ አንድ
# ጋብቻና የእግዚአብሔር ዕቅድ

ክርስቲያን ኑሮው ሁሉ በእግዚአብሔር በጎ ሀሳብ የተሞላ መሆን ስላለበት ቤተ ክርስቲያን ከምታስተምረው የሕይወት መንገድ የሚስማማውንና የሚችለውን አንዱን መርጦ ያለ ኃጢያትና ያለ በደል በንጽህና ይኖራል:: ጋብቻም ያስፈለገበት ምክንያት እግዚአብሔርን በንጽህና ለማምለክና የሰይጣንን ፈተና ለመቋቋም ነው:: በምንኩስና ወይም በትዳር ለመኖር አንድ ክርስቲያን ከመወሰኑ በፊት የእግዚአብሔር ዕቅድ በእያንዳንዳቸው ላይ ምን እንደሆነ አስቀድሞ መገንዘብ አለበት:: ምንኩስና ፍጹም እግዚአብሔርን መምሰል ነው:: ጋብቻም በተቀደሰ መኝታ ንጽህ በሆነ ምንጣፍ ኃጢያት በሌለበት ሩካቤ በፍቅር የሚኖሩበት ከምንኩስና እኩል ክብር የሚያስጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው በረከት ነው::

<u>ጋብቻ ሰው ሰራሽ ያልሆነ በእግዚአብሔር የተገነባ ትልቅ የሕይወት ተቋም ነው::</u> ሀገር፣ቤተክርስቲያን፣ቤተሰብና በዓለም ውስጥ ያለ እያንዳንዱ መንፈሳዊም ይሁን ማህበራዊ ተቋም የተመሰረተው በጋብቻ ላይ ነው:: ጋብቻ ባይኖር በሰው ልጅ ታሪክ ምንም አዲስ ነገር አይፈጠርም ነበር:: እግዚአብሔር ጋብቻን የትውልድ ምንጭ እንዲሆን አስቀድሞ ከወሰነ በኋላ ለአዳምና ለሔዋን ባርኮ ሰጣቸው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየገዙ እየነዱ ምድርና መላዋ በእነሱ ቁጥጥር ሥር ሆና እንድትኖር ታላቅ የንግሥናና የገዥነት ኃይልን ሰው ከመሆን የመፈራት ምልክትን ጋር ደርቦ በእንስሳትና በአራዊት ላይ ሳይቀር ባለሥልጣን አደረጋቸው:: የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን በዚህ ብቻ ተወስነው እንዲቀሩ አልነበረም በሰው ልብ ያልታሰበውን ዐይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን መንግሥቱንና ጽድቁን እንዲወርሱ እንጅ "ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሰራ የዘለዓለም ቤት የሚሆን በእግዚአብሔር የተሰራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን:: 2ኛ ቆሮ 5፣1

ጋብቻ የተመሰረተው ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነው:: ይህም ምን ያህል የተቀደሰ የአምላክ ስጦታ እንደሆነ የሚጠቁም ነው:: በዚህ ቅድስና ውስጥ ባልና ሚስት በአንድነት በሚኖሩበት ጊዜ አባትና እናታቸውን ሳይቀር ሊተው የሚችሉበት ፍጹም መተሳሰርን ጌታ በፍቅር መስርቶላዋል:: ሥጋዊና ሥነ-ልቦናዊ አንድነት ከመንፈሳዊ አንድነት ጋር ይዘው በሀሳብ፣ በስሜት፣ በዓላማ መዋሀድ እንዲችሉ አምላክ ጋብቻን የበረከት መሰረት አድርጐ ፍፁም ከኃጢያት በተለየ ቅድስና አንድነታቸውን አፀደቀው ::አንድነት ከሁሉ ይቀድማልና እግዚአብሔር በመጀመሪያ ይህንኑ አደረገ በቅድስና አንዲመስሉትም ስለወደደ በተቀደሰ ህብረት አንድ አደረጋቸው::

<u>ጋብቻ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጽም መተባበር ነው</u> ምድርን የሰው ልጆች ይሞሏት ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነውና በጋብቻ ውስጥ ልጆች ሲወለዱ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ ሕብረትን ይፈጥራል:: እግዚአብሔር ፈጣሪ እናት ና አባት ደግሞ ወላጅ ናቸው:: አምላክ ምሉዕ በኩለሔ ከመሆኑ የተነሳ ረዳት የማይሻ የሚያቅተው ነገር የሌለ ሲሆን ከፍቅሩ የተነሳ ሰውን ወዷልና በመፈጠር ሒደቱ የሰው ልጅን የድርሻውን እንዲያበረክት አድርጐታል:: ከወላጅነትም በተጨማሪ የእግዚአብሔር ፍጡሩን ተንከባካቢ ሞግዚት ወላጆች ናቸው:: በመልኩና በአርያው የፈጠረውን ሰው /ልጆቻቸውን/ እንዲጠብቁት በእምነት ቃል አደራ የሰጠው ለወላጆች ነው:: እግዚአብሔር የነፍስም የሥጋም ቤዛ ሲሆን ወላጆች ደግሞ በዓለም ውስጥ የልጆችን ፍላጐት የሚያሟሉ የእግዚአብሔር ወኪሎች ናቸው:: በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም መተባበር በጋብቻ ውስጥ አለ::

<u>ጋብቻ መንፈሳዊና ስብአዊ ፍቅር አጣምሮ የያዘ ነው</u>:: ትዳር የአካል ንክኪ የሰብአዊነት ፍቅር መግለጫ ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊነት ፍፃሜ ነው::መንፈሳዊነቱ ዘላቂነት ባለው ህብረት ውስጥ ዕረፍትን የሚሰጥ የተቀደሰና የተከበረ፣ ከነውር የጸዳ፣በደህንነት የሚኖር የሁሉ ነገር





ፍፃሜ በሆነው በፍቅር ላይ የተመሰረተ ነው :: በማህበራዊ ሕይወትም ውስጥ አስፈላጊውን ክብር ያጐናጽፋል በአግባቡ ከተጠቀሙበት ከሁሉ የበለጠውን ፀጋ እግዚአብሔር፣ የአካል፣ የአዕምሮና የመንፈስ ርካታን ጋብቻ ይሰጣል:: ሰው ብቻውን ቢሆን ይወድቃል በባህሪው ደካማ ነው:: ብቻውን ከጫፍ ማድረስ የማይችለውን ማህበራዊም ይሁን መንፈሳዊ ግዴታን በመተጋገዝ ማሸነፍ ይችል ዘንድ ሰውን ከውድቀት ለመታደግ እግዚአብሔር ራሱ በስሙ ለተጠሩት በአራያውና በአምሳሉ ለተፈጠሩ የለገሰው ንጽህ ገጸ በረከት ነው "ፍቅር የህግ ሁሉ ፍጻሜ ነው" ሮሜ 10፣13 ጋብቻም መንፈሳዊውንም ሰብአዊውንም ፈተና በፍቀረ ድል ያደርጋል::

<u>ባህላዊና ዘመናዊ ጋብቻ</u>

የእግዚአብሔር ሥጦታ ለሰው ሁሉ አንድ አይነት ነው:: አድሎ የለበትም:: ይሁን እንጂ በረከቱን ተቀብሎ በስጦታዎቹ እየተደሰቱና እየተጽናኑ መኖርን ገንዘብ ማድረግ ያልቻሉ የተለያዩ ወገኖች አልፎ አልፎ በተለያየ ዘመናትና ወቅቶች ብቅ ብቅ ሲሉ እንመለከታለን:: በጋብቻ ሥርዓትም ላይ ቢሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮ ውጭ በሆነ መንገድ ለሚፈልጉት ነገር ማስፈጸሚያ ሲሉ ብቻ የእግዚአብሔርን ፍላጐት ሲጋፉ መንገዱንም በመሳት እንደ ሀሳባቸውና እንደልባቸው መሻት ሲራመዱ ይስተዋላሉ::

ሀ. <u>ባህላዊ ጋብቻ</u>

ሴት ልጅ ለወንድ ልጅ አገልጋይ እንድትሆን ከእግዚአብሔር የተፈረደባት ይመስል ያለምንም ነፃነት በለፋችበትና በደከመችበት ቤት ውስጥ በአንድ ነገር ላይ እንኳን ሥልጣን ሳይኖራት እንደባሪያ የምትቆጠርበት ከጭፍን ኋላቀር አስተሳሰብ የሚመነጭ የጋብቻ ሥርዓት ነው:: ይህ ሁኔታ በተለይ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል በሰፊው ተንሰራፍቶ ቢገኝም እንኳን አልፎ አልፎ ግን ወግ አጥባቂ በሆኑ ባለሥልጣናትና ባለሀብቶች ዘንድ እንዲሁም ራሳቸውን የባህል አምባሳደር አድርገው ባስቀመጡ የህብረተሰብ ክፍሎች አካባቢ የዘወትር ልማድ ነው:: ጋብቻውንም የሚጠቁሙበት

1. ጥሩ እውቀት ችሎታና ሀብት ያለው ብረት መዝጊያ አማች ለማግኘት
2. ወላጆች የራሳቸውን የወደፊት ሕይወት በጥሩ መሰረት ላይ ለመመስረት
3. የተከበረ ስማቸውን በልጃቸው ስቃይም ቢሆንም እንኳን ጠብቆ ለማኖር
4. ልጃቸውን በሥርዓት ያሳደጉ ወላጆች መሆናቸውን በማሳወቅ የተለየ የከበሬታ ወንበር ለማግኘት
5. ከቢጤዎቻቸው ጋር የጠበቀ ዝምድና ለመፍጠር
6. ከጭፍን ብሔረተኝነት በሚመነጭ ዘረኝነት ላይ ተመስርተው ንጹህ ዘርና ወገን አለን ለማለት

አብዛኛው . ኢ- ሰባአዊ የሆነው ባህላዊው ጋብቻ ለወላጆች የሚያተርፍላቸው ነገር የሚፈልጉትን ክብር፣ ሀብትና ዝና ሳይሆን የልጃቸውን ሀዘን ነው:: ያለፍላጐቷ የተዳረች ልጅ በትዳሯ ደስተኛ ልትሆን አትችልም:: በዚያ ላይ የምትዳርበት ወቅት ዕድሜዋን ያላገናዘበ ሥለሚሆን ገና በህፃንነቷ በወሊድ ምክንያት የሞት አደ. ሊያጋጥማት ይችላል:: አጋጣሚውን ካገኘች ከቤቷ በመኮብለል በሰው ቤት ሰራተኝነትና በሴተኛ አዳሪነት ውስጥ ገብታ ወላጆቿን ለዘለዓለም እየረገመች አሰቃቂ ኑሮ እንድትገፋ ትገደዳለች:: በምትማርበትና በምታድግበት ጊዜ ያለ አቅሟ ሸክም ማሸከም ራስ ወዳድነት ነው::

ትዳሩን የሚኖሩት ሙሽሮች እንጂ ወላጆች አይደሉምና ወላጆች ድርሻቸውን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል:: ርብቃ ለይስሀቅ ሚስት እንድትሆን እያዉብር ቤተሰቦቿን በጠየቀ ጊዜ ፈቅደንልሀል ውሰድ ሳይሆን የተባለው በመጀመሪያ ፍላጐቷ ነው የተጠየቀው እርሷ ፍቃደኝነቷን ስትገልጽ ግን በአባቶቻቸው አምላክ ስም በብዙ በረከት ባርከው አሰናበቷት ዘፍ 24፣60 መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊተ በነበረው ዘመን እንኳን የሙሽሮች ፈቃድ ይጠየቅ እንደነበር የሚያስገነዝብ ምንባብ ነው:: በመሆኑም የቤተሰብ ድርሻ መዳር ፣መኳል፣ ማማከር እንጂ መወሰን አይደለም:: ምክንያቱም አባትና





እናት ትዳራቸውን አሙቀው እየተደሰቱ የልጃቸው ኑሮ ግን እሳትና ሥለት መሆን አይገባውም:: በባህላዊ ጋብቻ ዘርና ዘር ፣ሀብትና ሀብት ሥምና ሥም ይጋባል:: ሙሽሪትና ሙሽራው ግን ሳይጋቡ ይፋታሉ::

ለ. ዘመናዊ ጋብቻ

ያለንበት ክፍለ ዘመን ዘመናዊ ያደርጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ በተቻለ መጠን አውሮፓውያንን ለመምሰል በሚደረገው ሩጫ ውስጥ ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ መልካቸውን እየለወጡ ባህር ማዶ ባሀር ማዶ እየሸተተ ነው:: የሚያሳዝነው የሥራ ባህላችን አውሮፓዊ መሆን አለመቻል ነው:: በልብስና በኃጢአት አንድ መሆኑ ላይ ብዙም ልዩነት የለንም:: ዘመነኞቹ አውሮፓውያን ሞክረውት ስላላዋጣቸው ርግፍ አድርገው ትተው በሚሊዮን የሚቆጠር የወር ገቢ ያላቸው ሳይቀሩ የተወሰኑ ሰዎችን ጋብዘው ጋብቻቸውን ሲፈጽሙ አፍጥጠው እየተመለከቱ እነዚያ ከብዷቸው ያወለቁትን ካባ ተሸክመው ያለ አቅማቸው ዘመናዊ ለመሆን ሲባል ብቻ እየተንገዳገዱ ይራመዳሉ::

ለምን እንደተጋቡ እንኳን የማያውቁ ዘመናዊያን ተጋቢዎች ማግኘት ተራ ነገር ሆንዋል:: ለምን አገባሁት ቢባል ስላማረችኝ ከሚል የተሻለ መልስ መጠበቅ ከአንበሳ አፍ ሥጋ እንደመጠበቅ ያህል ሞኝነት ነው:: በእርግጥ መፍታት በራሱ የዘመናዊነት ምልክት ተደርጐ የሚቆጠርበት ወቅት ስለሆነ እንደቀልድ የተጀመረውን ትዳር ጨዋታ ፈረሰ ዳብ ተቆረሰ ብሎ መመነቃቀር ስለሚቻል ያንን ያህል አሳሳቢ ጉዳያቸው አይደለም:: ዘመናዊነት ማለት ከኋላ ቀር አስተሳሰብ መላቀቅ ነው የሚሉት ሳይቀሩ ነገሮችን በኃላ ቀር ፍልስፍና ሲያከናውኑና እንደ ጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር ሰው ሲያሰቡ እናገኛቸዋለን እነዚያ ለዘመናቸው ዘመነኛ እንደነበሩ እነዚህም ለዘመናቸው ዘመነኛ ይሆናሉ:: ምንም ልዩነት የላቸውም የዘመን ርቀት ካልሆነ በስተቀር ጋብቻን ለመመስረት የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. የተጋነነ የኢኮኖሚ አቅም ማደራጀት
2. ቢያንስ በአንድ ነገር ታዋቂ መሆን

3. መልክ መልካም ቆንጆና ውብ መሆን
4. ከጋብቻ በፊት ለሚፈጸም ወሲብ ዝግጁ መሆን
5. ሃይማኖትና ሥነ-ምግባር የሚጠይቁት ሰብአዊነት አለማጥበቅ የተዘረዘሩትና ሌሎች ምክንያቶች ዘመናዊ ጋብቻ የሚያንፀባርቅባቸው መርሆቹ ናቸው:: ለዚህም ነው ትዳሩ " የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ...... የሚሆነው ወላጅ የማይመርቀው እግዚአብሔር የሌለበት በሁከትና በጭፈራ የተሞላ ፍጹም ዓለማዊነት ያየለበት ዘመናዊ ኋላቀር ነው:: ሰዎች ህሊናቸውን ለቁሳቁስ የሚሸጡበት በራስ ላይ የሚፈጸም ነውር ከመሆኑ በላይ የትዳሩ ፍፃሜ ከወራት አይዘልም:: የሚያስፈልጋት ገንዘብ ስላለ ብቻ አብራው ትኖራለች ያንን የምታገኝበት ሌላ አማራጭ ካለ ግን በማንኛውም ቅጽበት ትለየዋለች:: እርሱም እንደዚያው በትዳር ውስጥ እያሉም ቢሆን ሁለቱም ወገኖች በፍቅር ሳይሆን በጥቅም ስለሆነ የተሳሰሩት ልባቸው የሚያፈቅረውን ለማግኘት መባዘኑን አይተውም::

<u>ክርስቲያናዊ ጋብቻና ሥርዓተ ተክሊል</u>

ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ " ጋብቻ የፍቅር ትምህርት ቤት ነው" በማለት ዕለት ዕለት ፍቅርን የሚማሩበት፣ ፍቅርን የሚተረጉሙበት፣ ፍቅርን የሚያስተምሩበትና በፍቅር የሚኖሩበት ሕይወት እንደሆነ ይገልፃል:: ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ የዓለማት አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ወገኖች ጋብቻቸውን በሕግና በሥርዓት ሲፈጽሙ ኑሮዋቸውን ለእግዚአብሔር ሕያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርገው ሲያቀርቡ እንደኖሩ ይታወቃል:: በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን የአዳምና የሔዋንን ጋብቻ ባርኮ የሰጠ እግዚአብሔር በቃና ዘገሊላ በነበረው የሠርግ ሥነሥርዓት ላይ ከእናቱና ከሐዋርያት ጋር በመገኘት ጋብቻውን ቀድሶ፣ ጉድሏቸውን ሞልቶ፣ ድንቅ ነገርን በመካከላቸው እንዳደረገላቸው እናነባለን:: የክርስቲያን ጋብቻ ለክርስቲያን አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ከሌላው ጊዜ ሁሉ በዚህ ወቅት አዕምሮውን አረጋግቶ ልቡን ሰብስቦ በፀጥታና





በዕርጋታ እግዚአብሔርን በማስተዋል ማምለክ የሚችልበትን ዕውቀት ስለሚያክል ነው::

1. <u>ክርስቲያናዊ ጋብቻ</u>

ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ግፊትና ተጽዕኖ በሁለቱ እጮኞች መልካም ፍቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በቤተክርስቲያን ሥርዓት መሰረት የሚፈጸም ሲሆን ቤተክርስቲያንም ልጆቿን ከምታገለግልበትና ከምትባርክበት የእናትነት ሥጦታዎቿ መካከል አንዱ ነው:: ተጋቢዎች ለጋብቻ ይጠቅመናል የሚሉትን ማንኛውንም በሁለቱ መካከል የሚያስፈል ነገር አከናውነው እንዲጠናቀቁ እንደ ክርስትና ሃይማኖትና ትውፊት ጋብቻቸውን ለመፈጸም ስምምነታቸውን ለወላጆቻቸው በመግለጥ ይሁንታን ያገኛሉ:: ከዚህ ቀጥሎ ይህንን መልካም ሀሳባቸውን ለመምህረ ንስሐቸው በማሳወቅ ራሳቸውን ለጋብቻው ዝግጁ ያደርጋሉ::

መምህረ ንስሐቸው ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ማለት እንደሆነ ፣ በትዳር ወቅት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ፣ የሚያጋጥሟቸወን ፈተናዎች እንዴት መቋቋም እንደሚችሉና ሌሎች ጠቃሚ አባታዊ ምክሮችን በማከል መልካም ምኞቱን ይገልጽላቸዋል:: ቀጥሎም መምህረንስሐቸው በሃይማኖት ያላቸውን እውቀት፣ጽናትና የሥነ ምግባር ባለቤትነት፣ እንዲሁም የዕድሜ ደረጃቸው ለጋብቻ የሚያበቃ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ እጮኞች ጋብቻቸውን ሊፈጽሙ ወደ አሰቡት ቤተክርስቲያን በመሔድ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ መሆናቸውን፣ ስለጋብቻና ሥርዓተ ተክሊል የተማሩ እንደሆኑ፣ ቤተሰቦቻቸውና እራሳቸው ሙሽሮች ለጋብቻው ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውን በማስረዳት ጋብቻው ቢፈጸም ለቤተክርስቲያን ክብር እንደሆነ ቃሉን ይሰጣል:: የቤተክርስቲያኑ ወይም የደብሩ አስተዳዳሪ ከመምህረ ንስሐ በተነገራቸው መሠረት አስፈላጊው ነገር ተሟልቶ ሥርአተ ጋብቻው እንዲፈጸም ይፈቅዳሉ::

ትኩረት የሚያስፈልገው ሌላው ጉዳይ ደግሞ ጋብቻን የሚከለክሉ የተለያዩ ዝምድናዎች እንዳይጣሱ መቆጣጠር ነው::

አህዛባዊ ወይም ዘመናዊ ጋብቻ ቢሆን ይህ ነገር እንኳን እንደ አስፈላጊ ቁም ነገር ሊነሳ ቀርቶ ከኋላ ቀርነት ያላነሰ ትርጉም ነው የሚሰጠው:: ቤተክርስቲያን ግን የጋብቻውን ዘላቂነት ግምት ውስጥ በማስገባት ከአበው የወረሰችውን ቀጥተኛ ትውፊት በመከተልና መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚያስተምረው በሥጋዊ ዝምድና በመንፈሳዊ ዝምድናና በጋብቻ ዝምድና ላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ገደብ ትጥላለች::ይህን ሕግ በመጣስ ጋብቻ እንዲፈጸም አታደርግም::

## ጋብቻን የሚከለክሉ ዝምድናዎች

### ሀ. ሥጋዊ ዝምድና

የቤተክርስቲያን የሕግ መጽሐፍ  ፍትሀ ነገሥት ፍትሀ መንፈሳዊን በሚደነግግበት ክፍሉ ሥጋዊ ዝምድና እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ እንዳልተፈቀደ ይጠቁማል:: በሁለቱም ወገን በእናታቸውና በአባታቸው የዘር ሀረግ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ዘመዶች እርስ በርሳቸው አይጋቡ ይላል:: ከሰባተኛው ዘመድ በኋላ ያሉት ወገኖች በዘር ሀረግ ውስጥ ምንም እንኳን ቢካተቱ ተፈቅዶላቸዋል:: አህዛብ ግን ከዚህ ፍጽም ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ወንድም እህቱን ሳይቀር የሚያገባበት የዝሙት ሥርዓት አላቸው:: ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል የተሸከመ ሊጸድቅ የሚተጋ በመሆኑ ፈጽሞ ከአሕዛብ የተለየ ነው:: የአማሌቃዊያንንም ነውር ወደቅድስቲቱ ከተማ ይዞት አይገባም:: ፍት፣ነገ 24:842-853 ዘሌ18፣7/20፣10 - 21

### ለ. መንፈሳዊ ዝምድና

የተለያዩ መንፈሳዊ ዝምድናዎች በክርስትና ውስጥ ይስተዋላሉ ለምሳሌ የጽዋ ማህበር መንፈሳዊ ዝምድና ፣ በአንድ ቦታ ወይም በሰንበት ት/ቤት በመማር የሚፈጠር መንፈሳዊ ዝምድና፣ በጥምቀተ ክርስትና የሚገኝ መንፈሳዊ ዝምድናና ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች መንፈሳዊ ዝምድናዎች አሉ:: ሁሉም ዝምድናዎች በተለያየ መልኩ መጠበቅ አለባቸው:: በጋብቻ እንዳይፈርስ ከሁሉ በላይ ጥንቃቄ የሚደረግበት መንፈሳዊ ዝምድና ግን በጥምቀተ ክርስትና የሚገኘው





መንፈሳዊ ዝምድና ነው:: ከዚህ አንፃር እንደፍትህ መንፈሳዊ ድንጋጌ የክርስትና ልጅ የክርስትና አባቱን ሚስት፣ልጅ የልጅ ልጅንና እህቱን አያገባም:: የክርስትና አባት ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ የክርስትና ልጅን እናት፣ እህቱን፣ የእህቱንና የወንድሙን ልጅ አያገባም::

በሌላ በኩል ደግሞ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ እጮኛሞች ወደ ጋብቻ መግባት በፍጹም የለባቸውም:: ያላመነች እጮኛ ብትኖረው አስተምሮ መክሮ እርሱን እንድትመስል ካደረገ በኋላ ሊያገባት ይችላል:: ከትዳር በሚገኘው ፀጋ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ልጅ ከሞት ወደ ሕይወት ስለመለሰም ክብሩ ከፀሐይ ሰባት እጅ ይበራለታል:: ፍት.ነገ 24:912

### ሐ. የጋብቻ ዝምድና

የጋብቻ ዝምድና የሚከለከልበት ዋናው ምክንያት ከመጀመሪያው ጋብቻ በኋላ አንድ ልጅ እንደተወለደ ዝምድናው ከጋብቻ ዝምድና ወደ ሥጋ ዝምድና መልኩን ቀይሮ የሥጋ ትስስር ስለሚፈጥር ነው:: በዚህ መሰረት ወንድ ልጅ የአባቱንና የአያቱን ሚስት እህት፣ እናት እንዲሁም የልጁንና የልጅ ልጁን ሚስት ልጁን፣ እህቷን፣ እናትና አያቷን አያገባም:: በተጨማሪም የወንድሞቹንና የልጆቻቸውን ሚስት ልጇን፣ እህቷን ፣እናቷን አያቷን አያገባም:: የሚስቱን አያት እናት፣አክስት፣እህት ፣ልጅና የልጅ ልጅ አያገባም:: ይህ አንቀጽ ለሚስትም እኩል ያገለግላል:: ፍት.መን 34:853 ማር6፣17 1ቆሮ 5፣1

የክርስቲያን ጋብቻ እጅግ የተዋበ ሃይማኖታዊ ሥርዓት በመሆኑ ቤተክርስቲያን በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ምስክርነቷን ታጸናለች:: በምንም ነገር ሳይተፋፈሩ በሥጋ ወደሙ ተዋህደው ለጸሎት ካልሆነ በቀር ሳይለያዩና ሳይከላከሉ በደስታና በሠላም፣ ለዲያብሎስ መግቢያ ቀዳዳ አሳጥተው በፍቅር የሚኖሩበት የአብርሃም ቤት የክርስቲያን ትዳር ነው:: እግዚአብሔርን ማገልገላቸውን ለስሙም ያሳዩትን ፍቅር እናት ቤተክርስቲያን ሳትዘነጋ ደአሸናፊነትና የድል ምልክት የሆነውን ሥርዓተ ተክሊል ፈጽማ አክሊል ታቀዳጃቸዋለች:: አንድ ጊዜ ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

በሕይወት የሚገኝ በአጋጣሚ ከሥርዓት ከወጡ ግን በፍጹም የማያገኙት ታላቅ ስጦታ ተክሊል ነው::

ሥርዓተ ተክሊል

ተክሊል ክብር ማለት ነው:: ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ለተክሊል የሚያበቃውን መስፈርት አሟልቶ አስከተገኘ ድረስ ያለምንም ልዩነት ጋብቻው ይፈጽምለታል:: በንጽህናና በድንግልና ላለ ሁሉ ቤተክርስቲያን ያለዋጋና ያለምንም ልዩነት ሥርዓቱን ታከናውናለች:: በቃል ኪዳንና በቀለበት የተጀመረው የትዳር ሀሁ በሥርዓተ ተክሊል ይፈጸምና በሥጋ ወደሙ ይፀናል:: ጋብቻ ጋብቻ የሚባለው እንደ ክርስትና ትምህርት በተክሊልና በቁርባን ሲፈጸም ነው:: ያለ ሥርዓተ ተክሊል ጋብቻ እንዲፈጸም የቤተክርስቲያን ሕግ አይፈቅድም::

1. ለተክሊል የማያበቁ ሁኔታዎች

ሀ. ድንግልናን ጠብቆ አለ መኖር

ለ. የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኝ አለ መሆን

ሐ. ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ፈቃደኛ አለ መሆን

መ. ስለ ሥርዓተ ተክሊልና ሥጋ ወደሙ በቂ እውቀት አለማዳበር

ሠ. በረከትን ለማግኘት አለ መዘጋጀት

ንስሐ ዘማዊውን ድንግል ያደርጋል ስለዚህ አንድ ሰው ንስሐ ከገባ የሥጋ ድንግልና ባይኖረውም ተክሊል ለማድረግ አይከለከልም የሚሉ ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ይሰማል:: እዚህ ጋር መረዳት የሚያስፈልገው ነገር ተክሊል የልዩነት ምልክት መሆኑን ነው:: ድንግልናውን የጠበቀው ካልጠበቀው ስለሚለይ ለከፈለው መስዋዕትነት የሚሰጠው ሽልማትም ነው:: አንድ ጥያቄ እናንሳ በድንግልና ላልኖረው ተክሊል ከተደረገ በድንግልና የኖረው ምን ይደረግለት? መቼም የተሻለ ነገር እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነው ከተክሊል የሚሻል ነገር ደግሞ የለም:: አክሊሉ በድንግልና ላልኖረው ወገን ከተሰጠና ስለሚሻለው ነገር ምንም ሳይሰራ ከወሰደው በድንግልና የኖረው ሰው ያን ያህል ጊዜ እንደ እሳት በሚነድ ስሜት እየተፈተነ መታገስ ለምን አስፈለገው? ስለዚህ ንስሐ





ዘማዊውን ድንግል ያደርጋል የሚለው ትምህርት በተሳሳተ ግንዛቤ ለተክሊል ከተተረጐመ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ወሲብን ማስፋፋትና ዝሙትን ማበረታታት ነው :: በእርግጥ ንስሐ ዘማዊውን ድንግል ያደርጋል:: በመንግስተ ሰማያትም በሥጋው ድንግል ከሆነው እኩል በረከትን ከእግዚአብሔር ይቀበላል የመንፈስ ድንግልናው ተመልሷልና በሦስት ሰዓት የመጡትን በዘጠኝ ሰዓት ከመጡት ጋር እኩል ዋጋን የከፈለ ጌታ ዋጋቸውን ለእያንዳንዳቸው ይከፍላል:: ቤተክርስቲያን ከመንግሥተ ሰማያት ትርቃለች እንደተባለ ሃይማኖትን፣ ሥነ ምግባርን፣ ትውፊትን ጠብቆ ለማኖር፣ መሰረታዊ የቤተክርስቲያንም ትምህርት ስለሆነ "ተክሊል ለድንግል" የሚለው አስተምህሮ ለትውልድ ሊተላለፍ ይገባዋል::

ቤተክርስቲያን የተቀደሰውን ጋብቻ የምትፈጽምበት መጸሐፍ መጸሐፈ ተክሊል ሙሽሮች የሚቀዳጁት የክብር አክሊል የድንግልናና የቅን ፍርድ ምልክት እንደሆነ አበክሮ ይገልፀዋል:: እግዚአብሔርም የድንግልናቸው ዋጋ አድርጎ እንዲቀበለው ካህናት ይፀልያሉ:: በተክሊል የሚጋቡትን መሹሮችም ባላቸውን ወይም ሚስታቸውን በድንግልና እንደተቀበሉ በመላዕክት ፊት ይመሰክራሉ:: መጽ.ተክ8፣7(ገጽ 20) በሌላ አንፃር ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ጋብቻቸውን በስርዓተ ተክሊል ከፈጸሙ በኃላ ወደ ጥልና ወደ ፍች ሲያመሩ እንመለከታለን::በዚህ ዋናው ምክንያት በቤተ መቅደሱ መካከል የማይገባቸውን የድንግልና ክብር ለራሳቸው ስለሚያደርጉ እግዚአብሔርን እንደ መናቅ ስለሚቆጠር ነው:: ከጋብቻ በኃላ እግዚያአብሔር በበረከት ወደ ቤታችሁ እንዳይገባ ሀሰትን አድርገዋልና በትዳራቸው ሠላም ያጣሉ ወደ ፍችም ያመራሉ::

ሌላው የቤተክርስቲያን የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት "የመአስባን ተክሊል" የሚባለው ነው:: ድንግልናቸውን ባለመጠበቃቸው ምክንያት ስለ ድንግልና ክብር የሚሰጠው አክሊል ባይደረግላቸውም ከጋብቻ በፊት ስላደረጉት ኃጢያት ተናዘው የማዓስባን ጸሎት ተደርሶላቸው ጋብቻቸውን ማፅናት ይችላሉ:: መጽ.ተክ ክፍል 2 ገፅ 47

በተቀደሰው ቦታ ርኩሰት ቆሞ እየታየ እግዚአብሔርን ሳይፋር የደፈሩ ጨካኞች አግብተው ፈትተው፣አርግዘው፣በዘማዊነት ሲመላለሱ ኖረው ተክሊልን እንደተራ ነገር በመቁጠር ለታይታ ብቻ ወይም ለሰው ሁሉ ፍጹም አድርጎ ይቆጥራቸው ስለነበር እፍረታቸውን ለመሸፈን የእግዚአብሔርን ቅድስና የወንጀል ምሽግ ያደርጉታል፡፡ እጅግ የሚደንቀው ነገር ደግሞ የራሳቸውን ማህበራዊ ግንኙነት ለማጠናከር አበው በስቃይና በመከራ ያቆዩትን የቀና የፀና አስተምህሮ ስለ ጭብጥ ገብስ አሳልፈው በመስጠትና አዲስ ትርጉም በማበጀት የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሸቀጥ በመቸርቸር ለሰው ስሜት ሲሉ ምራላቸውን መሸጣቸው ነው ፡፡ እነዚሁ ሰዎች ራሳቸውን የቤተክርስቲያን ተጠያቂና ተጠሪ አድርገው ሲቆጠሩ መመልከት ደግሞ እጅግ ያሳፍራል፡፡

አንዳንድ ግለሰቦች ተክሊል ለመፈጸም የሚወስኑት ከሁለቱ አንዱ ያለሥርዓተተክሊል ጋብቻን አልፈጽምም ስለሚል ብቻ የርሱን ስሜት ላለመጉዳትና እርሱን ላለማጣት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የማይፈልጉትንና የማይገባቸውን ያደርጋሉ፡፡ ምንም በቂ እውቀት ሳይኖራቸውም በድንግዝግዝ የጌታ እንጀራ ይበላሉ፡፡ " ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም ሳይገባው የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት ..... " 1ኛ ቆሮ 11:27-30 ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ ተክሊልን ለካሜራ ማሞቂያ አድርገው በቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ቬሎ ሲጐትቱ ያስተዋልንበት የ1980ዎቹ መጀመሪያ አጋማሽ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ማንም ወደዚህ ቅድስና ሲመጣ በረከትን ለማግኘት ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ እግዚአብሔር እንዲባርክ፣ ጸሎትንም እንዲሰማ፣ ጋብቻውም ወደፊት እንዲቀጥል የዘለዓለም ሕይወትን ከሁሉ የበለጠ መሆኑን አውቆ ተክሊልንም ሥጋ ወደሙንም ለሕይወት ብቻ መፈለግ ተገቢ ነው፡፡

ካህናት እንደ መላእክት እየዘመሩ፣ መዘምራን እያሸበሸቡ ሙሽሮች እንደ ቅዱሳን ነጭልብስ ለብሰው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ





መመልከት የሚያስችል ፍጹም መንፈስን የሚገዛ ይገኝ ሥርዓተ ተክሊል ነው፡፡ የሰማያት መስኮት ተከፍተው እግዚአብሔር ልጆቹን ሲቀድስ በመንፈሳዊ ዐይን በገሀድ መመልከት ይቻላል፡፡ ለሰው የእግዚአብሔር ሙሽራ ከመሆን የበለጠ ሙሽርነት የለውም።

2. <u>ጋብቻቸውን ያለ ሥርዓተ ተክሊል ለፈጸሙ</u>

ሙሉ ሰው መሆን የሚቻለው በሒደት ነው፡፡ ጥበብ ደግሞ በተለያየ ጊዜ፣ ከተለያዩ ቦታ፣ ከተለያዩ ሰዎች ነው የሚገኘው፡፡ የቤተክርስቲያንን ትምህርት በጊዜው የሚያደርሳቸው አጥተው ጋብቻቸውን በመዘጋጃ ቤትና በሀገር ሽማግሌዎች ምስክርነት የፈጸሙ ብዙ ክርስቲያን ወገኖች አሉ፡፡ ይሔ እንዳለ ሆኖ አሁንም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር በቤተክርስቲያንም ፊት ጋብቻውን ለማደስ የሚፈልግ ክርስቲያን ቢኖር ቤተክርስቲያን የሚያስፈልገውን ሥርዓት ፈጽማ ጋብቻውን ትቀድስለታለች፡፡ ማንም ዘመኖቼ በከንቱ አረጁብኝ በማለት በቀቢጸ ተስፋ ሊኖሩ አያስፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ከዚችም ቀን ጀምሮ ይባርካል፡፡ ወደ እኔ ከተመለሳችሁ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ በማለት የታመነ ቃሉን የሰጠውም ለዚህ ነው፡፡ ት.ሐጌ 2:19 ት.ሚል 3፥7

ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀ ራሱን የቻለ ልዩ የጸሎት ክፍል በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኝ ካህናት ይህንን ጸሎት ካደረሱላቸው በኋላ እንደ ሌሎች ሙሽሮች ሁሉ ሥጋ ወደሙ ተቀብለው የአካል አንድነታቸውን ወደ መንፈስ አንድነት ማሳደግ ይችላሉ፡፡ በትዳራቸው የጐደላቸውን የሕይወት ቁልፍ ነገር ከእግዚአብሔር ስለተቀበሉ አኗኗራቸው ሁሉ ከዚህ ከኋላ ፍጹም ይለወጣል፡፡ በመጀመሪያም ጋብቻን ፈጽሜያለሁ በማለት ዝም ብለው ያልተቀመጡት በሕይወታቸው ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ነውና አግባብ ያለው የሕይወት ርምጃን መራመድ ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊነትን በሥጋዊነት መለወጥ የዘወትር ልማድ እየሆነ ባለበት ጊዜ በሥጋ የተጀመረውን ነገር እንደማይጠቅም አውቆ በመንፈሳዊነት ለማጠናቀቅ መነሳት ታላቅ የግስተዋል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ፈታኙ ነገር ከሁለቱ አንደኛው ወገን

ፈቃደኛ አለመሆኑ ነው:: በተለይ ባሉት ሚስቶቻቸውን ሲያበሳጩ ይታያሉ:: ቢሆንም እግዚአብሔር ጊዜ አለውና ትዳርን በችኮላ ከማፍረስ በትዕግስትና በጸሎት በሒደት ለመግባባት መሞከር ያስፈልጋል :: እግዚአብሔር የልብን መሻት ስለሚፈጽም ተስፋ መቁረጥ አይገባም:: ብቻ በጸሎትና በምልጃ ማሳወቅ ነው የሚያስፈልገው:: እግዚአብሔር በበረከት ሲመጣ ሁሉን ያስተካክላል::

## ምዕራፍ ሁለት

## የትዳር አጋሬን እንዴት ልምረጥ?

ትዳር በሕይወት ዘመን ከሚፈጸሙ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው:: የሕይወት ዘመን ስህተትን ላለመስራት እያንዳንዱ ሰው ምርጫውን ማስተካከል ይጠበቅበታል:: ከፊት ለፊቱ ያሉትን ዘመናት በፍቅርና በሰላም፣ በመግባባትና በመተሳሰብ ለማሳለፍ ይረዳው ዘንድ አስቀድሞ መጤን ያለበት ነገር ቢኖር ምርጫን ማስተካከል ነው:: በተለይ ለመንፈሳዊ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ፍጹም የሆነ ጤናማ ግንኙነት በዓለት ላይ እንደ መሰረተው ለማቆየት እያንዳንዷን ርምጃውን በአግባቡ መከወን ይጠበቅበታል:: አንድ ሰው ትዳርን በሚያስብበት ወቅት እንዲሁ ፍቅር ይዞኛል በማለት ብቻ ዘሎ የሚገባበት እቃቃ ጨዋታ አይደለምና የሚከተሉትን ሀሳቦች በተግባር ቢያከናውናቸው ወደ ተሻለ ግንዛቤ ሊያደርሱት ይችላሉ::

ሀ. <u>ፍቅርን መመርመር</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ነገሮችን ሁሉ በጥንቃቄ መመርመር እንደሚገባ ይመክራል:: የሚሰማ ማንኛውም ስሜት እንደመጣ ከማስተናገድ ይልቅ መንፈስን ሁሉ መመርመርና አዕምሮንም ማሰራት ከከፋ ነገር ይጠብቃል:: በሃይማኖት የሚኖር ሰው ራሱን በቃሉ በመፈተሽ እግዚአብሔር ወደሚባርከው ትዳር ለመድረስ የሚያደርገውን ቅድመ





ሁኔታ በማስተዋል ይፈጽማል:: ፍቅር እውርም ነው ዓይናማም ነው የሚያሳውረውም ሆነ ዓይናማ የሚያደርገው ራሱ ሰውየው ነው:: በስሜታዊነት ላይ ያተኮረ ፍትወታዊ ፍቅር ሊዘልቅ የሚችለው እስከ ሩካቤ ብቻ ነው:: በእውነት አምድ ላይ የተተከለው ግን ያብባል፣ ያፈራል፣ ያከብራል ወደ ጽድቅም ይመራል::

ብዙውን ጊዜ ለፍቅር የሚሰጠው አስተያየት በጎ ጐኑን ብቻ የተመረኮዘ ነው:: በእርግጥ ፍቅር ከእምነትም ከተስፋም ይበልጣል እምነት፣ፍቅር ተስፋ እነዚህ ሦስቱ ፀንተው ይኖራሉ ፍቅር ግን ከሁሉ ይበልጣል" 1ኛ ቆሮ 13:16 ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በፍቅር ሕይወት ውስጥ ችግር ሲፈጠር ይስተዋላል:: ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸውን ህገ ወጥ አድርገው ያቀርባሉና ነው:: በሁኔታዎች መካከል አልፈው ነገሮችን በትኩረት ስለማይከታተሉ የያዛቸው ፍቅር በሕይወት ዘመን አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰት ሌላ ጊዜ ሊያስገኙት የማይችሉት ጥልቅ የደስታ ስሜት ይመስላቸዋል:: በዚህ ጊዜ ይህን ፍቅር መሳይ ስሜት በማስተናገድ ትኩረት ሰጥተው ሳይመረመሩ ሮጠው ወደ ስህተት ይገባሉ:: በዚህም የነገው ኑሮ ይልቁንም [illegible] አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስከ ሕይወት ፍጻሜ ከእነርሱ ጋር የሚኖረውን የተባረከ ፍቅር ያጡታል::

የፍቅር ፍልስፍናቸውንም ሲቀጥሉ እንደ እነርሱ እምነት በልብ ውስጥ የሚሰማ፣ ለመረዳት የማይቻል፣ ሲያጋጥም ብቻ የሚታወቅ፣ ራስን የሚያስረሳ ነው ይላሉ:: ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ለፍቅር ከዚህ የተሻለ ትርጉም ይሰጥና ፍቅር ከሀሳባዊነት ይልቅ በተግባራዊነት ላይ ያተኮረ መሆኑን ያስረዳል " ፍቅር ይታገሳል፣ቸርነትንም ያደርጋል፣ አይበሳጭም፣ በደልንም አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሳል ፣ሁሉን ያምናል ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይጸናል ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም" 1ኛ ቆሮ 13:4-8

ማፍቀር መታደል ነው ሰው የመሆንም ምልክት ነው የተፈቀረ ሰው ምንም አይነት ሥሜት ስለማይሰማው ፍቅር ለእርሱ



www.ethiopianorthodox.org

ምንም ላይሆን ይችላል:: ላፈቀረ ሰው ግን ከሁሉ በላይ ነው ብዙ አይነት ስሜቶች ይሰሙታል ለምሳሌ:- ስለ አፈቀረው ሰው ያስባል ያሰላስላል፣ያፈቀረውን ሰው ሊማርክበት ወይም ሊያስደስትበት የሚችለው ነገር ካለ ያፈላልጋል::አንዳንዴ እንቅልፍን ሊያጣ ምግብም ሰአግባቡ መመገብ ሊያቆም ይችላል:: ብቸኝነትን የሚመርጥ በትንሽ ነገር የሚከፋውም ይሆናል:: ይህ ሁሉ የፍቅር መገለጫ ባህሪይም ነው ተብሎ ቢታመን እንኳን የማይካደው ሀቅ ግን በፍቅር መያዝ አንድ የሕይወት ጣፋጭ ክፍል መሆኑ ነው:: ዋናው ጥያቄ ግን ፍቅር ሁሉንም አሸንፎ ለዘለዓለም ይኖራልና ሁሉንም አሸንፎ የሚኖረው ፍቅር የትኛው ነው? የሚለው ነው::

ስሜታዊ የሆነ ፍቅር በሰኮንዶች እይታም በሰው ላይ ሊፈጠር ይችላል እንዲህ አይነቱ ነገር ከዛር መንፈስ የማይተናነስ ነው:: ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን፣የመድረክ ተዋናዮችን ፣ስፖርተኞችን እና ሌሎችንም ዝነኞች አፈቀርኩ ብሎ የሚያብድ ሰው በየ አጋጣሚ ይስተዋላል:: በማንኛውም መስፈርት እነዚያ ሰዎች ጋር የሚያደርሰው ምንም ነገር ሳይኖር በወረት ብቻ በቅጽበት ዕይታ እራስን ለአደጋ ማጋለጥና ፍቅር ይዞኛል ብሎ ማሰብ በራስ ላይ ማፌዝ ነው:: እውነተኛው ፍቅር አላማን የሚያስናክል ማንነትን የሚያሳጣ አይደለም የሚወደውን ሰው ለአጭር ጊዜ ማግኘት ሳይሆን እስከ ዘለቄታው ከእርሱ ጋር እንዲኖር ስለሚፈልግ በአላማ፣በእቅድ፣በተለይ በእምነት አንድ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ለማጠናከርና ለማጣጣም በትኩረት ሁሉንም ነገር ያስኬዳል::

ሰ. ለመንፈሳዊነት ለሃይማኖት ማድላት

ያለ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም:: አስቀድሞ መንፈሳዊነትን ገንዘብ ያደረገ ወጣት ከእግዚአብሔር በፊት የሚያስቀድመው ምንም ነገር አይኖርም:: እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ እንደ ፈቃዱ መኖር ደመወዙ የዘለዓለም ሕይወት ነው:: ነብዩ ዮናስ ወደ ተርሴስ ሊኮበልል በተነሳበት ጊዜ የተሳፈረበት መርከብ ተናወጠ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር ሌሎች ተሳፋሪዎች ቀስቅሰው ወደ አምላኩ





እንዲጸልይ ተናገሩት:: ችግሩ የተፈጠረው በእርሱ ምክንያት ነውና ስራህ ምንድነው ብለው ጠየቁት ዮናስም ሲመልስ ባህሩንና የብሱን ሰማይና ምድሩን የፈጠረውን እግዚአብሔርን ማምለክ ነው ሥራዬ አለሁ:: ት.ዮናስ 1:1-8 ዮናስ ሌላ ሥራ የለውም ለማለት አይደለም የዓመት ልብሱን የእለት ጉርሱን ከሚያገኝበት ሥራ እግዚአብሔርን ማምለክ ታላቅነት ነውና ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔርን ክብር ገለጠ:: ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማህፀነ ዮርዳኖስ በጥምቀት የተወለደ በሥጋ ወደሙ የከበረ በሜሮን የታተመ የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያን ደግሞ ለመንፈሳዊነቱና ለሃይማኖቱ በማዳላት ከዓለማዊ ሰው የሚለይበትን ነገር ማሳየት አለበት:: " .... ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ...... " ማቴ 5:13 በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ዓላማን የሚያስቱ መንፈሳዊነትን የሚፈታተኑ ብዙ ነገሮች አሉ:: በነዚህም ምክንያት ሰዎች ጋብቻቸውን ከማን ጋር እንደሚፈጽሙ ግራ ገብቷቸው ጋብቻዬን ከማን ጋር ልፈጽም? የሚለው ጥያቄ የዘወትር ጥያቄያቸው ነው:: በሃይማኖት ለመኖር ስታስብ የሚፈታተኑና ምርጫችሁን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ የሚመሩ የሰውን ስሜት የሚገዙ ዓለማዊ እይታዎችና አስተሳሰቦችም አሉ::

1. ውበት

" ውበት ሀሰት ነው ደም ግባትም ከንቱ ነው" ምሳሌ 31:30 የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም አንድ እጅግ በተዋበና በማያንፀባርቅ መጠቅለያ የተጠቀለለ እቃ በውስጡ ያለውን እቃ የከበረና የተወደደ መሆኑን በፍጹም ሊገልጥ አይችልም:: እንዲያውም በውስጡ ያለው እቃ ምንም ጥቅም የሌለው ከላይ ካለው መጠቅለያ በእጅጉ የሚያንስ ሊሆን ይችላል:: በአብዛኛውም ውበት እንዲሁ ነው ከላይ ሲያዩት መልካምና የሚማርክ ይሁን እንጂ ውስጡ ባዶ እንደሸንበቆ በትል የተበላ በማር የተጠቀለለ እሬት፣የጠቆረ የጨቀየና ለኃጢአት በሚያነሳሳ ተንኮል የተሸፈነ ብቻ ሊሆን ይችላል:: ውበት እጅግ በጣም አደገኛ አስመሳይና አታላይ ነገር ነው:: ዓለሙ በዚህ ነገር

ሲጕዳ እንመለከተዋለን "በሬ ሆይ በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ" የሚለው የአበው ብሒል ለረጅም ዘመናት የተዘነጋ ይመስላል::

ውበት አሳዳጅ መሆን ነውርና ነቀፋ የሌለበትን ፍቅር፣ ከንፁህ ህሊና የሚመነጭ ቅዱስ ሀሳብን፣ ከመልካም ልብ የሚፈልቅ መከባበርን ፍፁም እንዲዘነጋና ነገ በአንድ ምክንያት ሲፈርስ፣ ሲጠፋና ፣ሲበላሽ ለሚችለው ነገር ትኩረትን ሰጥቶ የሙጥኝ ማለትን ያመጣልና ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ አይደለም:: በጣም የሚገርመው ነገር ራሳቸውን በትልቅ ሰገነት ላይ ሰቅለው ውበታቸውን ለትዳር መመረጫ ቀዳሚ መስፈርት የሚያቀርቡ ሰዎች አለመታጣታቸው ነው:: መንፈሳውያን ነን ብለው የሚያስቡት ሳይቀሩ ውበትን የሁሉ ነገር መጀመሪያ በማድረጋቸው ብፍለጋ ሥራ ተጠምደዋል:: ሁሉን ሲያማርጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ሲገፉ ይኖሩና በመጨረሻ እድሜያቸው ሲያልፍ የወደዱትን ያጣሉ የጠሉትን ይወዳሉ:: አወዳደቃቸው ኃያል ስለሚሆን ራሳቸውን በዓለማዊነት ውስጥ ሊሸሽጉት ይፈልጉና ያጡትን ውበት ለማግኘት ሲሯሯጡ የወደዳቸውን እግዚአብሔርን ያስቀይማሉ::

ለራሳችን እስኪ ጥያቄ እናንሳ የእኔ የትዳር ጓደኛ መሆን ያለባት መልከመልካም ነውን? እንበል ሁሉም ሰው የሚያገኘው መልስ አንድ አይነት ነው " አዎ" የሚል ምክንያቱም ማንም ሰው አጋሩ የተዋበና ያማረች ቢሆን አይጠላምና:: እንደነፍስ ጉዳይ አድርጐ መቁጠር ግን የሚገባ ነገር አይደለም:: ይልቁንም መንፈሳዊ ሰው ለእኔ ውበት ማለት ንጹህ ህሊና፣ አስተዋይ አዕምሮ፣ አፍቃሪ ልብ ነው ይላል:: እግዚአብሔርን የምትፈራ ሰውን የምታፍርና የምታከብር፣ ሰብአዊነት ያላት ከሆነች ደግሞ ለእኔ ከውቦች በላይ ውብ ናት በማለት ልቡን ያጽና::

ጥበበኛው ሰሎሞን " የወርቅ ቀለበት በእሪያ አፍንጫ ላይ እንደሆነ ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንዲሁ ናት" ምሳ.11:22 ነብዩ ሲገልጥ የፈለገውን ነገር እናስተውል ወርቁ ወርቅ ቢሆንም የእርያ ወርቅ ነው፡





ውበት ቢኖርም [illegible] የአዕምሮ ድሃ ከሆነ ምንም አይጠቅምም:: ለብዙ ወራትና ለብዙ ዘመን አብሮ ለመኖር ከሆነ የሚታሰበው ያለው ውበት እንዳለ ሊቀጥል አይችልምና ሰውን በሰውነቱ በአፍቃሪ ልብ ከመቀበል ውጭ ውበትን ብቻ መመልከት ዘላቂነት የሌለው ግንኙነትን ለመመስረት መዘጋጀት ነው:: ውበት ቢኖርም ባይኖርም የሚያኮራና የሚያሳፍር ነገር አይደለም ለመግለጥ እንደተሞከረው አስፈላጊው ነገር ከውጫዊ ውበት ይልቅ ውስጣዊ ውበት ነው:: እግዚአብሔር ሁሉንም በአርያውና በአምሳሉ ውብና ድንቅ አድርጎ እንደፈጠረ መዘንጋት የለበትም::

2. ሀብት፡-

ፍቅር በገንዘብ የሚገዛ ሸቀጥ አይደለም ገንዘብ ደስታን ፣ሰላምን ለሰው አስፈላጊ የሆነውን የመንፈስ እርካታ ሊገዛ አይችልም:: ትዳርን ለመፈጸም ሲነሳሱ ለሠርግ ስለሚወጣው አላስፈላጊ ወጪ በመጨነቅ ያለ ጋብቻ በሚፈጸም ወሲብ እየተቃጠሉ የሚያመነዝሩ ወገኖች አሉ::ትዳር ለመመስረት ብዙ ሀብት አስፈላጊ እንደሆነ ስለሚያምኑ ነው:: ይህንን በሰፊው እንመለስበታለን:: ለመሰረታዊ ፍላጐት ከሚያስፈልገው ውጭ በተትረፈረፈ ሀብት ውስጥ ያለምንም ጥረትና ሥራ ዘሎ ለመዘፈቅ መሞከርና ለሀብት ሲሉ ወደ ጋብቻ መግባት መጨረሻውን አሳዛኝ ያደርገዋል:: ክብር የሆነ ሰውነትን እንደ እቃ ለሀብት መሸቀጥ የሞራል መላሸቅን ያስከትላል ትርፍ የሕሊና ጠባሳ ነው::

እንደ ውበት ሁሉ ገንዘብ የሚጠፋበት ጊዜ ሊመጣ አይችልም ብሎ መገመት ስህተት ነው:: ገበያው የሚደራው በሀብትና በውበት መካከል ሆኖዋል:: ባለሀብት የተቀበችውን በገንዘብ ይገዛል:: እርሷም ለተወሰነ ጊዜ ሥጋዋንና ሕሊናዋን ትሸጥና ሁኔታዎች ሲመቻቹላት በአሸዋ ላይ የመሰረተችውን የፍቅር ቤት አፍርሳ ምንም ካላወጣችበት ሀብት ተካፍላ ትጠፋለች:: እርሱም ፀፀትን ባልንጀራው አድርጐ የሴት ዘር የተባለን ሲረግም ይኖራል:: በሌላ ወገን ፍጹም የማይመጣጠኑ የማይግባቡ እናትና ልጅ የሆኑ ሰዎች ጋብቻ ሲፈጽሙ እናያለን

ከፍቅር የተነሳ ነው ብሎ ለማመን በጣሙን ይከብዳል። እንዲያውም የተጠና ውጊያ የሚያከናውን ጠላትን በጉያ መታቀፍ ነው። የሚፈልገውን ገንዘብ ካገኘ በጊዜ ይሔዳል ካልሆነም ወራሽ እስኪሆን ይጠብቃል።

አሁንም የቀደመውን ጥያቄ መንፈሳዊ የሆነ ሰው ደግሞ ያንሳ እኔ ማግባት ያለብኝ ሀብታም ነውን ? ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ያስተምሩናል " ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚል ለእርሱ እግዚአብሔርን መምሰል አጅግ ማትረፍያ ነው ወደ ዓለም ምንም እንኳን አላመጣንምና አንዳችም ልንወስድ አይቻለንም ምግብና ልብስ ካለን ግን እርሱ ይበቃል" 1ኛ ጢሞ 6:7-8 ከዚህ የዘለዓለም ኪዳን ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል በመነሳት እንዲህ በማለት ራሱ ላነሳው ጥያቄ መልስ ይስጥ። በርግጥ ፍቅርና ትዳርን ለማጽናት ልጆችንም ለማሳደግ ገንዘብ ያስፈልጋል ነገር ግን ስለ ጭብጥ ገብስ፣ስለ ሳንቲም ድቃቂ ስለ ልብስ እላቂ ብዬ ወደማላምንበት ትዳር አልገባም ይህም ለእራሴ የምገባው ታላቅ ቃል ኪዳን ነው በሕይወት ዘመኔም ትልቁ ውሳኔዬ ነው ይበል። ፍቅር ሳይኖር ሀብትን ብቻ መሰረት አድርጐ ወደ ትዳር መግባት ራስን ለማጥፋት መወሰን ነው።

ለጊዜያዊ ደስታ በማሰብ የሚደነቀውን የእግዚአብሔር ብርሃን በድቅድቅ ጨለማ በመለወጥ የተከበረውን የእግዚአብሔር አላማ እንደ ቁሳቁስ በገንዘብ መመዘን አይገባውም " እንጀራን ለሳቅ የወይን ጠጅንም ለሕይወት ደስታ ያደርጉታል ሁሉም ለገንዘብ ይገዛል" መክ 10:19 የመጨረሻው ዘመን እየቀረበ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉም ራሱን ወዳድ ስለሚሆን ሀብትን በእግዚአብሔር ላይ አምላክ አድርጐ መሾም ይጀመራል። በገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው "አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ" 1ኛ ጢሞ 6:10

አሳሳቢው ነገር ደግሞ ሰው ሁሉ የሚንሰፈሰፍለትና ስብዕናውን የሚያጣበት ሀብት ከሚመጣው ቁጣ የሚያድን አለመሆኑ ነው።





ስለዚህም ለአንድ ነገር ብቻ ብሎ መስመሩን የሳተ ሰው ወይ ከሚፈልገው ነገር አይሆን ወይ ከእግዚአብሔር አይሆን የውሃ ላይ ኩበት ሆኖ ይቀራል"በእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ብራቸውና ወርቃቸው ሊያድናቸው አይችልም እርሱም በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ፈጥኖ ይጨርሳቸዋልና ምድር ሁሉ በቅንዓቱ እሳት ትበላለች" ሶፎ 1:18 ካልተባረከው ብዙ ነገር የተባረከው ፍርፋሪ ይሻላልና ሁካታ ካለበት ሀብት ድህነት ያለበት ሰላም ይጣፍጣል። በመሆኑም መንፈሳዊ ሰው ሆኖ በሃይማኖት መኖር ሃብትም ውበትም ነው። እረኛው እግዚአብሔር ነውና በለመለመ መስክ ያሳድራል በእረፍት ውሃ ዘንድም ይመራል በእውነት ያለ ሀሰት እግዚአብሔርን የሚጠባበቁ አያፍሩም ከሀብትና ከውበት ይልቅ መንፈሳዊነትን ወደዋልና እግዚአብሔር ፍቅር ያለበትን ትዳር ይሰጣቸዋል ፍቅር ያለው ጌታ አለው ጌታ ያለው ደግሞ ሁሉም አለው በከንቱ ነገር የተደገፈ ግን ድጋፉም ይወድቃል እርሱም ይሰበራል። " አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም በከንቱ የሚጋበዙ ያፍራሉ" መዝ 24:3

ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያን መከተል

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የትዳር ጓደኛን እንዴት መምረጥ እንደሚቻል ፍንጭ የሚሰጡ ገጸ ምንባባትን እናገኛለን። የአብርሃምን የይስሀቅን የያዕቆብንና የርብቃን ታሪክ በማንሳት በትዳር ምርጫ ውስጥ የእግዚአብሔር እገዛ እንዴት እንደሚገለጥ እንመልከት። እግዚአብሔር አብርሃምን በነገር ሁሉ ባረከው እድሜው እያረጀ በመጣበት የሽምግልናው ዘመን ለልጁ ለይስሀቅ ሚስት ሊድረው የልጁንም ዓለም ለማየት ፈለገ፡ እያውብርንም አብርሃም አስምሎታልና ታማኝ ባሪያነቱን ለማረጋገጥ እግዚአብሔርን ምርኩዝ መሪ አድርጎ ከአብርሃም በተቀበለው ትዕዛዝ መሰረት ለይስሀቅ ሚስት ይፈልግ ዘንድ ተነሳ አስተዋይ የነበረው እያውብር ተልዕኮውን ለመወጣት የራሱን የምርጫ መስፈርት በማውጣት የእግዚአብሔርም ምርጫ መሆኑን ለማረጋገጥ በጥንቃቄ ይመረምር ጀመር።

በእንቅስቃሴውም ውስጥ ለጌታው ልጅ ሚስት የምትሆነው በመልካም ሥነ-ምግባር ተኮትኩታ ያደገች መሆን እንዳለባት አጥብቆ ያምን ነበር:: ይህንንም ፍላጐቱን የመልካምና የበጎ ነገር ሁሉ አባት የሆነው የአብርሃም አምላክ ስለሚደግፍለት መንገዱን በብርሃን ይሞላለትና ከተሳሳተም ምርጫ ይጠብቀው ዘንድ በጸሎት ጠይቆ ነበር:: ለሰው መልካም የምትመስል ፍፃሜዋ ግን ሞት የሆነ መንገድ አለችና አካሄዱን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ:: የርብቃንም ባለሟልነት ወይም ትክክለኛ ምርጫ መሆኗን ለማረጋገጥ ትህትናንና ትዕግስትን የሚጠይቅ መልካም ሚስት ብቻ ልትመልሰው የምትችለውን ጥያቄን ለመጠየቅ ወሰነ "ውሃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብይ የምላት እርሷም ጠጣ፣ግመሎችህንም አጠጣለሁኝ የምትለኝ ቆንጆ እርሷ ለባሪያህ ለይስሀቅ ያዘጋጀኃት ትሁን" አለ:: ለርብቃ በጣም ፈታኝ ነገር ነው ምክንያቱም ለእርሱ ልታጠጣው ትችላለች ይህ ድንቅ ነገር አይደለም ለግመሎቼ አጠጭ ማለት ግን ጥልቅ ስብዕናን ይጠይቃል:: ግመል ውሃ መጠጣት ከጀመረ በቶሎ አያቆምም አንዴ ከጠጣ ደግሞ ሳይጠጣ አርባ ቀን መቆየት ይችላልና ለዚህ ደግሞ ብዙ ውሃ ማጠራቀም አለበት፣ እነዚህ ግመሎች ብዙ ከመሆናቸውም በላይ በበረሃ በውሃ ጥም ሲንገበገቡ የከረሙ ናቸው:: ርብቃም ወደ ቤቷ በጊዜ መመለስ አለባት:: እርሷ ግን ይህን ሁሉ ነገር በትእግስት ተወጣችው::

የሚፈልገውን ሁሉ በመፈጸሟ የእግዚአብሔር ፈቃድ በእርሷ ላይ እንደሆነ ከማረጋገጡም በላይ ከእናት ልጅ ይልቅ ቸር ሆነችለት ወደቤቷም ተመልሳ መንገደኛውን የበረሃ ሰው ያለበትን ሁኔታ በማስረዳት አባቷ ማደሪያ እንዲፈቅድለት ለግመሎቹም
ምግብእንዲያዘጋጅ አግባባችው " እግዚአብሔር ያዘጋጃት ሴት እርሷ ትሁን ,...... " ዘፍ24፡44 ርብቃ በሰው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም የተዘጋጀች ናትና ለእስራኤል ሁሉ አባት የሆነውን ያዕቆብን ወለደች ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል ተብሎ በነቢይ እንደተነገረ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከያዕቆብ ዘር ተወለደ መልካም ልጅ





ለቤተሰቦቹ መኩሪያ ነውና የርብቃ ወላጆች ልጃቸውን እንዲህ ሲሉ መረቋት "እህታችን ርብቃ እልፍ አእላፋት ሁኚ ዘርሽም የጠላቶቻችንን ደጅ ይውረስ" እግዚአብሔር ወዷታልና ባርኳት የነገድ ሁሉ አባት የሆነውን ያዕቆብን አስገኘች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የጠላታችንን የዲያብሎስን ደጅ ወርሶ ነፍሳትን ከሲኦል አወጣ:: ከዚህ አንፃር መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች እንደ እያውብር እንድንከተል ይጠቁመናል::

1. እግዚአብሔር የልብን መሻት የሚያከናውነው በጸሎት ነው በጸሎት የሚጠይቁትን በልግስና ይሰጣልና ሥራውን ይሰራለት:: ጉዳናውንም ያቀናለት ዘንድ ፈጣሪው መሪው እንዲሆን ተማፀነ ዘፍ 24:12
2. እምነቱ ፍፁም ነበርና እግዚአብሔር ለይስሐቅ መልካም ሚስትን እንደሚያዘጋጅለት አንዴም አልተጠራጠረም ጌታ የሚያደርግለትን ነገር በትዕግስት ጠበቀ ዘፍ 24:14
3. እግዚአብሔር በሥራው መቼም መች አይሳሳትም:: እያውብር በእርግጠኝነት አምላክ ወደ ትክክለኛ ምርጫ ሊመራው እንደሚችል ያውቃል ዘፍ 24:14
4. በሚያደርገው እያንዳንዷ ነገር ውስጥ እግዚአብሔር ላቀረበው ጸሎት መልስ እየሰጠው እንደሆነ አበክሮ ይከታተል ነበር:: ዘፍ 24:27
5. እግዚአብሔር ሊያዘጋጃት የሚችላት ልጅ ግሩም ባህርይ ያላት የታረመችና የአብርሃምን አምላክ የምትፈራ እንደምትሆን ያስባልና ይህንን ለማረጋገጥ መስፈርት አደረገ እንዳሰበው ይሳካለትም ዘንድ ተመኘ ዘፍ24:44

አብርሃም እንደነገረው በጌታው ሃሳብ ላይ ተመስርቶ የተከተለው ቅደም ተከተል ፍፃሜው አማረለት ሰው ሁሉ ይህንን ታሪክ በታሪክነቱ ብቻ ሳይሆን በራሱ የሕይወት ተሞክሮ ውስጥ በየጊዜው ቢጠቀምበት የአብርሃምን ምኞት የፈፀመ የእያውብርን ልፋት የቆጠረ እግዚአብሔር የሐሳቡን ይሞላለታል:: አብርሃም እንዲህ አለ " እኔም አብሬ

ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት አትውሰድ በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሀለሁ" ዘፍ 24:3 :: በባህል ፣ በሃይማኖት ከሚመስሉት ወገኖቹ ለልጁ ሚስት ፈለገ እንጂ በነውርና በርኩሰት ከሚያጌጡም ከከነዓናውያን አልፈለገም። በእምነትና በሥነ ምግባር ታንፃ ያደገቺው ርብቃ ግን ለልጁ መድኃኒት ሆና ከእናቱ ከሣራ ሞትም አጽናናችው ይስሀቅም ወደዳት። በእምነትና በጸሎት የተደገፈ እግዚአብሔር ያለበት ምርጫ ፍፃሜው ያምራል።

መ. ግፊቶችን መቋቋም

የሚወዷችሁና የሚያከብሯችሁ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ገደባቸው ያልፍና የሕይወታችሁ ውሳኔ ላይ ሳይቀር በቀጥታ ታዛ ተሳታፊ በመሆን የእነርሱን አቋም እንድትደግፉ ይፈልጋሉ። በልባቸው እንድታስቡ፣በሳንባቸው እንድትተነፍሱ ይጥራሉ መዋደድ መልካም ሆኖ ሳለ ሁሉን ከመጠን በላይ ማድረግ ግን በማንኛውም መንገድ አስፈላጊ አይደለም። የሚበጀውንና ለእርሱ ኑሮ ተስማሚ የሚሆነውን የሚያውቀው እርሱ ራሱ ባለቤቱ ብቻ ነው። ወደፊት የሚመጣውንም ሕይወት የሚኖረው እርሱ ራሱ ብቻ ነውና የሚጐዳውንና የሚጠቅመውን ነገር ለመወሰን የማንም ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ አይሆንም።

ቤተሰብ ወይም የንስሐ አባት የሥራ ጓደኛና የቅርብ ዘመድ አልፎ አልፎ ትዳር እንድትመሰርቱ መምከር ብቻ ሳይሆን የትዳር ጓደኛን እስከ መምረጥ ድረስ ያለውን ሀላፊነት ሊወስዱ ይፈልጋሉ። በወስጡ መልካም የሆነ ሀሳብ የለበትም ማለት አይደለም። ድርሻቸው ግን እከሌን አግባት ወይም እከሌን አግቢው ብሎ መገፋፋት ለማሳመን መሞከርና ተጽዕኖ ማድረግ ሳይሆን ለትዳር ይበጃል ብለው ያሰቡትን ሰው መልካምነት በመጠቆም እርሱ ራሱ ባለቤቱ ሁኔታውን እንዲከታተልም ማድረግ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን የራሱ ችግር አለበት በነፃ ሀሊና የሚከናወን ድርጊትና በቅድመ መረጃ ላይ የሚደረግ ክትትል በውጤቱ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።





ወደ ቤተክርስቲያን የሚቀርቡ ወጣቶች ሳያውቁት በተጽዕኖ ሥር የሚወድቁበት አጋጣሚ ይስተዋላል። ወጣቶቹ ለትዳር የደረሱ የራሳቸውን ኑሮ ለመምራት የተዘጋጁ ከመሰላቸው አብዛኛዎቹ መምህረ ንስሐዎች ልጆቻቸውን ለትዳር እንዲዘጋጁ ይመክራሉ። ይህ ቅዱስ ሀሳብ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ሌሎች መምህረ ንስሐዎች ልጆቻቸውን ከማስገደድ በማይተናነስ ተጽዕኖ ሲገፏቸው እንመለከታለን። እርሷ ያለባትን የኑሮና የኢኮኖሚ ችግር በመመልከት ብቻ ከእርሱ ጋር እንድትኖር ያላመነበትን ነገር እንዲያደርግ ያስጨንቁታል። ይልቁንም ህልም እንዳዩላቸው ከእግዚአብሔርም የሆነ መልዕክት አስመስለው የሚናገሩ አሉ። ይኼ አካሄድ ፍፁም አሳሳች ነው የሚያስፈልጋቸውን በጸሎት መጠየቅ መልካም ሆኖ ሳለ በራዕይ እና በሕልም ጊዜን ማጥፋት ከንቱን ድካም ነው።

በመሠረታዊ ሀሳብ ደረጃ ስንመለከተው ሰው በህልሙ እጅግ ብዙ ነገሮችን ይመለከታል በተለያየ ጊዜም " ሕልመ ሌሊት" ያጋጥማል ታዲያ በሕልሙ ሌሊት የተፈጠረውን ነገር አይቶ ለጋብቻ የሚነሳ ከሆነ ባለ ማስታዋል የሚደረግ ሩጫ ነው። በመሆኑም ከዚህ አንፃር የሚመጡ ጋብቻዎች ተቀባይነት ሊኖራቸው አይችልም። መንፈሳዊውን ነገር ለመመርመር ልቦናን ማንቃት ይገባል እንጂ ህልምን ለተመለከተው ሰው በምትሰጡት ክብርና ባለችሁ መቀራረብ ብቻ እግዚአብሔር ፍቃድ ተፈጽሞአል ማለት ቀልድ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ በየገዳማቱ የሚደረገው ጉዞ አልፎ አልፎ ከዕራይና ከሕልም ጋር እየተያያዘ ነውና ጥንቃቄ ሊቸረው ይገባል። በአንፃሩም ምንም በልቧ ውስጥ የተፈጠረ የፍቅር ሀሳብ ሳይኖር ፍቅርን በጉልበት ማምጣት የሚቻል ይመስል ነገ ከነገ ወዲያ እያደር ትዋደዳላችሁ በማለት እርሱን ከእርሷ ጋር በማድረግ ውለታን ሊውሉለት ይፈልጋሉ።

አባቶችን ማክበር የካህናትን ምክር መስማት ከጓደኛ ጋር መመካከር ሃይማኖታችንም ባህላችንም ያስተማሩን ነገር ከመሆኑም በላይ መልካም አስተሳሰብ ካለው ክርስቲያን የሚጠበቅ ነው። ነገር ግን

በሌሎች ሀሳብ ተመርቶ ሰዎችን ላለማስቀየም በማለት ብቻ ኑሮን ወደማይፈልጉት አቅጣጫ መምራት የእግዚአብሔርም ፈቃድ አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር የሚያምንናበራስ መተማመን ያለው ወጣትም የሚያደርገው አይደለም፡፡ ከታረመው ባህል ከተከበረው ሃይማኖት የምንገነዘበውን መልካም የመከባበርና የመተሳሰብ መንፈስ ዓላማውን በሳተ መልኩ ያለነፃነት በግፊት ለመጠቀም መነሳት አያስፈልግም፡፡

ሠ. ለፈተና የሚያጋልጡ ልዩነቶች አለመኖራቸውን ርግጠኛ መሆን

ወደፊት ሊያገቡት የወሰኑትን ሰው በሚመርጡበት ወቅት ሊጤን የሚገባው ሌላው ነገር በግለሰቦቹ መካከል ያለው መሳሳብ እስከ ትዳር የሚዘልቅ ከትዳርም በኋላ የሚቀጥል መሆኑን ነው፡፡ ተመሳሳይ ባህርይ ፍላጐትና ሥሜት ያላቸው ሰዎች በትዳራቸው ውስጥ እየተግባቡ ለመቀጠል ያን ያህል አስቸጋሪ የሆነ ፈተና ሲገጥማቸው አይታይም፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ምንም ምን የሚያመሳስላቸው ነገር ሳይኖር እንኳን ሊጋቡ ሊግባቡ በማ ችሉበት ርቀት ላይ ቆመው ሳለ በአንዳች ሥሜት ብቻ ተገፋፍተው ትዳር ይመሰርቱና የተከፋፈለች መንግስት እንደማትፀናው ሁሉ ትዳራቸውም ይፍረከረካል፡፡ በተጋቢዎች መካከል ያለው ውህደት ከብዙ ነገሮች አንፃር ሊስተዋል ይችላል፡፡

1. ዕድሜ

ዕድሜ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ የተለገሰው ታላቅ ትምህርት ቤት ነው ሁሉን ያሳያል፣ ሁሉን ያሳልፋል፣ ሁሉን ያመጣል ጋብቻ ደግሞ ለአንድ ጊዜ ብቻ ታይቶ ወይም አስደስቶ የሚጠፋ ቀልድ አይደለም፡፡ የአያ"ላክም በጎ ሀሳብ ሰው በትዳር እንዲተሳሰር የበሰጠ እንዲቀራረብ ዘላቂነት ያለው ጥምረት እንዲፈጥር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁለት ነገሮች መመርመር አለባቸው የመጀመሪያው ትዳር ለመመስረት ደርሻለሁ ወይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በእኔና በእጮኛዬ መካከል የሚኖረው የእድሜ ልዩነት ምን ያህል መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡





ህፃን እያለ እንደ ህፃን የሚያስበው ጉልማሳ እያለ እንደ ህፃን አያስብም ሽማግሌውም እንዲሁ እያንዳንዱ የእድሜ ክፍል በሰው ሕይወት ውስጥ የሚከናወኑ ብዙ አብይ ቁምነገሮችን ይዞ ይመጣል "ዳሩ ግን ማግባት ወደ ሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ስለ ድንግልናው ያፈረ ቢኖር የወደደውን ያድርግ ኃጢአትም የለበትም" 2ኛ ቆር 7:36 እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አስተምህሮ ለማግባት የተገባ የእድሜ ክፍል አለ ማለት ነው፡፡ ምንም ሊያከራክር የማይችል አንድ ሀቅ አለ በጣም ወጣቶች ሆነው ወደ ጋብቻ የገቡ ተጓዳኞች እስከ መጨረሻው ለመዝለቅ በሚያደርጉት ውጣ ውረድ ሊነገር የማይችል ፈተና የሚገጥማቸው መሆኑ ነው፡፡ ትዳር ምንምፈተና የሌለበት ፍቅር ብቻ ያለበት የህልም ዓለም አይደለም፡፡ ወደ ትዳር መምጣት ትልቅ ሰው የመሆን ምልክት እንደሆነ ስለሚቆጠር እንዲሁም ያለባቸውን የወላጅ፣ የማህበረሰብና የጓደኛ ተጽዕኖ ለመሸሽ ገና ፍትፍት በሚመገቡበት እድሚያቸው አጥንት ይታገላሉ፡፡ " ብታገባ ግን ኃጢአት አትሰራም ድንግሊቱም ብታገባ ኃጢአት አትሰራም ነገር ግን እንዲህ በሚያደርጉ በሥጋቸው ላይ መከራ ይሆንባቸዋል" 1ኛ ቆሮ 7:28 በማለት ሊታገሉት የሚገባ ፈተና ከፊት ለፊት እንደሚጠብቅ ይጠቁማል፡፡

ለሁሉም አይነት ችግሮች ትክክለ... ጋብቻ ሊሰጠን ይችላል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው፡፡ ይልቁንም አዳዲስ የሆኑ ችግሮችም ሊፈጠሩ የሚችሉበት አጋጣሚ በየጊዜው ይከሰታል፡፡ በታላቅ ጉ...ት ሲጠበቅ የነበረው ወሲባዊ ግንኙነት የተጠበቀውን ያህል አጓጊነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ሲመጣ ጋብቻን መፈጸማቸው ስህተት ሆኖ ያገኙታል፡፡ ትዳራቸው ለሚጠይቅባቸው ኃላፊነት ራሳቸውን ብቁ አድርገው ስለማይቀርቡ ትዳሩ ይናጋል፡፡ ወጣቱ በልዩ ልዩ ቦታዎች ጊዜውን አሳልፎ በቤትና በተለያዩ ቦታዎች ለትዳር አስፈላጊ የሆነውን ላያከናውን ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ወጣቷ እራሷን የፍትወት ማርኪያ እቃ እንዳደረጋት ትቆጥራለች፡፡ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶች ሳይበስሉ ወደ ትዳር ስለገቡ ድሮ እንደነበሩት ለመሆን ያስቡና በራሳቸው ... ሀሪግ መምዘዝ ይጀምራሉ፡፡ በአግባቡ መከወን ያለበትን የቤት ሥራ



www.ethiopianorthodox.org

እንኳን ማጠናቀቅ ሊማይችሉበት የእድሜ ክልል ላይ ሆኖ ከሠርግ በሚገኝ ደስታ በመታለል ለጋብቻ መቸኮል የሠርጉ ደስታ በተወሰኑ ቀናት በሚጠናቀቅበት ጊዜ አደጋው ይከፋልና ራዕይ ያለው ወጣት መሆን ግድ ይላል፡፡ ሌሎች ሰዎች ስላደረጉት ብቻ ሊደረግ የሚችል ነገር የለም፡፡ ሰው የሚኖረው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይደለም፡፡

ወደ ሁለተኛው ሀሳብ ስንመጣ ደግሞ በእጮኛሞች መካከል ከሚፈለገው በላይ የእድሜ መበላለጥ ካለ በተለይም በዕድሜ የምትበልጠው ሴቷ ከሆነች አሁንም ትዳሩ አደጋ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ቀይ መብራት ነው፡፡ በመሰረታዊ ሀሳብ ደረጃ ሴቷ የግድ መብለጥ የለባትም የሚል አስተሳሰብ የለም ዋናው ነገር ክፍተቱ በጣም ሰፊ መሆን የለበትም ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሚፈለገው በላይ የሴቷ እድሜ ከበለጠ ትዳሩ ፈታኝ አዝማሚያ እየያዘ የሚመጣ መሆኑን ነው፡፡ ወንዱ ከአምስት እስከ አስር አመት በእድሜ የሚበልጥ ቢሆን መልካም ነው፡፡ የፈጣሪ ሀሳብ ከሰው ሀሳብ የተለየ ነውና ሁለቱም ወገኖች በነገር ሁሉ ተስማምተው በፍፁም መግባባት ውስጥ የሚገኙ ከሆነ ሴቷ በዕድሜ ስለበለጠች ብቻ ጋብቻው ሊቆም አይችልም፡፡ ሴቷ በእድሜ የምትበልጥ ከሆነ ከሁለትና ከሶስት ዓመት ባይበልጥ ግን የተጠና ይሆናል፡፡ የእድሜ ጉዳይ እንደ አስፈላጊ ነጥብ የተነሳበት ዋናው ምክንያት ልዩነቱ የሚያመጣው የግንዛቤ አለመመጣጠን ትዳሩን እንዳይበጠብጠው ነው፡፡

2. መንፈሳዊና ዓለማዊ እውቀት

እውቀት የአስተሳሰብ አድማስን ያሰፋል በትዳር መካከል በውይይትም ሆነ ያለ ውይይት ሀሳብን ለመረዳት ሁለቱም ያሉበት የእውቀት ደረጃ ተቀራራቢ መሆን አለበት፡፡ አንደኛው ወገን ነገሮችን ሁሉ የሚመለከተው ከመንፈሳዊነት አንፃር በመንፈሳዊ እውቀት ይሆናል ሌላኛው ወገን ደግሞ በዓለማዊ አስተሳሰብ የሚመራ ከሆነ





ጋብቻው ሳይታወቅ ሠፊ ልዩነቶች ይንፀባረቁበታል አንደኛው ወገን በመንፈሳዊ አስተሳሰብ ሌላኛው ወገን በዓለማዊ አስተሳሰብ የሚመራ ከሆነ ጋብቻው ሳይጀመር ይጠናቀቃል፡፡ ሴቷ ከወንዱ በእውቀት መብለጥ የለባትም እርሱ ዲፕሎማ ካለው እርሷ ድግሪ ሊኖራት አይገባም የሚል አስተሳሰብ በማንኛውም መስፈርት ተቀባይነት አያገኝም፡፡ ሆኖም እርሷም ትሁን እርሱ የእውቀት መጠናቸውም ከተራራቀ ለመግባባት ስለሚያስቸግራቸው በትዳር ምርጫ ወቅት ሊታሰብበት የሚገባ አብይ ጉዳይ ነው፡፡ "በአንድ ሀሳብ ተስማሙ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ" ፊል 2:2

የእውቀታቸው መጠን የሚያገናኛቸው ከተለያዩ ወገኖች ጋር ስለሚሆን አስተሳሰባቸውም እንዳዋዋላቸውና እንደ ሥራቸው ፀባይ ነው፡፡ ይህንን ነገር ወደቤት ሲመልሱ ቢያንስ እንኳን በግማሽ ያህል ማግኘት አለባቸው ነገሩ በተቃራኒው ይሆንና አንድ አይነት ቋንቋ እየተነጋገሩ ካልተግባቡ የሚመስላቸውን ወገን ለማግኘት ልቦናቸው ወደ ውጭ ይሸፍታል " አስቀድሞ ነበር መጥኖ መደቆስ ኋላ ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ" የሚለውን የአበው ብሒል በመገንዘብ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው ልዩነት ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን ማወቅ ትልቅ ነገር ነው፡፡

3. አላማ፣ግብና፣አመለካከት

ጋብቻ የደስታ ወይም የስቃይ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎቹ ባላቸው ቅድመ ዝግጅት ላይ የሚወሰን ቢሆንም በዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደታቸው ቀዳሚ ዓላማቸው ልጆቹን ወልዶ በፍቅር መኖር ርግጥ ነው፡፡

የጋብቻም ዋናው ዓላማም ይሔው ነው፡፡ ቢሆንም የዓለማቸው ፍፃሜና ግብ የሚለያይበት አጋጣሚም አይታጣም፡፡ ለምሳሌ፡- አንደኛው ወገን እንደ ታላቅ ደስታ የሚቆጥረው የራሱን ደስታ ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦችንም ሠላም ነውና ይህን ለመፈጸም ደፋ ቀና ሲል ሌላኛው ወገን ደግሞ ቤተሰብ፣ዘመድ ወዘተ.. ራስ ምታቱ ሊሆን ይችላል፡፡ ሃይማኖትን በመከታተል በእግዚአብሔር እርዳታ እስከ መንግስተ

ሰማያት መንግዝ በሚያስብና መጨፈር፣መደነስ፣ሁልጊዜ ሱቆችን መጐብኘት በሚያስደስተው መካከል ትልቅ የልዩነት ተራራ አለ።

በገንዘብ አጠቃቀማቸው ላይም የሚፈጠሩ ነገሮች አሉ ችግረኞችን መርዳት፣ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ማስፈጸሚያ መባእ ማቅረብ የአንዱ ሃሳብ ሲሆን በሌላው ወገን ደግሞ ለበአላት፣ ለልደት፣ለተለያዩ ጉዳዮች የሚወጡ ወጭዎች ላይ ተመስርቶ የሚመጣ ውዝግብ የሚፈጠረው የግለሰቦቹ ዓላማና ግብ ፍጹም የተለያየ ሲሆን ነው። በተጨማሪም የሚከተሉት የፖለቲካ ራዕይ የእያንዳንዳቸው የተለያየ ከሆነ በፍቅር ከመደሰት ይልቅ ጋብቻን ሌላ የጦርነት ሜዳ ማድረግ ነው።

ከሁሉ በፊት ለእኔ ዓላማ ምንድነው? ድልስ ምንድን ነው? የደስታዬ ፍፃሜስ ምንድን ነው? በዚህ ረገድ ከእኔ ጋር ትዳር የሚፈጽመው አካል ያለው ሀሳብ ምን ይመስላል? ብሎ በውይይት ለመረዳዳት መነሳት ያስፈልጋል። ለአንደኛው የሕይወት መንገዱ የሆነለት ለሌላኛው ጭንቀትን የሚፈጥርበት ከሆነ ተቻችሎ ለመኖር ያስቸግራል። ክፍተትን የሚፈጥሩ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አመለካከቶችን በተቻለ መጠን ወደ አንድ አቅጣጫ ማምጣት አማራጭ የሌለው አማራጭ ነው። እርስ በርስ መግባባትና በሀሳብ አንድ መሆን አንዱ በአንዱ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ሕይወቱ ውስጥ ቦታ ማግኘት የጋብቻ ተቀዳሚ ተግባር ነው።





## ምዕራፍ ሦስት

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ሌላው አንገብጋቢ ጥያቄ እኔና እጮኛዬ ብንፈቃቀድ እንኳን እግዚአብሔር ካልፈቀደ ፍፃሜው አያምርምና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ? የሚለው ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሚጠየቅበት ጊዜ አስቀድሞ በሥጋዊ ፍቅር አለመያዝ በጣም አስፈላጊ ነው። በሥጋዊ ፍቅር አስቀድሞ ከታሠሩ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ጸሎት ፈቃዱ ቢሆን እስከመጨረሻው እንዲያዘልቅ ባይፈቅድ ግን ወደፈቀደው እንዲመራ ሳይሆን የወደደውን እንዳያፀድቅለት ነው። በህልም በዕውንም፣ በማታም በጠዋትም ስለወደደው ሰው ስለሚያስብ አንዴ ተይዟልና እግዚአብሔር የፈቀደለት ይመስለዋል። በጸሎቱም ሰዓት የምወዳትን ለእኔ አድርግልኝ እንጂ ፈቃድህ ባይሆን ከኔ አርቃት አንተ የወደድከውን አድርግ የወደድከውን እወደዋለሁ አይልም።

ጥበብን በተሞላ መንፈሳዊ እውቀት የእግዚአበሔር ሀሳብ የሆነውን መርምሮ ማግኘት ታላቅ መታደል ነው። ኧንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጅ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ " ኤፌ.25:27 ሥራን የሚሰራ እግዚአብሔር ነውና ፈቃዱን እንዲያሳውቃቸው በምልጃና በፀሎት እርዳታውን አብዝቶ መሻት ያስፈስጋል " አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ" መዝ 142:10 ሀሳብን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጥሎ በሰው ሰውኛው ደግሞ ፈቃዱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ፈቃዱን ለማወቀ ለትነሳሱ የተለያዩ አቅጣጫዎችን መቃኘት ያስፈልጋል።



www.ethiopianorthodox.org

ለሰው ሁሉ የተሰጠ በረከት ነውና በዚህኛውም ነገር ያለ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ እግዚአብሔር ፈቃዱን ገልጦላቸዋልና ወደ ትዳር እንዳይገቡ የሚያግዳቸው ነገር የለም።

ምን አልባት መካንነት ቢኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ የለበትም ማለት ነው ወይ? ከተባለ መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደፊት የሚሰራው ተአምር ስለሚኖር፣ ቸርነቱን አብዝቶ ለመግለፅ ስለሚፈልግ የእግዚአብሔር አሰራር ከሰው አሰራር ልዩ ስለሆነና የማይመረመር በመሆኑ ባለ ትዳሮችንም የማያከብርበት በሌላ ፀጋ ሊሆን ስለሚችል መካንነት ስለ መጋቢት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። ተጨማሪውን በገጽ109ይመልከቱ

2. በተመስጦ ጊዜ ማረጋገጥ

ጥልቅ የመንፈስ መረጋጋት በመያዝ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መበርታት እያንዳንዱን ነገር በአንክሮ ለመመርመር ጥበብን ያስገኛል። በሕይወት ወስጥ አስፈላጊ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ይበልጥ አስፈላጊ ከሆነ ሱባዔ በመያዝ፣ ከሰው በመለየት ልቦናን ለማዳመጥ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፈቃደ እግዚአብሔርን በሚገባ ለማወቀ የሚያስችል አንዱ መንገድ ነው። እግዚአብሔር ለጥያቄዎቻችሁ ሁሉ መልስ አለው። የማዳን እጅም አላጠረችምና በራስ ማስተዋል ከመደገፍ ይልቅ በልቦናችሁ ውስጥ የሚፈጠረውን ስሜት ከእግዚአብሔር ይሁን ከፈታኙ የምትመረምርበት ጊዜ የተመስጦ ጊዜ ነው።

ዘወትር በልቦና ውስጥ የሚቀመጥ የፍቅር ምልክት የእግዚአበሔርን ፈቃደኝነት የሚጠቁም ነው ብሎ መገመት ትክክል የማይሆንበት አጋጣሚ አለ። እንዳውም የውስጥን ሥሜት ማዳመጥና ያንን ሥሜት ከወዴት ወገን እንደሆነ አለመመርመር ውጤቱን ተቃራኒ ያደርገዋል። ከሁሉም ነገር በላይ አሳሳች የሆነ ነገር ቢኖር በውስጥ የሚፈጠር ፍላጎት መልካም ነው ብሎ በመገመት የእግዚአብሔር ፈቃድ አድርጎ መቀበል ነው። አንዴ በህሊናቸው ተጽፎአልና ሌሎች አማራጮችን ከማየት ይልቅ በራሳቸው ማስተዋል





በመሆን የኑሮን ሸክም በጋራ ለመሸከም የሚያስችል ሁኔታ በሁለቱ መካከል ካለ በቀረው ነገር እየተረዳዱ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለመፈጸም ይችላሉ። በሥራ፣በፀሎት፣በድካም መረዳዳት የሚቻልበት ሁኔታ የሚፈጠር ከሆነ እግዚአብሔር ፈቅዶላታል ማለት ያስችላል። መረዳዳት ማለት ግን እርሷ የግድ ደመወዝ ወይም የወር ገቢ ሊኖራት ይገባል ማለት አይደለም። አንዳንዶች ግን "አዳም ለሔዋን ረዳት ትሁነው እንጂ ሸክም ትሁነው አላለም" ብለው የራሳቸውን አንድምታ ያትታሉ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህ የተለየ ነገር ያስተምረናል።

" እግዚአብሔርም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" ዘፍ 2:18 ከዚህ ገጽ ምንባብ እንደምነገነዘበው መረዳዳት ማለት ጭራሹኑ ገንዘብን እንደማይመለከት ነው የምትመቸው፣ የምታጽናናው፣ የምታዝንለት፣ ከጕኑ ወጥታ ጕኑን የምትሞላ፣ የምትጠግነው፣የምታበረታው ማለት ነው ። "ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳል አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት" ምሳ 19:14። እግዚአብሔር ያዘጋጃት፣ ቤቷን የምታከብር፣ በእጇም የምትሰራ፣ እርሱ የድርሻውን ሲወጣ እርሷም ድካሙን የምትረዳለት፣ ሠላሟንና ፍቅሯን የምትለግሰው እንደምትሆን አስቀድሞ በቅርበታቸው ወቅት ከተረዳው በእውነትም ይህንን ፍቅር እግዚአብሔር አለበት ብሎ ለመናገር የሚያስፈራ ነገር የለም። "ብልህተኛ ሴት ቤትዋን ትሠራለች ሰነፍ ሴት ግን በእጇም ታፈርሰዋለች።" ምሳ 14:1

"ልጆች የእግዚአብሔር ሥጦታ ናቸው።" መዝ 126:3 እግዚአብሔር በረከቱን በልጆች ላይ አድርጐ ወላጆችን ያስደስታል። ሕፃናት ንጹሐን ስለሆኑ ምስጋናቸውን ይፈልጋል በነቢያት ያናገረውን በሆሳዕና ዕለት የፈጸመው ፍጹም የሕፃናት ወዳጅ በመሆኑ ነው። በመዋዕለ ሥጋዌው ህፃናትን ወደርሱ ይቀርቡ ዘንድ የፈቀደላቸው የእግዚአበሔር ክብር መገለጫዎች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ሁለቱ እጮኞች ልጆችን መውለድ እንደሚችሉ አስቀድመው ስለሚያውቁ

ለሰው ሁሉ የተሰጠ በረከት ነውና በዚህኛውም ነገር ያለ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ እግዚአብሔር ፈቃዱን ገልጦላቸዋልና ወደ ትዳር እንዳይገቡ የሚያግዳቸው ነገር የለም።

ምን አልባት መካንነት ቢኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ የለበትም ማለት ነው ወይ? ከተባለ መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደፊት የሚሰራው ተአምር ስለሚኖር፣ ቸርነቱን አብዝቶ ለመግለፅ ስለሚፈልግ የእግዚአብሔር አሰራር ከሰው አሰራር ልዩ ስለሆነና የማይመረመር በመሆኑ ባለ ትዳሮችንም የማያከብርበት በሌላ ፀጋ ሊሆን ስለሚችል መካንነት ስለ መጋበት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። ተጨማሪውን በገጽ109ይመልከቱ

2. በተመሰጠ ጊዜ ማረጋገጥ

ጥልቅ የመንፈስ መረጋጋት በመያዝ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መበርታት እያንዳንዱን ነገር በአንክሮ ለመመርመር ጥበብን ያስገኛል። በሕይወት ወስጥ አስፈላጊ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን ከእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ይበልጥ አስፈላጊ ከሆነ ሱባዔ በመያዝ፣ ከሰው በመለየት ልቦናን ለማዳመጥ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፈቃደ እግዚአብሔርን በሚገባ ለማወቀ የሚያስችል አንዱ መንገድ ነው። እግዚአብሔር .ለጥያቄዎቻችሁ ሁሉ መልስ አለው። የማዳን እጅም አላጠረችምና በራስ ማስተዋል ከመደገፍ ይልቅ በልቦናችሁ ውስጥ የሚፈጠረውን ስሜት ከእግዚአብሔር ይሁን ከፈታኙ የምትመረምርበት ጊዜ የተመሰጠ ጊዜ ነው።

ዘወትር በልቦና ውስጥ የሚቀመጥ የፍቅር ምልክት የእግዚአበሔርን ፈቃደኝነት የሚጠቁም ነው ብሎ መገመት ትክክል የማይሆንበት አጋጣሚ አለ። እንዳውም የውስጥን ሥሜት ማዳመጥና ያንን ሥሜት ከወዴት ወገን እንደሆነ አለመመርመር ውጤቱን ተቃራኒ ያደርገዋል። ከሁሉም ነገር በላይ አሳሳች የሆነ ነገር ቢኖር በውስጥ የሚፈጠር ፍላጐት መልካም ነው ብሎ በመገመት የእግዚአብሔር ፈቃድ አድርጎ መቀበል ነው። እንዴ በህሊናቸው ተጽፎአልና ሌሎች አማራጮችን ከማየት ይልቅ በራሳቸው ማስተዋል





ተደግፎው ልቦናቸውን እልከኛ ያደርጉታል። ሐዋርያውም ይህንን በመረዳት ይመስላል " ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ " ዕብ4፣7 መዝ 94፣8 በማለት አሮጌው አስተሳሰብና የፈሪሳዊነት ጠባይ (እልከኛነት )ከልብ ውስጥ አስወግዶ በአዲስ ልብ /በመንፈሳዊ ልብ/፣ በአዲስ አስተሳሰብ፣ በመመርመር በመንፈሳዊም ይሁን በምድራዊ ሕይወት ሥኬታማ ለመሆን ይቻል ዘንድ ልቦናችሁ ያመነበት ነገር በተሳሳተ ግንዛቤ ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን ርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሰው ያመነበትን ነገር ለማድረግ መክፈል ያለበትን መስዋዕትነት መክፈሉ አይቀሬ ነውና ውጤቱ መልካም ለማይሆን ክፉ የልቦና ሀሳብ በመገዛት ጊዜን፣ ገንዘብን እውቀቱንና ለእናንተ አስፈላጊ ከሆኑት ማንኛውም ነገር አንዱን እንኳን ማጥፋት ሥለሌለባችሁ ነው።

ሴት ወይም ወንድ ያለ አንዳች ችግር ማግኘት ይችላል ቁምነገሩ እግዚአብሔር ያዘጋጃትን ለሚስትነት የምትበቃ ሴት፣ ለባልነት የሚበቃ ወንድ ማግኘት ነው። ሁኔታዎችን በጥልቀት እየመረመራችሁ ከእግዚአብሔር መልስ ለማግኘት በተመስጦና በማስተዋል ስትቆዩ ልትዘነጉት የማይገባ ነገር እግዚአብሔር መልሱን መች እንደሚሰጥ አይታወቅምና መልሱ አጠገባችሁ ቀርቦ ማስተዋል ስለተሳናችሁ ብቻ የእግዚአብሔር መልስ ያልመጣ መሰላችሁ ጊዜያችንን በከንቱ እንዳታጠፉ አይናችሁን መግለጡን ነው።ምክንያቱም እግዚአብሔር መልሱን ከሰጠ በኋላ በአጠገብ አስቀምጦ አይን ጨፍኖ መፈለግ የብዙዎች ችግር ነውና። አይንን በደንብ መግለጥ የግድ ነው። በሌላ በኩል በፊት ለፊታችሁ መልካም ያልሆኑ ነገሮች እየታዩ ከጋብቻ በኋላ ቀስ በቀስ ይስተካከላሉ በማለት የሚያዩትን ነገር ባለመቀበል የሕሊናን ምስክርነት በጉልበታችሁ መግፋት ለአደጋ ያጋልጣል። ሚስት ከእግዚአብሔር የምትሰጥ በረከት እንደሆነች የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ያረጋግጥልናል። ነገር ግን በበረከት ፈንታ መርገምን የምትጠራ ሆና ላለ ሊሻሻሉ የማይችሉ ልዩነቶች እያሉ ነገ ይሻሻላሉ ብሎ መግባት የጌታ ፈቃድ ካለመሆኑም በላይ እንደማይድን በሽታ

የሁልጊዜ ህመም ነው:: አስተዋይ ሚስት ግን በረከት ናት:: "ሚስት ያገኘ በረከት አገኘ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል" ምሳ 18:27

ብዙ ሰዎች የሰው ልብ የማይሳሳት የፍቅር መመዘኛ እንዳለው ያስባሉ:: የያዛቸው ፍቅር እውነተኛ መሆኑንና ያለመሆኑን፣ እግዚአብሔርም በፍቅራቸው ላይ ስላለው ሀሳብ ከልባቸው ማግኘት እንደሚችሉ ርግጠኛ ይሆናሉ:: ይህ የሚወሰነው እንደሰውየው ጥንካሬ በጸሎት እንደመትጋቱ፣ የጌታን ፍቃድ በሚጠይቅበት የሱባኤ ጊዜው ሁሉንም በአግባቡ መመርመር በመቻሉ ነው:: በአሜሪካን ሀገር በ1990 ዎቹ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ዕድሜያቸው ከ20 -25 ዓመት ያሉ ወጣቶች በአማካይ ከ 6 - 10 ጊዜ አፍቅረዋል:: ጥናቱ እንደሚያብራራው ወጣቶቹ ፍቅር በያዛቸው በእያንዳንዱ ጊዜ ትክክለኛ ፍቅር እንደያዛቸው ልባቸው ተቀብሎ እንደነበር መስክረዋል:: አንድ ሰው ስድስት ወይም አስር ጊዜ ካፈቀረ እያደረገ ያለው ከሕፃናት የጭቃ ጨዋታ የሚያንስ ነገር ነው:: እነዚህ ወጣቶች በኋላ ላይ ሆነው ሲያስቡት ፍቅር ይዞናል ያሉበት ወቅት የተሳሳተ እንደነበር ገልጠዋል:: አሁን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ያለው ጓደኞቸው ወደፊት ለትዳር አጋር የሚሆናቸው እንደሆነ ያስባሉ:: ነገር ግን እንዳለፉት ጊዜያት ላይሆን የሚችልበት ምንም ምክንያት የለም:: ይህም ጊዜ ሲያልፍ የአሁኑም ፍቅር ቢሆን እግዚአብሔር ያልፈቀደው ነው የሚሉበት ወራት ሊመጣ ይችላል:: ለዚህም ነው አንዳንዶች የልቦናቸውን ነገር በተሳሳተ አተረጓጐም አዳምጠው የገዛ ልቦናቸውን ተመክተው ትዳር ከመሰረቱ በኋላ ተሳስተው እንደ ነበር የሚናገሩት:: "በገዛ ልቡ የሚታመን ሰው ሰነፍ ነው በጥበብ የሚሄድ ግን ይድናል"ምሳ28:26 :: ልባችሁ እንዳይስታችሁ ጠብቁት:: እውነት የሆነውን ነገር እንደገለጠላችሁ እርግኛ ከሆናችሁ ግን ከልቡ የበለጠ ቅርብ ለሰው የለውም::

3. ነገሮችን በሒደት መመርመር

"ያዕቆብም ስለ ራሔል ሰባት አመት ተገዛ እርሷንም ይወዳት ስለነበር በእርሱ ዘንድ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት" ዘፍ 29:20::





በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሰረተ ፍቅር ሁልጊዜም አያረጅም፣ መቼም አይቀዘቀዝም የተመኘውንም እስከሚያገኝ ድረስ ይታገሳል:: የያዕቆብ ፍቅር የስሜት ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል ጊዜ ባልታገሰ ዘመናቱም እንደ ጥቂት ቀን ባልሆኑለት ነበር:: ፈትኖ ለማወቅ ተፈትኖም ለመውጣት ከሁሉም የተሻለው መንገድ አስፈላጊ የሆኑት ጥናታዊ ውጤቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ ጊዜ መውሰድ ነው:: ማንም ሰው አጭር በሆነ ቅርበት የእርሱን ማንነት፣ የረጅም ጊዜ እቅዱንና ከሚቀርበው ሰው ማግኘት የሚፈለገውን ነገር ሊገልጥ አይችልም :: በቂ ጊዜ ሰጥቶ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው እግዚአብሔርን የሚያከብር መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል:: በዚህ ረጅም ጊዜ በተቻለ መጠን አምላኩን የሚፈራ እንደ ፈቃዱም ለመሔድ የሚሞክር ከሆነ ጌታ የሚያከብሩትን ያከብራልና እግዚአብሔር ያከበረው የትዳር አጋር እንደ ሰጠው ሊያውቅ ይችላል::

ፍቅር የማይገባውን አያደርግም የራሱንም አይፈልግምና ተጨማሪ ጊዜ መውሰድ የያዛችሁን ፍቅር በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን ለመመዘን ያስችላችኋል:: የማይገባውን ዝሙት በመፈፀም የራሱን ፍላጎት ብቻ ለማርካት የሚፈለግ ከሆነ ያፍቅር ከእግዚአብሔር አይደለም:: በተጨማሪም ጊዜን በአግባቡ ተጠቅሞ ነገሮችን መመርመር ከታች ለምናነሳናቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጥልናል:: ዓላማውና ፍላጎቱ ከእኔ ጋር አንድ አይነት ነው? ለእኔ ያለው አመለካከት ሳይቀደር ይዘልቅ ይሆን? የሚያስበው ስለ ስሜቱ ነው? ወይስ ለእኔ ክብር አለው? ክብር ካለውስ ይጠነቀቅልኛል? በቅርባችን ወቅት የማይገባ ነገር እንዳደርግ ገፋፍቶኛል? በእኔ የሚያፍርበት ነገር አለው? ጥሩ ባል ወይም ሚስት መሆን ይችላል? ትችላለች? ለእነዚህ አይነትና ሌሎች ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠው በአንድ ጀምበር አይደለም:: በሒደት ነገሮች ስለሚገለጡ ከትዳር በላይ አስፈላጊ ጉዳይ የለምና በጽሞና መከታተል አስፈላጊ ነው:: በአብዛኛው ሕሊናችሁ ለጥያቄዎቻችሁ አወንታዊ መልስ ከሰጠ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያለ ችኮላ ተገንዝባችኋል ማለት ነው::

ማረፊያ እንዳጣች ወፍ እንዲሁ በሚያከንፍ የፍትወት ፍቅር ላይ ተቀምጦ መንዝ ለአደጋ ይጋብዛል:: በአንድ ቀን በተፈጠረ የስሜት መሳሳብ ብቻ እውነተኛ ፍቅር አይመጣም:: በውጫዊ ውበት መማረክ የእያንዳንዱ ሰው ባህሪ ስለሆነ ቆንጆ መስላ ለታየችው ሁሉ መሸነፍና ወዲያውኑ ስለትዳር ማሰብ እየተለመደ የመጣ እብደት ሆኗል:: መከራው የሚመጣው ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ ከጥሩ ባል መገኘት ያለባችሁን ስታጡ ከጥሩ ሚስት የምትጠብቁትን አክብሮት ስትነፉጉ ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለማወቅ በምትነሳሱበት ጊዜ ሁሉንም ነገር በርጋታ፣ በሒደት፣ በወንጌል በዳበረ አዕምሮ ተረዱት:: እግዚአብሔርም የሚፈልጉትን ስለማያሳፍር ፈቃዱን ከድርጊት መካከል በአንዱ ይገልጣል:: "እናንተ ደግሞ እንዲህ አድርጉ በእነዚህ ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት" ቆላ 3:14





# ምዕራፍ አራት

## የእጮኝነት ጊዜን በመልካም ሁኔታ ማሳለፍ

ሰው በራሱ ጥበብና ማስተዋል የትም አይደርስም:: መዝሙረኛው ዳዊት" እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሰራተኞች በከንቱ ይደክማሉ እግዚአብሔርን ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል" መዝ 126:1 በማለት የተናገረው የሰው ሀሳብና ችሎታ ውስንና ገደብ ያለው መሆኑን ለመግለጥ ነው:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በትዳር የሚሆንን አጋር ከመረጡ በኋላ የሚቀጥለው ጉዞ የእጮኝነት ጊዜ ነው ይህ ጊዜ ከሁሉ የበለጠ ለበጐ አስፈላጊው ጊዜ ነው ለመቀራረጽና ለመግባባት ከዚህ የተሻለ ወቅት የለም::

ማንም ዝም ብሎ ሰውን በትዳር አያስብም የግድ መውደድና ማፍቀር አለበት:: ፍቅሩ የወረትና ስሜታዊነት የሚያይልበት እንዳይሆን ግን በነገር ሁሉ ይጠነቀቃል:: መጠናናት ያስፈልግ ይሆናል:: አጥንቶ መልካም ነገር ባይገጥም ማሸሽ ግን የፍርሀት መንፈስ ነው:: ፍቅር ደግሞ አያስፈራም አምስት አመትም ተጠና አስር አመት ሥጦታ ሁሉ ከላይ ነውና ከላይ ካልተሰጠ በጅምር መቅረቱ አይቀሬ ነው:: ሰውንስ እንዴት ማጥናት ይቻላል? "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ እጅግ ተንኰለኛ ነው ማንስ ያውቀዋል" ኤር 17:9 የተሻለው አማራጭ ለእግዚአብሔር በጸሎት እያሳሳቡ መቀራረጽ ነው:: አንዱ የአንዱ ሰላይ ሆኖ ነገሮችን በትዝብት እየተመለከተ እጮኛዬን እያጠናኋት ነው ማለት ባልት ነው:: ይልቁንም በእያንዳንዱ ስህተትና የማያመሳስሉ ነገሮች ላይ በመተጋገዝ የመፍትሔ ሀሳቦችን እያዳበሩ አንዱን ወደ አንድ ስሜት በማምጣት እየተቀራረቡ ወጥ የሆነ ባህሪን መያዝ መቻል አሸናፊ ክርስቲያንነት ነው:: በቋንቋ ደረጃም ቢሆን ከመጠናናት ይልቅ መቀራረጽ ለመንፈሳዊነት የቀረበ ነው:: ታዲያ በእጮኝነት ወራት ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ማወቅ አስፈላጊ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ሀ. ፍቅርን ንጹህ ማድረግ

ፍቅር በባህሪው ንጹህ ቅዱስ ሩህሩህና ፍጹም ነው። ፍቅር እግዚአብሔር ነው የሁሉ ነገር ማሰሪያ መደምደሚያ ስለሆነ እንዴት ሊቆሸሽ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። በትክክል ፍቅር ንጹህ ነው። ንጹህ ያልሆነ ፍቅር የለም ማለት ግን አይደለም። ሰው ፍቅርን ከሚመሰርትበት የመጀመሪያው ወቅት አንስቶ ትኩረት የሚያደርግበት ዋናው ነገር ከበደል በነጻ ፍቅር እንዴት አንድ መሆን እንደሚችል ነው። የብዙ ወጣቶችን ተሞክሮ ስንመለከት በየጊዜው በወረት ፍቅር መያዝ ምግብ የመብላት ያህል እንኳን አይከብዳቸውም። ይህ አይነት ፍቅር የትም አያደርስምና ህሊናን ከወረተኝነት ማጽዳት ያስፈልጋል።

ከፋ የጎልማሳነት ምኞት ልጓም እንደሌለው ፈረስ ያስጋልባል "ከከፋ የጐልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ" 2ኛጢሞ 2:22 በጎልማሳነት ወቅት የእድሜ ጉዳይ ነውና ለመቆጣጠር የሚያስቸግር ኃይለኛ ወሲባዊ ፍላጐት ይቀሰቀሳል። ክርስቲያን ስሜቱን በጸሎትና በስግደት እግዚአብሔር እንዲገዛለት ይማፀናል እንጂ ከፍቅር ጓደኛው ጋር ወሲብን በመፈጸም ፍቅርን ለማርከስ አይነሳም። ለሁሉም ጊዜ አለው። ሴቶች ካላቸው ሰፊ ማህበራዊ ተሳትፎ አንፃር ፍቅራቸውን በንጽህና ለመያዝ መክፈል ያለባቸውን መስዋዕትነት መዘንጋት የለባቸውም ሁኔታዎች በአንፃራዊነት ሲታዩ ለሴቶች ፈታኝ ናቸው። በተለይ ገንዘብንና ዝናን ተገን አድርገው የሚመጡትን ፈታኞች ለመመለስ ልቦናቸው ይጨነቃል። "አስተውሎ የሚጓዝ ብዙርቀት ይጓዛል" ነውና ለጊዜው መልካም በሚመስል ወረት መሸነፍና መውደቅ በአጠቃላይ የወደፊት ማህበራዊ ግንኙነትን ያጠፋል።

በጣም አጭር ጊዜ የሚቆይም ቢሆን የወረት ፍቅር በአንድ ወጣት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ብዙም ትኩረት ስለማይደረግበትም የሚፈጠረው ችግር እንደ ዱብ እዳ ይሆናል። ወረተኛነት ዓለምን ከመውደድ ይመነጫል "ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንደሆነ አታውቁምን" ያዕ 4:4 እግዚአብሔር





ከጠላ ደግሞ ማንም አይወድም ዓለምና መላዋን መውደድ ደግሞ ጣኦት ማምለክ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ፍቅር ያስረሳል "ከጣኦት ራሳችሁን ጠብቁ" 1ኛ ዮሐ 5:21 አንዲት ወጣት አንድ ታዋቂ ሰው ትወድ ይሆናል ቤቷንም በእርሱ ምስል ከዳር እስከ ዳር ትሞላዋለች ስትተኛም ስትነሳም ስትበላም የግድ ማየት ካስፈለጋት ከዚህ የበለጠ ጣኦት አለ? አስደንጋጩ ነገር ደግሞ መፈጠሯን እንኳን ከማያውቅ ሰው ጋር የወረት ፍቅርን ለብቻ እየቃኙ ማሰላሰል፣ ራሴን አጠፋለሁ እያሉ በራስ ላይ የግድያ ዛቻ እስከ መፈጸም ያደርሳል። ነገሮች ተስፋ እያስቆረጡ ሲመጡ ሀዘኑ ይበረታል "የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታሳዝናለች" ምሳ 13:12

እንደ ጉም የተበተነን ሀሳብ ተስፋ ማድረግ ምን ያህል ጥፋት መፈጸምና ራስን ወደ ማይወጡበት የችግር አረንቋ ውስጥ መክተት መሆኑ ግልጽ ነው። ከቁጥጥር ውጭ ይሆንና ትምህርትን ያስጠላል፣ ብቸኝነትንና ገለልተኝነትን ያስመርጣል ሥነ-አዕምሮ ሊቀውንት ደግሞ ይህ ሁኔታ እየተጠናከረ ከመጣ ትካዜን፣ ጭንቀት፣በሀሳብ መብሰልሰልና ተስፋ መቁረጥ ስለሚያስከትል የምግብ ፍላጐት ይቀንሳል፣ እረፍት ይነሳል ፣አንቅልፍ ያሳጣል፣ የመንፈስ መረጋጋት ያጠፋል ለደረት ውጋት፣ለትንፋሽ መቆራረጥና ለልብ ድካም ህመም መንስኤ ይሆናል። ጌታ ረድቶዋችሁ ከዚህ ችግር ብትላቀቁ የተጓዛችሁበት መንገድ ምን ያህል በጽልነት የተሞላ እንደሆነ ትገነዘባላችሁ።

በተለያዩ ምክንያቶች ልታገኗቸው ከማትችሏቸው ሰዎች ጋር ፍቅር ቢይዛችሁ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለራሳችሁ ማንሳት ይጠበቅባችኋል። ፍቅር ልመሰርት የምችልበት አጋጣሚ አለ? ምን አልባት ያፈቀርኩት ሰው በጣም ዝነኛ ከሆነ ከነጭራሹም አላገኘው ይሆን? የወደድኩት ሰው ለእኔ ፍላጐት አሳይቷል? ለእነዚህ ጥያቄዎች ለራሳችሁ መልስ ስንትሰጡ እንደምኝ አራት ጊዜ እየሳቃችሁ ራሳችሁን ትታዘባላችሁ። ምክንያቱም ሲጮየው ከላይ እነደተገለጠው ፍጹም መኖራችሁንም

አያውቅም:: በሌላ ወገን ያፈቀራችሁት ግለሰብ ለእናንተ የሚያርገው ከመልካም ሰው የሚጠበቅ ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት እንደፈለጋችሁ የሚጠቁም ምልክት ላይሆን ይችላል:: እንደዛ አይነት አስተሳሰብ ከተፈጠረ ደግሞ መልካም መንፈሳዊነትን ሁሉ ወደፆታዊ ግንኙነት መምራት ይሆናል:: ሌላም ነገር እናንሳ ግለሰቡ ፍቅሬን ቢቀበል ምን ላደርግ ተዘጋጅቻለሁ? ወደ ትዳር የሚያደርስ አጋጣሚ አለ? ነው ወይስ ፍቅር ተብሎ ብቻ በሩካቤ ይጠናቀቃል? የትዳር ኃላፊነት ለመውጣት ብርታቱ አለኝ? የእነዚህ ሁሉ መልስ በአብዛኛው ተቃራኒ ከሆነ በእርግጥም በአደጋ ቀጠና ውስጥ እንዳላችሁ መረዳት ያስፈልጋችኋል::

በጽኑ ፍቅር ላይ ያልተመሰረተ ግንኙነት ራስ ወዳድና ለኔ ብቻ የሚል ግትር ነው:: ከስግብግብነቱም የተነሳ የሚፈልገውን ካላገኘ አያርፍም አላስፈላጊ መሆኑን የሚገልጥ አሳማኝ ምክንያት ቢደረደርለት እንኳን ከልብ ውስጥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈንቅሎ ለመውጣት ያስቸግራል:: መፍትሔው የሚያባብሱ ነገሮችን ከአጠገባችሁ ማራቅ ነው::? ፊልሞች፣ዘፈኖች፣የፍቅር ጽሑፎችንና ሌሎቹ ነገሮችን በአጠቃላይ:: ጊዜው እየረዘመ ሲመጣ ደግሞ ሥሜታችሁ እየሰከነና እየቀዘቀዘ ይመጣል:: "እንጨቱ ባለቀ ጊዜ እሳቱ ይጠፋል" ምሳ 26:20 እናም ፍቅርን ንጹህ አድርጐ ከምሬት በመላቀቅ የእጮኝነትን ጊዜ በመልካም ማጠናቀቅና ወደ ተቀደሰወ ትዳር መግባት ስለሚያስፈልግ ያላችሁበትን ሁኔታ የምትኖሩበትን ፍቅር ንጹህ ነው? ወይስ የሚለውን ቀጥሎ ባለው ቅዱስ ጳውሎስ የፍቅር ትንታኔ መዝኑ ቆሮ 13:4-7





| ንጹህ ፍቅር |
| --- |
| ፍጹም ራስ ወዳድ አይደለም:: ለፍቅር መስዋዕትነት ይከፍላል ይንከባከባል ይጸልያል ከራሱ ያስቀድማል |
| ነገሮችን አስተውሎ ጊዜ ወስዶ ከወራት ከዓመታት በኋላ በተረጋጋ ሥሜት ፍቅር ይጀምራል |
| ሊማርከው የሚችለው አጠቃላይ ስብዕናና መንፈሳዊነት እንጂ ከሰውነት ክፍል አንዱ ብቻ አይደለም:: |
| በመልካም ሥነ-ምግባር የታረመ ከቀድሞው የተሻለ ሰው ያደርጋል በነገር ሁሉ ታማኝነትን ያስገኛል |
| ያፈቀረውን ሰው ጉድለት በግልፅ ይመለከታል፣ ከስህተት እንዲታረም ይመክራል፣ አስፈላጊ በሆነው ነገር ሁሉ ከጐኑ ሆኖ ይረዳል:: |
| አለመግባባት ሲያጋጥም በወይይት ይፈታል፣ ለቁጣ አይቸኩልም ይታገሳል፣ ለነገር ፈንታ አይሰጥም ምንም አይነት ክፋት አያውቅም::<br>አይታበይም፣ ይቅርታ ይጠይቃል፣ ይቅርታ ያደርጋል:: |
| ሁሉን በሚያድርግ በእግዚአብሔር ፊት ይጠነቀቃል ከሁሉ ጋርበሠላምለመኖር ተካፍሎለመብላትና በማህበረሰቡ መካከል አርአያ ለመሆን ይጥራል ከሁሉ ጋር ደስ ይለዋል ለምንም ነገር አይወድቅም እስከ ሞት ድረስ የታመነ ነው እስከመጨረሻው ይጸናል:: |

| ሥሜታዊ ፍቅር |
| --- |
| ሁልጊዜ ምን ጥቅም እንደሚያገኝ ያስባል፣ ተጽዕኖ ያበዛል ይጨቃጨቃል፣ መስዋህትነት ከመክፈል ይልቅ በችግር ጊዜ ትቶ ለመሔድ ይቸኩላል:: |
| ቅጽበታዊ በሆነ እይታ ብቻ ስለምንም ነገር ሳያስብ በፍትወት በሚቃጠልበት ጊዜ ፍቅርን ይጀምራል:: |
| የሚያማክረው በቁመት፣በፀጉር፣በጥርስ፣በአጠቃላይ በውጫዊ ገጽታ ነው ዓይኑ ወደ ወስጥ ጠልቆ መመርመር የማይችል እውር ነው:: |
| መላ ቅጥን ያሳጣል ምንም ነገር ማሰብ የማይችልና ከቀድሞው ይልቅ የተበላሸ ያደርጋል:: |
| ማገናዘብ ስለማይችል የወደደው ሰው ፈጹም የማይሳሳት ጉድለት የሌለበት አድርጎ ይቆጥራል ችግር እንዳለ ህሊናው ሲነግረው ማስተዋል ስለማይችል ዝም ማለትን ይመርጣል:: |
| አለመግባባት ዘወትር ያጋጥማል፣ ስድብ፣ ድብድብ፣ ንትርክ ይበዛል:: ወዲያውኑ ወሲባዊ ስሜታቸው ሲቀሰቀስ ለፍትወታቸው ይታረቃሉ :: መታረቃቸውን የሚያረጋግጡት ጥልቅ በሆነ መሳሳምና ሩካቤን በመፈጸም እንጂ ይቅርታ በመጠያየቅ አይደለም:: |
| ከመቀበል ይልቅ መስጠት እንደሚሻል ስለማያውቅ ለመቀበል ብቻ እጅ የተዘረጋ ይሉኝታ የለሽ ነው::<br>ደስታው ለራሱ ብቻ ነው ላፈቀረው እንኳን አይጠነቀቅም ስሜታዊ ነወና ወረቱ ሲለቀው ፈጥኖ ይጠፋል:: |

### ለ. ፍቅርን መንከባከብ

ፍቅር እዚህ ቦታ ወይም በዚህ ጊዜ እጀምራዋለሁኝ ተብሎ "ፎርሙላ" የሚበጅለት ነገር አይደለም:: በሆነ አጋጣሚ በአንዳች ቅጽበት ህሊናህን የሚገዛ አጋጣሚ ሲፈጠር በእያንዳንዱ ልቦና ውስጥ ያልታወቀ አዲስ የደስታ ምልክት ያለው ስሜት ይቀሰቀሳል:: ይህን





ሁኔታ እየደጋገማችሁ ስታስቡት የበለጠ በአዕምሮ ውስጥ ቦታን ስለሚያገኝ የተማረካችሁበት ሰው ከእናንተ ጋር እንዲሆን ትፈልጋላችሁ::በመዋደድ ይጀመርና ሥር እየሰደደ ሲመጣ ፍቅር ይሆናል:: ከእናንተ በጭራሽ እንዳይለይ አጥብቃችሁ ትጥራላችሁ:: መንገድ ላይ፣ መዝናኛ ቦታ፣ ቤተክርስቲያን፣ ወይም ከሆነ አጋጣሚ እንዲህ አይነት ክስተት ሲከሰት በብዛት የሚታየው ስሜት ከላይ የተዘረዘረውን የሚመስል ነው:: እንዲህ አጥብቃችሁ የፈለጋችሁትን ፍቅር ደግሞ ካገኛችሁ በኋላ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ በመንፈግ በጅምር አስቀርታችሁ ቤታችሁ በእጃችሁ እንዳታፈርሱት ብልህ መሆን ያስፈልጋል::

1. <u>ለፍቅር ጓደኛ ክብር መስጠት</u> :- ሰው በተፈጥሮ ክቡር ስለሆነና እግዚአብሔርም ውብና ድንቅ አድርጎ ሥለፈጠረው መከበር ይገባዋል:: መከበርም አለበት:: በተለይ ለወደፊት አብረው ጎጆ ቀልሰው ትዳር መስርተው መኖር ከተሰማው ምን ያህል መከባበር እንደሚገባቸው ብዙ ማብራሪያ አያስፈልግም:: እርሷ ወይም እርሱ ጓደኞቻቸውን ከሰው ጋር ሲያስተዋውቁ ሲያስቡ ትህትናና ክብር በተሞላበት ሁኔታ ማንነታቸውን ሲገልጡላቸው ይገባል:: በባልንጀሮች መካከል ተሰብስበው በሚጨዋወቱበት ጊዜ ለንግግራቸው ዋጋ በመስጠት በጨዋታው መካከል አንዱ ለአንዱ ያለውን ክብር መግለጥ የግድ ይላል:: መቆጣትና መገሰጽ የሚገባቸው ነገር ቢኖር እንኳን ለሁሉም ጊዜ ስላለው በአጠገቤ ያሉት ጓደኞቼ ናቸው በሚል የዋህ አስተሳሰብ በማመራት የፍቅር አጋርን ህሊና ክፉኛ መጉዳት ፍቅርን መሸርሸር ነው:: በጨዋታ መካከል በሚነሱ ቀልዶችና ጨዋታዎች ላይ ተንተርሶ በሰዎች መካከል ትችት መስጠት ጭራሹኑ አስፈላጊ አይደለም:: ከተቻለ ማበረታታት፣ ማድነቅና ፍቅርን መግለጥ ወሳኝ ነው::

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ባህል ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት ስለነበር እንኳን ወሳኔን የመጋራት ቀርቶ ሀሳብ የማቅረብ መብት አልነበራትም:: ዘለቄታዊ ውህደት ለመፍጠር ግን ከዚህ ሰው ሰራሽ ባህል ተላቆ በአዲስ የስልጣኔ እቅጣጫ መጓዝ ያስፈልጋል:: ብዙ

ጊዜ ሴቶች የትዳር ጓደኛቸው የሚሆነው ሰው እንዲረዳቸውና እነርሱም ሀሳብ ማመንጨቴትና ማሳመን የሚችል ህሊና እንዳላቸው እንዲገነዘብ ይፈልጋሉ:: በለገሳቸው ክብር ከእነርሱ ጋር ለመኖር ያለውን ቁርጠኝነትን ጥልቅ ፍቅር ይረዱበታል:: እኔ ብቻ አውቃለሁ አንቺ ምን አገባሽ "ሴት" ብታውቅ በወንድ ያልቅ:: የሚለው ተረት በተረትነቱ በነበር መቅረት አለበት:: በሌላ በኩል በነገሮች መግባባት የማይቻልበት ሁኔታ በሚፈጥርበት ጊዜ ከብዙ ሰዎች የትዳር፣ የኑሮና የፍቅር ተሞክሮ እንደምንረዳው ለፍቅራቸው ህልውና ሲባል ወንዱ የመወሰን ሥልጣን ቢኖረው መልካም ነው:: በዚህ ጊዜ ሴቷ መብቷን እንደተነፈገች በፍጹም መቁጠር የለበትም::

2. ሥጦታ መለዋወጥ:- አፍቃሪ ልብ በየጊዜው ፍቅሩን ማረጋገጥ ይፈልጋል:: እንደሚፈቃቀሩ እርግጠኛ ሆነው እንኳን እወድሻለሁ አፈቅርሀለሁ እያሉ ደጋግመው ደጋግመው ይነጋገራሉ:: ከዚህም አልፈው ልዩ ልዩ ሥጦታዎችን በመለዋወጥና በከበረ ቦታ በማስቀመጥ ፍቅራቸውን ያስታውሱበታል:: እጮኞች የሚኖሩት በተለያየ አካባቢ ከሆነ የሥልክ አገልግሎት እንደአስፈላጊነቱ የማያገኙ ከሆነና በሌላም ምክንያት ርቀት ከተፈጠረ ብቸኛ መጽናኛቸውና ፍቅራቸውን የሚያዩበት መነጽራቸው የሚወዱት ያበረከቱላቸው ሥጦታነው:: በሕይወታቸወ ውስጥም ትልቅ ቦታ አለው::

እልፎ እልፎ የሚስነዘሩ አስተያየቶች አሉ በተለይ ክርስቲያን ሥጦታ መለዋወጥ አይገባውም እስከማለት የሚደረስበት ጊዜም ይስተዋላል:: ይህ ፍጹም ከሀቁ የራቀና ራሱ ሊነካው ያልወደደው ሌሎች እንዲፈጽሙት ማሸከም ነው:: ፍቅር በባህሪው ከሀሳባዊነት ይልቅ በተግባራዊነት ላይ እንደ ሚያተኩር ተደጋግሞ ተገልጧል:: እንኳን የራስ የሆነን ነገር ራስን አስልፈው የሚሰጡበት እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ነው:: ፍቅር እግዚአብሔር ነውና:: በነባ አዕምሮ ሆናችሁ ስታስቡት እንኳን ከፍቅረኛ ከሌላም ወገን የተሰጣችሁን ስጦታ ወደሌላ ወገን ላለማስተላለፍ የምትጠቀሙበት መንገድ የሰው ስጦታ ነው የሚል ሆኖ





ታገኙታላችሁ:: ይህ ማለት እጅግ እፈልገዋለሁ ልሰጠው አልችልም ማለት ነው:: ከእናንተ ሊወስድ የፈለገውም ሰው ልክ የሰው ስጦታ ነው ሲባል ጥያቄውን እዚያው ያቆማል ማንኛውም ሰው ለሰው ስጦታ ይህንን ያህል ክብር የሚኖረን የሰጠን ሰው ለሰውየው ያለው ክብር መግለጫ ስለሆነ ነው:: ከፍቅረኛችሁም የተቀበላችሁት ሥጦታ ሊሰጥ ያለውን ፍቅር ስለሚገልጥ ትወዱታላችሁ:: እዚህ ጋር አንድ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ሥጦታ መልካም ነውና የወርቅና የአልማዝ መሆን አለበት ማለት አይደለም:: የአስር ሺህ ብርም ሆነ የአሥር ብር፣ መኪናም ሆነ የመኪና ስዕል እኩል ፍቅርን የመግለጥ ችሎታ አላቸው:: ፍቅር የሚለካው በቁሳቁስ ሳይሆን አንዱ ለአንዱ ባለው ትክክለኛ የመውደድ መጠን ነው::

3. <u>በሚቻለው ሁሉ መደጋገፍ</u>:- የኑሮን ሸክም ለመሸከም አስቀድሞ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ወደፊት ሊመጣ ያለውን ትዳር በጥሩ መሰረት ላይ ለማቆም በእጮኝነት ጊዜ በሚችሉት ሁሉ እየተረዳዱ የኑሮ መስመርን መቀየስ አንድ እርምጃ ነው:: ሚስት በቤቷ የምትፈልገውን ነፃነት ለማግኘት የምትሰራው ሥራ ቢኖራት ትመርጣለች:: ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ ማህበራዊ ሕይወት ሥለሚሰፋ ሥራን የመስራት አጋጣሚዋ ሊቀንስ ይችላል:: ለዚህ አይነተኛው መፍትሔ በእጮኝነት ጊዜያቸው ቢቻል ሁለቱም የሥራ እድል መፍጠር ነው:: አንድ ጊዜ ሥራ ከተጀመረ ግን ምንም እንኳን ማህበራዊ ሕይወት ቢሰፋ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር ሥራን ማቆም አይታሰብም:: ከትዳር በኋላ ግን ወደ ሥራ ዓለም ለመግባት ከባድ ነው :: ሚስት ሥራ ከሌላት ለሚስትነት የሚያበቃትን መስፈርት አላሟላችም ማለት ግን በፍፁም አይደለም:: በእርግጥ ማድረግ የሚችሉት ነገር ካለ ለትዳራቸው ስምረት የጋራ ጥረታቸውን ሁለቱም በሚሰሩት ስራ ማሳየት ቢችሉ አማራጭ የለውም:: እርሱ የራሱን የትምህርት ደረጃ ከአንድ እርከን ወደሌላው እርከን ለማሳደግ የሚሮጠውን ያህል እሷንም ወደተሻለ ደረጃ እንድትደርስ በሚቻለው ሁሉ ቢረዳት የልብ አፍቃሪነቱንና ታማኝነቱን

ይገልግል፡፡ ምክንያቱም በተለያየ የሥራ መስክ እርሱም ተሳተፊ እርሷ ጥቅሙ የጋራ ነው፡፡ እንዲያውም በመካከል ያለውን የእውቀት፣ የሥራና የአስተሳሰብን ስፋት ስለሚያጠበው በመካከላቸው ልዩነት እንዳይፈጠር ጥሩ የመግባቢያ ቋንቋ ነው፡፡

4. <u>ግልፅ ውይይት ማድረግ፦</u> የበጉ ነገር ሁሉ ጠላት ዲያብሎስ ፍቅርን ሊያደፈርሱ የሚችሉ ብዙ መሰናክሎችን ሊፈጥር ይችላል፡፡ እንዲህ አይነትሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ አጉል እልከ ውስጥ በመግባት እርሱ ካልደወለ አልደውልም፣ እሷ ካልመጣች አልመጣም አይነት የህፃናት ጨዋታ እየተጫወቱ ዓለማቀፋዊ ስህተት መፈፀም የፍቅር ፀር ነው፡፡ ፍቅር አኩራፊ አይደለም፡፡ ይቅር ባይና፣ ሩህሩህና ታጋሽ ነው፡፡ ዓለማውያን ሰዎች ብዙን ጊዜ ፍቅራቸው በጥቅም ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከአንዱ ወገን ካልመጣ ሌላኛው ወገን ምንም ነገር ለማድረግ አይሞክርም፡፡ ሁሉንም ነገር በሂሳብ ስሌት ነው የሚያንቀሳቅሱት ይሔን ስላደረገች አደርጋለሁ ይህንስላላደረገ አላደርገውም የዘወትር የራስ ወዳድነት ጀብዳቸው ነው፡፡

ዛሬ በዓለም ላይ ለዘመናት በደም መፋሰስ ተለያይተው የነበሩ ሀገሮች እንኳን ጦርነትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስወግዱት በጠረጴዛ ዙሪያ በሚያደርጉት ውይይት ነው፡፡ በየጊዜው በችግራችሁ እየተወያያችሁ ለእያንዳንዱ ነገር መፍትሔ መስጠት ከቻላችሁ ፍቅራችሁን እየተንከባከባችሁት ነውና ምንም ነገር ሳይገድባችሁ ፍቅራችሁም ሳይቀዘቅዝ እስከ ዳር መዝለቅ ትችላላችሁ፡፡ ከዚህም አልፎ ያካበታችሁት የውይይት ልምድ ለወደፊት ኑሯችሁ የመረዳዳትና የመደማመጥ መንፈስን ይፈጥራል፡፡ ገመናችሁን ከጣሪያችሁ ስር ሸሽጋችሁ ሕይወታችሁን በብስለት ለመምራት ጥሩ የኑሮ ዘዬ ግልጽነትን የቁመሳ ብስለት የታከለበት ውይይት ነው፡፡ በተጨማሪም እራሳችሁን ከፈተና ለመጠበቅ እብራችሁ በምትጫወቱበትና አልፎ አልፎም በምትዝናኑበት ጊዜ አብራችሁ መሆናችሁ ለምታዩት ነገር ሁሉ እንግዳ እንዳትሆኑና እንዳትማረኩ





ገደብ ያበጅላችኋል፡፡ በዚያ የአብሮ ቆይታችሁ ወቅት መመካከርና ውስጥ ለውስጥ መናበብ ትችላላችሁ፡፡

ሐ. በተገቢ ጊዜ ጋብቻን መፈፀም

ለምኞቱ ገደብ የሌለው ሰው በሕይወቱ ለአንድ ጊዜ እንኳን ጣፋጭ የሆነን ደስታ አያገኝም ምክንያቱም ምኞት መቼም ይሁን መች እዚህ ድረስ ይበቃኛል እስካልተባለ ድረስ በራሱ ገደብ አይኖረውም፡፡ የእጮኝነት ጊዜ በአግባቡ እንዳይፈፀም ከሚያደርጉ አብይ ነጥቦች አንዱ የጊዜው መርዘም ነው፡፡ ቤት ሳልሰራ፣ መኪና ሳልገዛ፣ ደሞዜ ከፍ ሳይል፣ በሚሉት ምክንያቶች ጊዜው እየተጉተተ ሲመጣ አላስፈላጊ የሆነ ሕይወትን ሊያበላሽ የሚችል አደጋ ይፈጠራል፡፡ በእርግጥ ሰው እንደየስሜቱና እንደየፍላጎቱ የተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ የግድ አስፈላጊና ሊሟሉ የሚገባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መዘንጋት የሌለባቸው ሌሎች ነጥቦችም አሉ፡፡

1. በአለንበት የሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ የምንፈልገውን ነገር በሙሉ በአንድ ጊዜ ማግኘት አንችልም፡፡
2. ለሕይወት አስፈላጊ የሚሆነው ነገር ከተገኘ ተጨማሪ የቅንጦት ፍላጎቶችን ቀስ ብሎ ማሟላት ይቻላል፡፡
3. ጊዜው ከሚፈለገው በላይ ከረዘመ እጮኝነት በጋብቻ የማይጠናቀቅበት አጋጣሚ ይፈጠራል ፡፡
4. እድሜ እየገፋ ከመጣ ልጆች መወለድ ባለባቸው ጊዜ አይወለዱም ፡፡
5. በጣም ከተዳከሙ በኋላ ወደ ትዳር መግባት የሚፈለገውን ያህል በትዳርና በፍቅር ደስተኛ መሆን የማይቻልበት አጋጣሚ ይኖራል

በኢኮኖሚ፣በአካል ብቃት፣ በአዕምሮ ብስለት፣ በመንፈሳዊ እውቀት የሚፈልግበት ደረጃ ሳይደርስ ማንም ወደ ጋብቻ እንዲገባ አይመከርም፡፡ ኑሮውን ማሸነፍ የሚችልበት አቅም እያለው እንዲሁ የሚቀመጥ ከሆነ ግን የመቀራረባቸው መጠን አላስፈላጊ ወደሆነ ጾታዊ ግንኙነት ይመራቸውና አሁን በብዛት እንደሚታየው የ10 ዓመት

ልጃቸውን ሻማ ያዥ አድርጉ ወደ ሚሞሸሩበት ፋሽን ማዝገም ይመጣል። ክርስቲያን እግዚአብሔር ስለሰጠው ነገር እያመሰገነ ስለጐደለው ነገር እየጸለየ ሁሉንም ከእግዚአብሔር እንደሚቀበል በማወቅ ነገሮችን በጊዜያቸው ማከናወን ይጠበቅበታል።

መ. ከጋብቻ በፊት ከሚፈጸም ሩካቤ ራስን መጠበቅ

በእርግጠኝነት አንድ ነገር በድፍረት መናገር ይቻላል። ከጋብቻ በፊት ሩካቤን መፈጸም ማለት የሁሉ ነገር የመጀመሪያው መጨረሻ ላይ መድረስ መሆኑን። ወጣቶች ወሲብ መፈጸም የሚችሉ መሆናቸውንና፣ በጾታዊ ክንውኖቻቸው ላይ ምንም አይነትጉድለት እንደሌለባቸው ለማረጋገጥ በፍጥነት ወደ ሩካቤ ይገባሉ በሃይማኖታዊ እይታም ይሁን በሳይንሳዊ ምርምር ምንም ድጋፍ ያላገኘው በሩካቤ መጣጣምና አለመጣጣምን መፈተሽ የትዳር ቁልፍ ነገር እንደሆነ ስለሚታሰብ ወደ ቅድመ ጋብቻ ወሲብ ያመራሉ። በሩካቤ ለመስማማት ትክክለኛው አማራጭ ከጋብቻ በፊት ሩካቤ መፈጸም ሳይሆን ከጋብቻ በኋላ በሚኖረው ሩካቤ ወቅት ራስ ወዳድ አለመሆን ነው።

ከቁጥጥር ውጭ የሚሆን ፍጹም ለመግራት የሚያስቸግር ፍትወት በሚያይልበት የወጣትነት ዕድሜ ላይ የጓደኞች ተጽዕኖ ተጨምሮበት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ይመራል። ጓደኞቻቸው ከጋብቻ በፊት ሩካቤን የሚፈጸሙት በጣም ስለሚዋደዱና ስለሚተማመኑ ይመስላቸዋል። ሰው በባህሪው መወደድንና መፈቀርን ስለሚፈልግ ሩካቤ በመፈጸም እንደ ጓደኞቻቸው መፈቀራቸውን በአይናቸው ለማየት ወደ ቡድን ኃጢያት ይቀላቀላሉ። ከሌሎች ሰዎች የመለየትና ራስን ነፃ የማውጣት ብቃታቸው አስተማማኝ ስለማይሆን ወንድነታቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው የተመከሩትን የጅል ምክር በመተግበር ሞኝነቱን ይያያዙታል።

በቅርብ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በወጣትነት የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ወሲብ አይፈጽሙም ብሎ መገመት እጅግ እየከበደ መጥቷል። ከአስር አመት በፊት ከአስር ወጣት ወንዶች ስምንቱ ከአስር ወጣት ሴቶች ሰባቱ ወሲብ ይፈጽሙ





ነበር። ከአስር አመት በኋላ ግን የወንዶቹ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት ከስምንት ወደ 9.9 ሲያድግ የሴቶች ደግሞ ወደ 9.5 አሻቅቧል። ክርስትያን የሆኑ ሁሉ ከዝሙት ደቦ የሚሸሹበት በማምለጥም የሚያሸንፍበት የሚያስፈራ ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሰወ ሁሉ ከዝሙት ርቆ ተቀድሶ እንዲኖር ነው።" እኔ ቅዱስነኝ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" በእርግጥ እንደ እግዚአብሔር ማንም ቅዱስ የለም ይሁን እንጂ ሰው በሚችለው መጠን የመልካም ሥነ ምግባር ባለቤት ከሆነ እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር እየፈጸመ ነው። "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ" ነውና ከዝሙት እንድትርቁ" 1ኛ ተሰ 4:3 ሐዋርው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በፃፈው መልዕክት ላይም ዝሙት አስነዋሪ ኃጢያት እንደሆነ በመግለጥ ሰማንኛውም ክርስቲያን ከአምላኩ ጋር እንዳይለያይ አጥብቆ ሊጸየፈው እንደሚገባ ያብራራል "ሥጋ ለጌታ እንጂ ለዝሙት አይደለም" 1ኛ ቆሮ 6:13 "እንደ ሥጋ ፈቃድ እንኖር ዘንድ የሥጋ አይደለንም እንደ ሥጋ ፈቃድ ብንኖር እንሞታለን " ሮሜ 8:12 በማለት በዝሙት ምክንያት የሚመጣ የነፍስና የሥጋ ቅጣት እንዳለም ጨምሮ ያስገነዝባል።

1. በሽታ

በዚህ ምድር ላይ ምንም ዋጋ የሌለው ነገር የለም ጽድቅም ዋጋ አለው ኃጢአትም ዋጋ አለው። ለጽድቅ ከእግዚአብሔር የዘለዓለም ሕይወት ሲሆን የኃጢአት ደመወዝ ደግሞ ሞት ነው። ዕለት ዕለት ወሲብን መደበኛ ሥራቸው አድርገው የሚኖሩ ሰዎች በየጊዜው ይህንን በማድረጋቸው እግዚአብሔር ስለታገሳቸው ምንም ነገር በእነርሱ ላይ የማይደርስባቸው ይመስላቸዋል። እንኳን የጥፋተኛነት ስሜት ሊሰማቸው ቀርቶ በዝሙት መርከሱን ቋሚ የደስታ ምንጭ አድርገው ይቆጥሩታል። እግዚአብሔርም ውብና ድንቅ አድርጐ የፈጠራቸው መረን ለመሆን እንደሆነ ያስባሉ። በዚህ ምክንያት ግና ሳይቀጡ አይቀሩም። በዝሙት ምክንያት የመጣውን በሽታ ለማቆም ባልተቻለባት ባሁኑ ጊዜ ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

ከተለያዩ የአባላዘር በሽታዎችና ብኤድስ መያዝ ማለት የሕይወት ሰንኳላ ክፍል ወይም የሞት ዋዜማ ነው:: በቅድመ ጋብቻ ሩካቤ ወቅት በዚህ ችግር የተጠቃችን ሴት በየትኛውም ደረጃ ቢያፈቅራት ወደፊት የትዳር አጋሩ ያደርጋታል ብሎ ማሰብ አይቻልም:: የአባላዘር በሽታ በጤንነቷ ላይ የሚያስከትለው ጣር ብዙ ነው::

1. መካን ሊያደርጋት ይችላል
2. ለተራክቦ ዝግጁ እንዳትሆን ተጽዕኖ ይፈጥራል
3. በመራቢያ አካሏ ላይ የሚፈጥረው ህመም በተራክቦ ጊዜ ስቃይን ስለሚጨምርባትና የደም መፍሰስ ችግር ስለሚኖር በትዳር ተወስና ለመኖር ያስቸግራታል::
4. ፍቅርን መንከባከብ የሚያስችል ሕሊና አይኖራትም በትዳር ውስጥ የደባልነት ሕይወት ትገፋለች::
5. ኤድስ ከሆነ ደግሞ ይገድላል:: እነዚህ ነገሮች ወንዶችንም በቀጥታ ይመለከታሉ::

አንድ ጊዜ ብቻ የሚኖሩበትን ሕይወት በአግባቡ መኖር ያስፈልጋል:: 20 ዓመትም ይሁን 30 ዓመት በሚገባ ከተኖረበት በቂ ነው:: ዛሬ በችኩልነት የሚገባበት የፍትወት መንገድ በመንግስተ ሰማያት ብቻ ሳይሆን በዚህም ምድር ከመኖር ይከለክለናል:: እግዚአብሔር ከፈቀደ ግን ሁሉም ነገር ይገኛል ይደርሳል:: መሬት ላይ ሆናችሁ አውሮፕላን ሲበር ስትመለከቱት እጅግ በጣም ትንሽ ይመስላል:: አውሮፕላኑ ሲያርፍ ግን ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ትገነዘባላችሁ:: ከጋብቻ በፊት ሩካቤን መፈጸም ማለት እንዲሁ ነው:: በርቀት ስታዩት ሲያጓጓችሁ የነበረውን ነገር ታገሳችሁ ወደ ትዳር ብትደርሱ አውሮፕላኑ ካረፈ በኋላ ትልቅ መሆኑን እንዳወቃችሁ ከዝሙት በመሸሻችሁ ምክንያት ከጋብቻችሁ የምትቀበሉት በረከት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ታውቃላችሁ:: እንደዚያማ ካልሆነ መጀመሪያ ሁሉን ነገር ከፈጸማችሁ ከትዳራችሁ ምን ትጠብቁ?

ትውልድ እየተቀሰፈ ወገን እያለቀ ባለበት በዚህ ዘመን ዝሙትን እያበረታቱ ኤድስን ማቆም ቀልድ ነው:: በላስቲክ /በኮንዶም/





እያመነዘራችሁ ራሳችሁን ጠብቁ ሕይወት ላስቲክ ነው የሁልጊዜ የመገናኛ ብዙሀን ወሬ ሆኖዋል:: ሕይወት ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እውነትም ሕይወትም እርሱ ነው:: አንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ በንጽጽር እንመልከት የእስራኤል ንጉስ የነበረው ኦዝያን ሳይገባው በድፍረት የእግዚአብሔር ቤተመቅደስን ለማጠን ተነሳ እግዚአብሔርም ድፍረቱን አልወደደለትምና በለምጽ ቀጣው እስራኤል ደግሞ በባህላቸው በለምጽ የተመታ ኃጢያተኛ እንኳን ንጉሳቸው ሊሆን በመንገዳቸው ሊያዩት አይፈልጉም:: ለምጹን ለመሸፈን የሚደርስበትን ነቀፋ ለማትረፍ ብሎ በለምጽ የተነደፈ ግንባሩን በጨርቅ ጠቀለለው የኃጢያት ምልክት የሆነው ለምጽ ግን በጨርቁ ላይ ወጣ:: የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንጂ በእግዚአብሔር ላይ ብልጣ ብልጥ መሆን አይደለም:: እንኳን በአንድ ላስቲክ በአስር ላስቲክ ቢጠቀለል ቀሳፊው ላስቲኩን ማለፉ አይቀርም:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ግን በስህተት ቢወድቅም እንኳን አምላኩ ሊራራለት የታመነ ነው:: ከእግዚአበሔር ጋር ያለውን ውጊያ ማንም አይችለውም:: 2ኛ ዜና 26:16-23

2. ሰላምን ማጣት

ወሲባዊ ፍላጐት አቅልን ይነሳል፣ እስከትፈጽመው ድረስ እየወተወተ ያስገድዳል ሰላምንም ይነሳል:: ከፈጸሙት በኋላ ዘለቄታዊ ሰላም የሚሰጥ ቢሆን ክፉ ነገር ባልሆነ ነበር:: ይልቁንም ነገሩ ይገለበጥና ካደረጋችሁት በኋላ የወንጀለኝነት ስሜት እየተሰማችሁ ላታገኙት ሰላማችሁን ታጣላችሁ:: አንድ ጊዜ አላስፈላጊ ወሲብ መፈጸም ማለት እጅግ በጣም ብዙ ነገር ማጣት ማለት ነው::ጥበበኛው ሰሎሞን መጨረሻዋ ሞት የሆነ የዝሙትን መንገድ መጠንቀቅ እንዲገባ ያሳስባል "ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባል አፍዋም ከቂቤ የለሰለሰ ነው ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የመረረ ነው ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍ የተሳለ ነው እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ አረማመድዋም ወደ ሲኦል ነው የቀና የሕይወት መንገድ አታገኝም

በአካሄድዋ የተቅበዘበዘች ናት የሚታወቅም አይደለም...... በመጨረሻም ሥጋና ሰውነትህ በጠፉ ጊዜ ታለቅሳለህ" ምሳ 5:3-11

በሥነ ምግባር የታነጸ ክርስቲያን ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ ለራሱ ያለው ትክክለኛ ግምትና ለራሱ የሚሰጠው ክብር ነው:: ለራሱ ክብር የሌለው ለማንም ክብር አይኖረውም:: ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ሩካቤ ሰው ለራሱ ያለውን ክብር እንዲቀንስ ነጭናጫና ስሜት የለሽ እንዲሆን ያስገድደዋል:: ሁሉም ነገር እንደጠበቀው ስለማይሆን ለምን አደረኩት? እያለ ቀድሞ ማስብ ያለበትን ነገር እንደ ተራ ነገር አሳልፎ በመጨረሻ በሀሳብ ይብሰከሰካል:: ድርጊቱ ምን ያህል ከባድ ኃጢአት እንደሆነ ሲገነዘብ ደግሞ በሌሊትም በቀንም ሰላሙን ያጣል:: አንድ እግርኳስ ተጫዋች ምንም ሳይሰራ ዘጠና ደቂቃውን ቢፈጽምና በባከነ ሰዓት ያገኘውን ፍጹም ቅጣት ምት ባይጠቀምበት በኋላ ስለሁኔታው ሲያስብ የሚሰማው ስሜት ራስህን አጥፋ የሚል ሰላም የሚነሳ ሊሆን ይችላል:: ከጋብቻ በፊት ዝሙትን የሚያደርግ ሰው የእግር ኳስ ተጫዋቹ የቡዱኑን የወደፊት ጉዞ እንደአጠፋ ሁሉ የራሱን ህይወት ያጠፋል ከዚያ በኋላ ለመመለስ ቢፈልግ እንኳን የባከነውም ሰዓት አልቋል::

ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸው ከተለያዩ ሰዎች ጋር በሰፊው ይቆራኛሉ ተሰብስበው እየጠጡ መጨፈርን ያዘወትራሉ ደስታቸውን ፍጹም ለማድርግ አብረዋቸው የሴት ጓደኞቻቸው እንዲኖሩ ይፈልጋሉ:: ይህ ሁኔታ በዝሙት የሚጠድቁበትን ዕድል ሰፊ ያደርገዋል:: ካሉበት የስመመን ዓለም ሲባንኑ የጥፋተኛነት ስሜት ይወቅሳቸዋል:: ከህሊና ወቀሳ ለማምለጥ አንዱ አንዱን ይወነጅላል ወንዱ ለምን እንዲህ አይነት ነገር እንዳላደረግ አልከለከልሽኝም ይላታል:: በዚህ ጊዜ እርሷ ደግሞ ማድረግ የሌለባትን ነገር በማድረጓ ክብሯን እንዳጣችና የርካሽ ስሜቷ ማርኪያ ትሆን ዘንድ እንደ እቃ የተቆጠረች ይመስላታል:: ሁኔታውን ባስታወሰችም ቁጥር ሰላሟ ይበጠበጣል:: በእንዲህ አይነት ተጽዕኖ ውስጥ የወደቀ ሰው የራስ መተማመኑን ስለሚያጣ የሕይወት ትርጉም ይጠፋበታል::





3. የሞራል መላሸቅ

ቢያስፈልግ ሕይወት መስዋዕት ማድረግ ይቻላል:: ሞራልን ግን ስለምንም ነገር አሳልፎ መስጠት አያስፈልግም:: ከጋብቻ በፊት ጾታዊ ግንኙነት የፈጸሙ ወጣቶች ከፈጸሙ በኋላ በግንኙነቱ ጊዜ የነበረው ሁኔታ ያሳፍራቸዋል፣ እርስ በራሳቸው አንደኛው ለአንደኛው ያለው አመለካከት ይለወጣል፣ እንደ ጽጌረዳ ተውባ የታየችውን ቆንጆ ለማየት እንኳን ይጠላታል፣ ተራና ምናምንቴ ትሆንበታለች፣ ከዚያ በኋላ እንደማታስፈልገው ይወስንና እንባዋን እያዘራች ብትማፀነው እንኳን ነውሯን ሊሸሽግላት ፈቃደኛ ሳይሆን ተረማምዶባት ያልፋል:: ያቀራርበናል ብለው ያሰቡት ነገር በተቃራኒው ትልቅ የልዩነት ገደል ይፈጥርባቸዋል:: ልቦናቸው በበቀል ስለሚነቅዝ ክፍዎች ይሆናሉ:: አንዱ አንዱን እስኪያጠፋው ድረስ እረፍት ያጣል ከዚያ በኋላ ማንንም የሚያምን ልብ ስለሚያጡ ወደፊት ለማድረግ በሚፈልጉት ኑሮ ላይ ሁሉ ተጠራጣሪዎች ይሆናሉ::

አምኖን ትዕማርን ወደደ እስኪታመም ድረስም ፈጽሞ አፈቀራት ወሲባዊ ግንኙነት ከፈጸመ በኋላ ግን በፊት ከወደዳት ወድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል እንደ በለጠ በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ እናገኘዋለን 2ኛ ሳሙ 13:15:: በቁም ነገር ኑሮንም እየተረዳዱ ለመግፋት የሚያስቡ ሰዎች ፈጥነው ወደ ወሲባዊ ግንኙነት አያመሩም:: አንዲት ወጣት ለወሲባዊ ግንኙነት በየጊዜው የምትጠየቅ ከሆነች አብሯት ያለው ሰው ፍጹም የትዳር አላማ የሌለው እርሷን የትዳር መዳረሻ ሊያደረጋት የፈለገ እንደሆነ ለማሰብ ከእንቅልፍዋ መነሳት አለባት:: ሊያገቡት እንደሚችል እየማለ እየተገዘተ ቃል ቢገባላት እንኳን በፍጹም ማድረግ የለባትም:: ተፈላጊነቷ የሚጨምረው ሩካቤ በማድረጓ ሳይሆን ራሷን እንደተከበረ ንጉስ ቆጥራ ሞራሏም እንዳይወድቅ ስትጠነቀቅ ነው:: ምን አልባት እንደ አምኖን ቢታመም እንኳን የሚድነው ጋብቻን በመፈጸም እንጂ ሩካቤ በመፈጸም ስላልሆነ መስዋዕትነት ሊከፈልለት የሚገባ ጉዳይ አይደለም:: ለሌላው መዳን ሲታሰብ ሌላኛው መሞት የለበትም:: ፍቅር በምንም መመዘኛ በወሲብ አይገለጥም:: ሩካቤን ከጋብቻ በፊት

መፈጸም መመለስ በማይቻልበት ሁኔታ የሃይማኖትን የባህልንና የሰብአዊነትን ህግ ጥሶ ህሊናን /ሞራልን/ አጥቶ እንደ እንስሳመሆን ነው::

4. አለመተማመን

ቅንአት አጥንት የሚያነቅዝ ክፉ ነገር ነው ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ጾታዊ ግንኙነት ደግሞ በቀጥታ ወደ ቅንአት ማምራቱ አይቀርም:: "ፍቅር እንደሞት የበረቷችናት ቅንአትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናት" መ.መ.ዘሰ 8:6 ያንን ሁሉ ነገር ፍቅር በሚመስል ስሜት ከጨረሱ በኋላ ተከትሎ የሚመጣው መዘዝ ሰው መሆንን እስከ መጥላት የሚያደርስ አለመተማመን ነው:: ሲጀምሩ በተዋቡ ቃላት፣ ብዙ ሥጦታዎችን ማዥጐድጐድ እንኳን ሊፈጽሙ ሊታሰቡ የማይችሉ ቃል ኪዳኖችን በመግባባት ሩካቤን ይፈጽማሉ:: ከጋብቻ በፊት ወሲብ አስፈላጊ ነው ብለው የተቀበሉት ያለምንም ቅድመ ዝግጅት ስለነበር በዚህ ክፉ ድርጊታቸው እዚያ እየነወሩ እንዳይቆዩ እንኳን አለመተማመኑ ይቀጥላል::

ከእኔ ጋር ሩካቤን ከፈፀመች/ከፈጸመ/ ከሌሎች ጋር እንደማትፈጽም ርግጠኛ አይደለሁም፣ ከእኔ ጋር ያደረገውን ነገር ከሌሎች ጋር ሳያደርግ የሚችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም ይላሉ ሩካቤው በፍቅር የበለጠ ሊያዋህዳቸው ቀርቶ እንደ ቀድሞው መኖር እንኳን አያስችላቸውም:: አንዱ አንዱን እየተጠራጠረ በሚያደርገው ነገር ሁሉ በቅንአት እየተብሰለሰለ ሩካቤን ከመፈጸማቸው በፊት የነበረው መከባበርና መተማመን በአንድ ጊዜ ፍርስርሱ ይወጣል::

5. እርግዝና

እንደኛ ሀገር አይነት ባህልና ኢኮኖሚ ባለው ሕብረተሰብ መካከል ሆኖ ከጋብቻ በፊት ማርገዝ በማንኛውም መልኩ ምላሹ መጥፎ ነው:: በወጣትነታቸው ጊዜ ልጅ መውለድን ፈልገው የሚያረግዙ አይኖሩም:: ምን አልባት ከእነርሱ ጋር ያለው ሰው አብሮዋቸው ሊኖር የሚችለው ሲወልዱ ብቻ ከመሰላቸውና በፍቅር ሳይሆን በልጅ ሊያስሩ ከፈለጉ ይህን ዕቅዳቸውን ለማሳካት ሲሉ ያረግዛሉ:: በዚህም ቢሆን ታዲያ





ውጤታማ የሚሆኑት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው:: ከጋብቻ በፊት እርግዝና ምንም ጥቅም የሌለው መቶ ፐርሰንት ኪሳራና የማይችሉትን ግፊት በራሳቸው ላይ መሰብሰብ ነው::ሴት ወጣቶች ከጋብቻ በፊት ሩካቤ በማድረግ ሳረግዝ እችላለሁ ብለው እንዳያስቡ የሚያደርጋቸው ነገር በአካባቢያቸው የተለያዩ ወጣቶች ከሚደረጉት ነገር ተነስተው በግምታዊ እውቀት መመራታቸው ነው:: እንዲህ ያስባሉ:-

1. አንዳንድ ጓደኞቻቸው ሩካቤ ሥጋ ፈጸመው እንኳን እንዳላረገዙ ሲያስተውሉ እነርሱም እንደማያረግዙ ይገምታሉ:: ለምን እነዚያ እንዳላረገዙ እንኳን ጠንቅቀው አይረዱም::
2. ራሳቸውን ከሌሎች በመለየት እርግዝና በእነርሱ ላይ የማይፈጠር ነገርም አድርገው የሚገምቱም አሉ::ሩካቤን እያዘወተሩ ሳያረግዙ ብዙ ጊዜ ስለቆዩ::
3. ወሲብን አልፎ አልፎ መፈጸም ለእርግዝና አደጋ የሚያጋልጥ ነገር እንደሌለው ያስባሉ::
4. በአንድ ጊዜ ሩካቤ እርግዝና አይመጣም የሚል የተሳሳተ እምነት ያላቸውም አሉ::

ከላይ የዘረዘርናቸው ሐሳቦች ሁሉ ካለመብሰል የሚመጡና በወደፊት ሕይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥማቸውን አደጋ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ያጋጠማቸውን ያህል ከባድ ይሆናል ብለው ስለማይጠብቁ ነው:: እውነታው ግን ከጋብቻ በፊት ማርገዝ ማለት የራስን እድገት እንደካሮት ወደ ታች እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው:: በማህበራዊ ሕይወት ላይ ከሚያጋጥሙት ቀውሶች የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው::

1. በቤተሰብ ላይ ተጨማሪ ሸክም ስለሚሆን ወላጅ ይህን አላስፈላጊ የሆነ ርግዝና አይቀበልም ሊቀበል ቢፈልግ እንኳን የኑሮው ደረጃ አይፈቅድለትም::
2. ምን አልባት ወላጆች ያሉበት የኑሮ ደረጃ ከሚያስፈልገው በላይ የተንደላቀቀ ቢሆንም ክብራቸውን ለመጠበቅ ሲሉ "ዲቃላ" ልጅ የማሳደግ ሞራል አይኖራቸውም::

3. የ ዲታላ እናት የሚለው ተቀጽላ አንገትን ከማስደፋቱም በላይ በሕብረተሰቡ ወስጥ በጣም የተናቀ ቦታ ከሚመደቡት ወገኖች ተርታ ያስቆጥራታል::
4. ከወለደች በኋላ ማግባት አትችል ይሆናል:: የወለደችለት ጥሩ ሰው ከሆነ ምን አልባት ገንዘብ ሊረዳት ይችላል እንጂ አሁን ዕለት ዕለት በሚታየው ሁኔታ ግን ወደትዳር ሲገቡ አይስተዋልም:: ሌላ ሰው ማግባት ደግሞ ከወለዱ በኋላ እንኳን ለሴት ለወንድም አስቸጋሪ ነው::
5. አንዱን ልጅ ለማሳደግ ሲባል ሌላ ተጨማሪ ልጅ በመውለድ በዚያው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በማይመለሱበት የተበላሸ የኑሮ መስመር መንገዝ ይመጣል::
6. የሕፃናቱን ሕይወት መጠበቅና መንከባከብ ያስቸግራል::
7. የወደፊት ዓላማ፣ ትምህርት፣ ኑሮንና ሌላውንም ነገር ያበላሻል::
8. ወደ ማይፈለጉት ጋብቻ ልጆቸውን ለማሳደግ ብቻ ሲሉ ይገባሉ::
9. እርግዝናው የተፈጸመው በጣም በወጣትነት ከሆነ በወሊድ ሰዓት አስጨናቂ ምጥና ለሞት የሚያጋልጥ አደጋ ይፈጥራል:: ቢወልዱ እንኳን ተቶት የሚሄደው በሽታ አደገኛ ደዌ ነው::
10. ጽንስን ማስወረድ ያስከትላል /ይህንን በገጽ102 / ይመልከቱ::
11. እርግዝናውን ለመከላከል ተብሎ የምትጠቀመው መድኃኒት የማኅፀን ካንሰርና መካንነትን ሊያመጣ ይችላል::

ሠ. ከጋብቻ በፊት ወሲብን ላለመፈጸም ምን ላድርግ?

አመንዝራነት ታላቅ ክህደት ነው:: በዓለም እጅግ የተከበሩና የተወደዱ ባለስልጣናትና ታዋቂ ሰዎችን የቅሌት ሸማ ያከናነበ በቁማቸው የገነዘ አሰጸያፊ ነው:: ከጋብቻ በፊት በነበራቸው ሕይወት ዝሙት አንዱ የኑሮዋቸው ክፍል ያደረጉ ሰዎች ይሔው የቅሌት አባዜያቸው እያገረሸ ስለሚያስቸግራቸው እርያ ወደ ርኩሰቱ ውሻም





ወደ ትፋቱ እንዲመለስ ይመለሱበታል:: የሚያስፈልጋቸው ሲኖር እያንዳንዱን ነገር ቤታቸው ማግኘት ሲችሉ አመል /ሱስ/ ነውና ሊቋቋሙት አይችሉም:: ለማቆምም አይፈልጉም:: ሥር ይሰድና ትደራቸውን ከበጠበጠ በኋላ ደግሞ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ ነው የሚሆነው:: ስለዚህ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸምን ወሲብ ለማቆም በተቻለ መጠን መትጋት ተገቢ ነው::

1. ከእግዚአብሔር ጋር መሆን

አምላክ ለሰው ሁሉ ካለው ፍቅር የተነሳ ከበደል ርቀው በጽድቅና በበረከት እንዲኖሩ የዘወትር ፍቃዱ ነው:: እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ በእግዚአበሔር ሀሳብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር የሚቻለው ህጉን ለመንገዳችሁ ብርሃን ስታደርጉና በጎውን ነገር ለመፈጸም ስትጣጣሩ ነው:: መዝሙረኛው ዳዊት እግዚአብሔር አላማዬ ነው እንዳለው ለዘለዓለም በሕይወት ለመኖር የሚፈልግ ሰው እግዚአብሔርን የሚያስቀይም ኃጢያትን ሁሉ በመሸሽ፣ አምላኩን በመውደድ እጣውን የሚያጠናለት እርሱ ብቻ ነውና መንገዱን አደራ ይሰጣል:: እግዚአብሔርም ስለ ስሙ ክብር ያሳየውን ቁርጠኝነት ተመልክቶ በመከራ ቀን ይሸሽገዋል፣ በባህርና በእሳት መካከል ይመራዋል፣ በአውሎና በወጀብ ያሳልፈዋል:: በሞት ጥላ መካከል እንኳን ቢሄድ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ አይሰጣትም::

ሰው ያሰበበት ቦታ ሊደርስ የሚችለው እግዚአብሔር ከእርሱጋ ከሆነ ብቻ ነው "ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነፃል" መዝ 118:9 ብሎ ጥያቄ ይጠይቅና መንፈስ ቅዱስ በሕሊናው ያሳደረለትን መልስ ነብዩ ሲመልስ "ቃልህን በመጠበቅ ነው " በማለት ነው:: ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ማወቅ ወይም ደግሞ ምስጢሩንና ትርጉሙን መረዳት ብቻ ሳይሆን በልብ ሰሌዳ ውስጥ ቃሉ ተጽፎ ከእግዚአብሔር የሚለይ የሥጋ ሥራን እንድንፈጽም ሰውነታችን ሲያስገድደን መከላከል የምንችልበትን ብርታት ያገኘን እንደሆነ ነው:: ብዙው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መሆን እንደ ቃሉም መመላለስ መልካም



www.ethiopianorthodox.org

መሆኑን የሚዘነጋው አይደለም። ዲያብሎስን ተቃውሞ እግዚአብሔርን የሕይወት ዓላማ አድርጐ ለመከተል ሲሞክር ግን አይታይም።

ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ወሲብ ለመጭዎቹ ዓመታት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚለያይና እግዚአብሔር ካልረዳ በስተቀር ዳግም በማንኛውም ነገር ስኬታማ መሆን ስለማይቻል እንኳን ሊፈጸም ሊታሰብ አያስፈልግም። ቅዱሳት መጽሐፍትን ትርጉም ሰጥቶ ማንበብ ለእኔ ምን መልዕክት አላቸው ብሎ ራስን በቃሉ መፈተሽ፣ በጸምና በጸሎት መትጋት፣ ወንጌል የሚሰበክባቸውን ጉባዔዎች ማዘውተር፣ መዝሙራትን ማዳመጥ፣ ከቀልድ ከቧልትና ከጉንጭ አልፋ ወሬ ይልቅ ከማንም ጋር ቢሆን ስለ እግዚአብሔር ቃል መነጋገር የሚቻል ከሆነ ሁለትም ሶስትም ብትሆኑ እንኳን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ከሆነ ደግሞ ፈተናውን በብቃት ማለፍ ትችላላችሁ።

## 2. ለድንግልና ክብር መስጠት

በስልጣኔ ሽፋን የሚመጡ አላስፈላጊ ስልጣኔ መሳይ ኋላቀርነት በተለይ በሃይማኖትና በባህል ላይ አሳሳቢ አደጋ እየሆኑ ከመጡ ውለው አድረዋል። ድንግልና የክብር ምልክት መሆኑ ተዘንግቶ ሰው የማጣትና ያለመፈለግ እንደሆነ ተቆጥሯል። በራሳቸው የአመንዝራነት እንድምታ ዝሙትን ሥልጣኔ በማለት ሲተነትኑት ይውላሉ ያድራሉ። በእርግጥ ዝሙትን ጌጥ ያደረገ ከዚህ የበለጠ እንዲያስብ አይጠበቅበትም። አባቶቻችሁን እናቶቻችሁን ብትጠይቋቸው ግን ድንግልናን መጠበቅ ማለት ክርስቲያን መሆን፣ መልካም ሰው መሆን፣ ጀግና መሆን እንደሆነ ይነግሯችኋል። መስዋዕትነት የሚከፈልለት ልዩ ክብርም ነው። ይህን ለማረጋገጥ ከስሙ ብቻ መነሳት በቂነው"ክብረ ንጽህና"

እናቶቻችን ሴት ልጅ ድንግልናዋን ለመጠበቅ "እንደ እራስ ነብር" መሆን አለባት ይላሉ ምክንያቱም የወንድ ስሜት የተመቻቸ ሁኔታ ካገኘ ጠቦት ካየ አንበሳ ይከፋል። አንዲት ወጣት ለድንግልናዋ ክብር የምትሰጥ ከሆነ ራሷን በሠራዊት እንደተከበበ ቅጥር እንደጸና ግንብም መቁጠር ትችላለች። በምንም ማባበያና ማታለያ በቃላት ውበትና





በሚፈጸምም ሆነ በማይፈጸም ቃልኪዳን መታለል የለባትም። ለራሷ ያላት ክብር የሚጨምረውና ሰላም እንድታገኝ የሚያስችላት ማንም እንዲያቆሽሻት ሳትፈቅድ ድንግልናዋን ጠብቃ የኖረች እንደሆነ ነው። ድንግልናዋን ጠብቃ የምትኖር ወጣት።

2.1 ክብሯን ለማን መስጠት እንዳለባት እርግጠኛ ስለምትሆን በወሳኔዋ ስትደሰት ትኖራለች። በሕይወት ዘመኗ ሁሉ ሌሎች ጠንካራ ውሳኔዎችን ለመወሰን በራስ መተማመኗን ታዳብራለች።

2.2 ፈጽሞ ተአማኒ በመሆኗ ባሏ የሚሰጣት ክብር ከራሱ አስበልጦ ነው

2.3 ባሏ እጅግ ስለሚያምናት ነገሯን ሁሉ በደስታ ያዳምጣል

2.4 ምንም ያልተነካካ ንጹህ ገጸበረከት ስላቀረበችለት በማንኛውም አጋጣሚ ሊያስቀይማት አይፈልግም ይልቁንም የሚያስደስታትን ነገር ይፈልጋል።

2.5 በሕብረተሰቡ መካከል በተለይም በባሏ ወላጆች እንደ ጀግና ስትወደስ ትኖራለች።

2.6 ቤተክርስቲያን የሰማዕታትን የድንግልና አክሊል ታቀዳጃታለች ።

በአሁኑ ጊዜ ድንግልናን ጠብቆ መገኘት አስቸጋሪ ሆኖዋል። በአንድ ወቅት አንድ ሰው ያለው ነገር አስገርሞኛል። ድንግልናን የጠበቀች ሚስት ማግኘት በሁሉም አቅጣጫ መልካም ነው ሲባል ደም የማፍሰስ ልክፍት ካለባችሁ ነው. ደግሞም ከፈለጋችሁ ማግኘት የምትችሉት "ፖሊዮ" የሚከተቡት ሕጻናት ጋር ብቻ ነው አለ። ለእኔ አስደንጋጭ ንግግር ነበር። ድንግልናቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ወጣት ሴቶች ግን ከእንቁዎች ሁሉ የሚበልጥ የከበረ እንቁ አላቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ድንግልና የማንነት መገለጫ እንደሆነ የሚጠቁሙ ምንባበት አሉ። ዩፍታሔ ጠላቶቹን ለጦርነት ሊገጥም ሲሔድ ለእግዚአብሔር ስዕለት ተስሎ ነበር ስዕለቱም ወደ ቤቱ በድል ከመለስከኝ መጀመሪያ የተቀበለኝን እሰዋልሀለሁ የሚል ነው። ወደቤቱ

ሲመጣ ብቻዋን ድንግል ልጁ ከበሮ እየመታች ተቀበለችው። ለእግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሲነሳ ልጁ ለድንግልናዋ እንድታዝንለት ለሁለት ወር እንዲያሰናብታት ለመነችው ከሁለት ወር በኋላ ስለ ድንግልናዋ አልቅሳ ለእግዚአብሔር ሰውቷታል መ.መሳ 11:1-40

ድንግልናዋን እስከዚያ ጊዜ ጠብቃ የኖረችው በሠርጓ ዕለት እንድትከብርበት ይህንን በመፈጸሟ የባሏ ወላጆች መልካም ሥነ ምግባር ያላት ልጅ ወደኛ ቤት መጣች ብለው እንዲደሰቱ ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለምና ለዚህ ቀን ስላልበቃች እግዚአብሔር ድንግልናዋን ንጹህ መስዋዕት አድርጐ እንዲቀበልላት አዘነች፣ አለቀሰች፣ ጸለየች።ድንግልናዋን እንደ ክብር ባትቆጥር ኖሮማ የመምጫዋ ጊዜ ሲደርስ ለምን ይዥው እቀበራለሁ ብላ በሥጋዋ ላይ በደልን በፈጸመች ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ውጭ የሆኑ ሰዎች እግዚአብሔር የፈጠረልን ለዚህ ነው በማለት ለሚያደርጉት ክፉ ሥራ እግዚአብሔርን እንደተባባሪያቸው በመቁጠር በድፍረት ኃጢአት የሞት ምክንያትን ለራሳቸው ይደረድራሉ።

በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ደግሞ አምኖን እህቱ ትዕማርን ካስነወራት በኋላ ልብሷን ቀዳ እጆቿን በራሷ ላይ አድርጋ እያለቀሰች እንደወጣች እናነባለን። መተርጉማን ቤተክርስቲያን እንደሚስተምሩት በእስራኤል ባህል አንዲት ልጅ ድንግል ከሆነች ፀጉሯን ትሸፍናለች፣ እስከጥፍሯም የሚደርስ ልብስ ትለብሳለች ፀጉሯን ገለጠች ሰወነቷን አጋለጠች ማለት መታፈሪ መከበሪ ቀረ ድንግልናዬንም አጣሁኝ ማለት ነው በዚህም ሰው ሁሉ ያውቅና እንደ ወደቀች ይረዳል። እዚህ ጋር መረዳት የሚያስፈልገው ነገር ድንግልና ፍጹም ክብር ከመሆኑ የተነሳ የራሱ የአለባበስ ሥርዓት እንደነበረው ነው። በመሆኑም ድንግልናን መጠበቅ እንደ ስጦታ ዋጋን የሚያሰጥ በማህበራዊ እሴት ውስጥ ያለው ፋይዳ እጅግ ታላቅ የሆነ ነው። ከጋብቻ በፊት በሚደረግ ስሜታዊ ወሲብ ተመልሶ ማግኘት የማይቻለውን የንጽህና ምልክት ማጣትና መሪር ሀዘንን ያስከትላል።





### 3. መቀራረብን ውስን ማድረግ

በእጮኝነት ወቅት ላይ የሚገኙ ወጣቶች በአብዛኛው ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙት አስበውበትና አቅደውበት አይደለም። በአንድ ወቅት በጣም እየተቀራረቡ እየተነካኩ ረጅም ሰዓት ጭር ባለበት ቦታ ከተቀመጡ ሁኔታዎች መልካቸውን ቀይረው መተቃቀፍ ይጀምራሉ ከዚያም ወደመሳሳም ይገቡና ሩካቤን ይፈጽማሉ። ለጋብቻ ለመጠናናት በሚል ሰበብ በሚቀራረቡበትም ወቅት አደጋው ሊፈጠር ይችላል። ፍተወትን ሊያስነሱ ከሚችሉ ነገሮች ፈጽሞ መራቅ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል። አብዛኛዎቹ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብን የሚፈጽሙት አዘውትረው ከሚያገኙት፣ ከሚቀራረቡት፣ ከሚወዱትና እየተቀጣጠሩ ከሚጫወቱት ሰው ጋር ነው። በትንሹ የተጀመረው መደባበስ ሳይታወቅ ገደቡን ጥሶ መግታት በማይቻልበት ፍጥነት ይጓዛል።

ሰው በተፈጥሮው የሚወደውን ሰው ለማስደሰት የማይፈገቀለው ድንጋይ የለም በዚህ ሁኔታ ላይ ባለበት ወቅት በተለይም ሴቷ የምታሳየው አሳሳች ምልክት እርሱን ወደ አልሆነ አቅጣጫ ሊመራው ይችላል። ለምሳሌ በአንድ የቀጠሯቸው እለት ከወትሮው የተለየ በጣም ተሽቀርቅራና ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ የሰውነት ክፍሏን የሚያሳይ ልብስ ለብሳ ልብን በሚሰርቅ ፈገግታ እያናገረችው አብራው ለተወሰነ ጊዜ የምትቆይ ከሆነ ያደረገችው ነገርን በመመልከት መልስ መስጠት እንዳለበት ያስባል። ያስደስታታል ብሎም ስለሚገምት በፍጥነት ወደ ተግባር ይቀይረዋል። እርሷ እንደዛ ያደረገችው መጥፎ ጉትን አስባ ባይሆንም እንኳን አደገኛ አሳሳች ምልክት ነው።

በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ኋላ ቀርነት የሚቆጠር ቢሆንም ጥቅሙ ግን ብዙ ነውና በመዝናኛ ቦታዎች፣ መልካም ላይሆን ይችላሉ ብላችሁ በምትገምቱበት የቀጠሮ ጊዜ ታዛቢ ይዞ መቅረብ መልካም ነው። አቅምን ማወቅ ታላቅ ጥበብ ነው። ሰዎች ወሲብን አላስፈላጊ በሆነ ጊዜ የሚፈጽሙት ከእነርሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ምን እያደረጉ እንደሆነ ለራሳቸው እንኳን ሳይገባቸው ነው። ራሴን መግዛት

እችላለሁ፣ ማገናዘብ እችላለሁ ማለት ሰው መሆንን መዘንጋት ነው:: በሰው ተፈጥሮ ውስጥ በየቀኑ ፆታዊ ፍላጐት ይንጸባረቃልና:: "በራሱ ማስተዋል የሚታመን ሰው ሞኝ ነው" ምሳ 28:26

ባልታሰበ ወቅት ሁኔታዎች ወደ አልተፈለገ አዝማሚያ ሲያመሩ አንደኛቸው ድርጊቱን ሊያቆም የሚችል ነገር መናገር የግድ አለባቸው:: በተለይ የሴቷ ጥንካሬ ከምንም በላይ አስፈላጊ የሚሆንበት አጋጣሚ ይህ ነው:: ያለ ምንም ማንገራገር በቁርጠኝነት ልትቃወም በግልጽ ቋንቋ እምቢልትል ይገባል:: ይህ እንግዲህ የመጨረሻው ደረጃ ነው:: እዚህ ከደረሱ በኋላ መመለስ ከባድ ስለሚሆን የነገር ሁሉ ቁልፍ ያለው ለእያንዳንዱ ርምጃ መቀራረብን ውስን ማድረግ ላይ ነው::

ረ. <u>ተጨማሪ አስተያየት</u>

በትዳር ተወስኖ መኖር የሚያስገኛቸዉ እያሌ ጥቅሞች ቢኖርም በሌላ በኩል ደግሞ ተስማምቶና ተከባብሮ መኖር የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ የዚያኑ ያህል እልህ አስጨራሽ ይሆናል:: በእጮኝነት ወራት መጤን ያለበት አንገብጋቢው ነገር ትዳሩን ለዘለቄታ እንዴት ማቆየት እንደሚቻል ነው:: ውጤቱ ተቃራኒ ከሆነና ልዩነቶች ሊጠቡ ካልቻሉ ይሉኝታ አያስፈልግም:: መፈራራትም ሆነ መሳቀቅ ሳይኖር በግልጽ ውይይት ተማምና መለያየት መልካም ነገር ነው:: አብረው በትዳር እንደማይዘልቁ እያወቁት አንዱ በአንዱ ላይ ሆኖ የተሻለ ነገር እስከሚያገኝ ድረስ እንደ እውሬ አድፍጦ መጠበቅ በሰው ነፍስ ላይ የሚፈጸም ደባ ነው::በአንድ ነገር ላይ ስኬታማ መሆንና አለመሆን የሕይወት አንዱ ክፍል መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል:: ወደ መምህረ ንስሀ በመሔድ ወደፊት መቀጠል እንደማይችሉ አሳውቆ በእጮኝነት ጊዜ የተነጋገሩትን ምስጢር ለመጠበቅ ቃል በመግባት በጸሎት መለያየት አያስነቅፍም::

ከሥነ "ምግባር" ውጭ በሆነ ሁኔታ ለምን እንኳን ግንኙነቱን ማቋረጥ እንዳስፈለገ ሳያሳውቁ "እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይብቀል" አይነት ክፋት ለመንፈሳዊ ሰው ወንጀል ነው:: ማንም በማይፈልግበት ሁኔታ ውስጥ በተጽዕኖ መቀጠል የለበትም:: ስለ እሳለፉት መልካም ጊዜ





ተመስጋግኖ እግዚአብሔር መልካም የሆነውንና የተሻለውን ነገር እንዲያዘጋጅላቸው በመመኘት ለወደፊቱም በጥሩ ወንድምነትና እህትነት ለመቀጠል በሚያስችሉ ጠቃሚ ሐሳቦች ላይ በመወያየት ሥነ ስርዓት ባልጐደለው መግባባት ሁሉንም ነገር ባለበት ማቆም ሰብአዊነትም መንፈሳዊነትም ነው:: ሰፊ ርቀት ባለበት ቦታ ላይ ሆኖ ወይም ከሀገር ውጭና በሀገር ቤት እያሉ በፍቅር መኖር ካልቻሉ ሀሳባቸውን መቀየራቸውን ለማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው::በተስፋ የሚጠብቀው ወገን እየተጐዳና እየሞተ የራሱን ኑሮ በሌላ አቅጣጫም ለማጠንከር መሯሯጥ በእግዚአብሔር ፊት ጸያፊ ነው:: ተማምኖ መለያየት ግን ምንም ክፍት የለውም::

# ምዕራፍ አምስት

## ሠርግና ጣጣው

ሠርግ በዘፈን፣በጭፈራ፣በመብላትና በመጠጣት የጋብቻ በዓል የሚከበርበት መንገድ ነው። ሠርግ ጠቀሜታም ጉዳትም አለው። በንጽጽር ሲታይ ግን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እጅግ ያመዝናል። ብዙዎች ብዙ ጥቅም እንዳለው ስለሚገምቱ በዚህ ጽሑፍ ያንኑ ደግመን እናወራም ነገር ግን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚፈጥረውን ጉዳት ለማሳየት ተሞክሯል። ሰዎች ወደ ሠርግ የሚገቡት ዋናው ምክንያት ጋብቻ ጋብቻ የሚሆነው ሠርግ ከተሠረገ ነው የሚል ፈሊጥ ስላለ ነው። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ባህል ሊቀረፍ የማይችል ተጽዕኖ እንዳሳደረ አይካድም። ከጋብቻ በፊት ሩካቤን የፈጸሙ ከሆነና በአጋጣሚ ሴቷ ካረገዘች ይህንን ውርደት ለመሸፈን ሲባል ያለምንም ዝግጅት ሠርግን ሠርገው ይጋባሉ። በዚህ ወቅት ግን የሚያስፈልገው መጋባት አልነበረም አስቀድሞ ንስሀ መግባት እንጅ። የሠርግ ባህል እንደየ አካባቢው እንደ ባህሉና እንደ ሕብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ መለያየቱ ግልጽ ነው። የሠርግ ባህል በዚህ ዘመን ሊወጡት የማይችሉት የችግር አረንቋ እየሆነ መጥቷል። እያደረሰ ያለው ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ተጽዕኖ ከታየ ከጉጅ ባህልም በላይ እንደሆነ ክርክር አያስፈልግም። የችግሩ ውጤት ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሀገር ጀምሮ እስከ አንድ ግለሰብ ድረስ ያጠቃልላል።

### ሀ. በሙሽሮች ቤተሰብ ላይ

ወላጆች ሠርግን በአብዛኛው የሚፈልጉት የሚያተርፍላቸው ደስታ ስላለ ብቻ ሳይሆን አላስፈላጊ የሆነ ውዳሴን ለማግኘትም ጭምር ነው። ከዚህ በፊት ለሰዎች ሠርግ ያደረጉትን አስተዋጽኦ መልሰው ለመቀበልና ባለመሠረጋቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ግፊት ለመጋፈጥ ስለማይፈልጉ ነው። የራሱን ኑሮ መኖር የማይችል ሰው ደግሞ ኑሮውን ይቀማና የሰው ኑሮ መኖር ይጀምራል። የሰው ኑሮ





የሚኖር ሰው እየኖረ ሳይሆን እያኗኗረ ነው። ሠርግ መሰረግ ያሰበት መደገሻ ገንዘቡ በቂ የሆነና ሠርጉ ካለፈ በኋላ በኑሮው ላይ ምንም ተጽዕኖ የማይፈጥርበት ከሆነ ቢሠረግ አንዳች ችግር የለውም የሚሉ አንዳንድ ወገኖች አሉ። በመሰረታዊ ሀሳብ ደረጃ ሠርግ ምንም ትርፍ የለውም። ሠርግ አለመሰረግ የሚያያዘው ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ሳይሆን ከመልካም አስተሳሰብ ጋር ነው።

ልጃቸውን ለመዳር ብለው ከባንክ በመበደር፣ ከዕቁብ በመውሰድ፣ ከመስሪያ ቤት "ክሬዲት" በመጠየቅ የራሳቸውን የትዳር መሰረት የሚጉዱ ሰዎች ልጆቻቸውን ካለመጥቀማቸው በተጨማሪ ሌሎቹን ልጆች በአግባቡ ለማስተማር እንኳን እንዳይችሉ ጥሪታቸውን አሟጠው ያፈሳሉ። ኑሮ በጣም ከባድ ነው። አንድ ወላጅ ለልጄ ይህንን አወርሰዋለሁ የሚለው ነገር እየጠፋ መጥቷል ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ኑሮ ውርስን ማንም አይጠብቅም። የጥንቱ የኑሮ ሒደት ልጆች ከወላጅ በሚወርሱት ገንዘብ ላይ ተመስርተው የራሳቸውን አዲስ ኑሮ መመስረት ነበር። አሁን ግን ሊያወርሷቸው የሚችሉት ነገር ቢኖር ትምህርት ብቻ ነው። ወቅቱ የሚጠይቀውን ዕውቀት እንዲያገኙ ማድረግ ለልጆች ባለውለታ ከመሆን በላይ ለሀገርም መሥራት ነው። ወቅቱ የሚጠይቀውን ትምህርትን ለማግኘት ብዙ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ያስፈልጋል። በልቶ ለማያመሰግን ሰው ያንን ያህል ድካም ከመድከም ልጆችን በጥሩ ሁኔታ ማስተማር ግን የማንነት ጥያቄን በአግባቡ መመለስ ነው። አንድን ልጅ ለመዳር ተብሎ ብቻ በሚደረግ ከንቱ ድካም የመላ ቤተሰቡን የኑሮ አቅጣጫ የሚያጠፋ ድርጊት ወላጆች ለመፈጸም መነሳት የለባቸውም። አዲስ ቤት የማይጉለው ነገር የለም ይህንን ሁሉ ሕዝብ ጠርቶ ብሉልኝ ጠጡልኝ እያሉ ልብን ከማድረቅ ለልጆቻቸው ጉጆ ድጋፍ የሚሆን ዘወትር የማይረሳ መልካም ነገር አድርገው ለልጆቻቸው የሕይወት ዘመን ባለውለታ ቢሆኑላቸው አርቆ አስተዋይነት ያመለክታል። እንዲያውም ከፍተኛውን ኃላፊነቱን መውሰድ ያለባቸው ሠርግ የመደገስ አቅም ያላቸው ባለሀብቶች ናቸው። በህብረተሰቡ መካከል ትልቅ የአመለካከት ለውጥ



www.ethiopianorthodox.org

የሚመጣው ማድረግ የሚችለው ማድረግ እየቻለ ጠቃሚ አለመሆኑን አውቆ ሲተወው ብቻ ነው:: እነርሱ ከተውት እኔማ ብተወው ምንም ችግር የለውም የሚለው አስተሳሰብ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ወደሚኖረው ህብረተሰብ መካከል ሰርፆ ይገባና በሒደት ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ሠርግ የሚባለውን ከንቱ ድካም ርግፍ አድርጐ ይተወዋል:: ዛሬ በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር አመታዊ ገቢ ያላቸው አውሮፓውያን በሠርጋቸው ላይ የሚጋበዟቸው እንግዶች ውስን መሆናቸውንና ያላቸው ብቸኛ አንድ ሚዜ እንደሆነ ስንሰማ ሠርጋቸውን በመጠኑ ያደረጉት የገንዘብ ችግር ስላለባቸው ሳይሆን የአመለካከት ልዩነት ስላለ እንደሆነ ቁልጭ ብሎ ይታየናል::

ለ. በሙሽሮች ላይ

ሠርጉን ራሱ የደገሰ ሙሽራን ሠርጉ ካለፈ ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ ትዳር እንዴት ነው ብላችሁ ጠይቁትና ሠርግ መሠረግ እንዳስበችሁ ንገሩት የሚመልስላችሁ መልስ የዘለዓለም ትምህርት ነው:: ወደ አዲስ ጐጆ ሲገባ ቤትን አደራጅቶ ከሰዎች ጥገኝነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገል ነበር:: በሠርግ ምክንያት ግን የታሰበው ይቀርና ባዶ ቤት ገብቶ መተከዝ ይጀመራል ብድሩም ይቀጥላል:: ከዚህ ይልቅ ወደፊት እንደ ትናንቱ ቤተሰብን መጐብኘት፣ ሲቸገሩ መርዳት ሲከብድ ስለሚችል ማንንም ሰበብስቦ ከማስከር የእርሱን እጅ ዳግም እንዳይጠብቁ የሚቋቋሙበት ነገር ቢያደርግላቸው፣ ልጆች መወለዳቸው አይቀሬ ነውና ቅድመ ዝግጅቱን ቢያጠናቅቅ ኑሮን ይቀድመዋል:: ሳይማር ያስተማራቸውን ቤተሰብ ካልረሱ እግዚአብሔርም አይረሳቸውም ልጆቻቸውንም እነርሱ አደረሱበት ያደርስላቸዋል:: የእናት ምርቃት እድሜን ያርዝማል የአባት ምርቃን መንገድን ያቀናል::

ቤታቸው ቁጭ ብለው የፎቶ ግራፍ ክምር እየተመለከቱ ቪዲዮአቸው ላይ ሲያፈጡ የሚሰማቸው ሥሜት በሠርጉ ሰሞን የተሰማቸውን ስሜት አይነት በፍጹም ሊሆን አይችሉም:: ቢያንስ ሠርግ የጐዳቸው ነገር ባይኖር እንኳን መድረስ ያለባቸው ደረጃ ላይ





በፍጥነት እንዳይደርሱ በተለያየ መንገድ ተጽዕኖ እንዳደረገባቸው ያውቁታል:: "ገንዘብ የሚገኘው በሠለለ ልብ የሚገኘው በስልሳ" ሆኖ ነው እንጂ እንዲህ በጉዞ ላይ እንቅፋት ከሆነ እስከ ወዲያኛው ቢቀርም ግድ የለም::

ሐ. በሙሽሮች ወዳጆች በተለይ ሚዜዎች ላይ

ሚዜነት ስሙ ተቀይሮ "ከኘሮግራም ውጭ" መሆን ተብሎ ቢተረጐም የደረሰባቸው ይስማሙ ይመስለኛል:: ጓደኛን ላለማስከፋትና ላለማስቀየም ሲባል ሠርግ እያስፈልግም ብለው የሚያምኑ ሳይቀሩ አብረው ይቸገራሉ:: ለሠርግ አንድ ልብስ፣ ለመልስ ሌላ ልብስ፣ ለቅልቅል ሌላ ነገር እንዴት ይቻላል?:: ችግሩ ደግሞ ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል አለመሆኑ ነው:: እንግዲህ ሰው ሁልጊዜ ሚዜሆኖ አይኖር:: እነዚህ ሚዜዎችም ሚዜ ሁኑን ሲባሉ እምቢ ማለትን አይደፍሩም ምክንያቱም ሚዜዬ ነህ ማለት የቅርብ ሰዌ ነህ ማለት ነው:: ለእኔ ሠርግ ማን ሚዜ ይሆነኛል ዛሬ እምቢ ካልኩ የሚል ፍራቻም አለ:: ለሚዜነት መመረጥ ደግሞ ከሰው ተለይቶ ክብር እንደ መሰጠት ይቆጠራል:: ይሁን እንጂ በነዚህና በሌሎች ተራ ስሜቶች ላይ ተመስርቶ ራሳቸውን እየጐዱ አላስፈላጊ የሆነ መስዋዕትነት መክፈል ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው:: የራሱ ጓዳ የጐደለው ብዙ ነገር እያለ ከደመቀው ለመጨፈር መነሳት ኑሮን፣ቤተሰብን፣ልጆችን መዘንጋት ነው:: ሠርጉ ሲያልቅ ሚዜ ቤት ሌላ ግጭት ከተፈጠረ ሚዜ ባይሆን ይሻለዋል:: ከሌሎች ጋር ባይጋጭ እንኳን ከራሱ ጋር ይጋጫል:: ከዚህ የበለጠ ግጭት ደግሞ በዓለም ላይ የለም::

መ. በመንፈሳዊነት ላይ

መንፈሳዊነት የሚነገር ሳይሆን የሚኖር ነው:: ሀሳባዊ የሆነው መንፈሳዊነት በጽድቅ ስራዎች ይገለጣል:: የመንፈስ ፍሬ ግን "ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ራስን መግዛት" ገላ 5:22:: ሠርግ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በሚያገናኘው መሰላል መንፈሳዊነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ይፈጥራል በዚሁ ምዕራፍ ቁ.19 ላይ የሥጋ ሥራ ተብለው ከተገለጡት መካከል ስካር፣

ዘፈን፣ ዝሙት፣ መዳራት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን የሚያደርግ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም፡፡ የመንፈሳዊነት ነቀርሳ የሆኑት የሥጋ ሥራዎች ደግሞ በሠርግ ጉልተው ይታያሉ፡፡ ከጾቅም በላይ ይበላል፣ ይሰክራል፣ መዳራት ይነግሳል/ከአለባበሳቸው ጀምረው ለመዳራት ተዘጋጅተው የሚመጡ ይበዛሉ/ በኃጢያትና በዝሙት ይጠናቀቃል፡፡

የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥበታል ተብሎ በሚጠበቀው መንፈሳዊ ጋብቻ ላይ እንኳን ወንጌልን ማስተማር የማይቻልበትን እንቅፋት እየተፈጠረ ነው፡፡ የሠርጉ ግርግር ሁካታ፣ የሚጠጣው ጠጅና አልኮል፣ ሰዎች በቃለ እግዚአብሔር ለመፈወስ፣ ሙሽሮቹን የባረከ እንደባረካቸው ሳይሆን ሠርግን ለማድነቅ ብቻ መምጣት የወንጌል ጸር ሆኖዋል፡፡ በሁሉ ነገር የተሰማማች ሙሽሪት ሠርግ አያስፈልግም፣ ቬሎ አልጉትትም፣ጡርምባ እያስነፋሁ ከተማውን አላውክም በሚለው መልካም አስተሳሰብ ተደንቃ ሳታበቃ ሌላ መዘዝ ትመዝና መንፈሳዊነቷን ገደል ትከተዋለች፡፡ "ለሠርጌ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" የሚለውን የባህል ዘፈን ለራሷ እየዘፈነች ካደፈጠችበት ቦታ ተነስታ ትዳሯን ሳትጀምረው ትጨርሳለች፡፡

የሠርጉ ድግስ ሲደገስ ዝም ብለው ይጠብቁና የጥሪ ካርድ ከተበተነ በኋላ ቤተሰብ አስቸገረኝ ወንድሜ ተቆጣኝ በማለት ምንም በማያሳምን ተራ ምክንያቱ የተሰማሙበትን ነገር ጥሰው ሰው ከተጠራ በኋላ ምንም አያመጣም ስለዚህ የፈለኩትን አደርጋለሁ ይላሉ፡፡ በዓለም ውስጥ የምትደረገው እያንዳንዷ የሠርግ ዝግጅት አትቀርብኝ "ሠርግና ሞት አንድ ነው" ይህ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ ጋብቻው ቢቀር ይሻለኛል የሚል መከላከያ ነጥብ ያነሳሉ፡፡ በዚህኛው ወገን ካልፈለግሽ ውሳኔሽን አጸድቅልሻለሁ የሚል አስደንጋጭ መልስ ሲመጣ ሠርጉ ይረሳና አንተም ተው አንቺም ተይ የሚል ሽማግሌ መከራውን ማየት ይጀምራል፡፡ እንደሆነ ሆኖም ሠርጉ ይፈጸማል፡፡ በእርግጠኝነት ከዚህ በኋላ እነዚህ ወገኖች የትዳር ጓደኞች ሳይሆኑ የኑሮ ጓደኞች ናቸው፡፡





ትዳሩም በማንኛውም ወቅት ሊቋረጥ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

ጋብቻው እንዲባረክ በቃና ዘገሊላ የነበረው አምላክ ከሐዋርያትና ከእናቱ ጋር ከተገኘ በቂ ነው እርሱ ደግሞ በሥርዓተ ተክሊል በሥጋወደሙ ጋብቻው ሲፈጸም በሕይወታቸው ውስጥ ይኖራል ለዘለዓለምም አይለያቸውም፡፡ ሌላው በቅርብ አመታት የተጀመረ "አልሸሹም ዘወር አሉ" አጉል መንፈሳዊነት ማስመሰል ነው፡፡ ሁለቱም እንዳይቀርባቸው የእግዚአብሔርም የዓለምም ናቸውና በሁለት ሀሳብ ያነክሳሉ፡፡ ክርስትና ግን የምርጫ ሕይወት ነው፡፡ ደግሞም ሁልጊዜ የሴኬምን ነውር ሳይቀብሩ መጥተዋልና ተመልሰው ለማንሳት ብዙም አይቸገሩም፡፡ አንድ ቀን ሠርግ አንድ ቀን ተክሊል፡፡ ለእነርሱ የጋብቻ ዕለታቸው የተክሊሉ ቀን ሳይሆን የሠርጉ ቀን ነው፡፡ ይህንንም በእያንዳንዱ የሠርግ ጥሪው ወረቀት ላይ ተመልከቱ፡፡ ለምን እንዲህ እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ ለሥጋወደሙ ክብር ለመስጠት ነው ይላሉ፡፡ ጥሩ! እንደዛ ከሆነ ከተክሊሉ ጋር አንድ ቀን ማድረግ ስላልፈለጉ እንጂ በዓለማዊያን መንገድ ሠርጋቸውን ለመፈጸም፣ ቬሎ ለመጐተት፣ ተስማምተዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህም በኩል በመንፈሳዊነታቸው ላይ ጉድለት እንደሚታይ መገንዘብ አለባቸው፡፡ የቤተክርስቲያንን ጌጥ የክብር መልክት የሆነውን ካባውን ለብሰው፣ አክሊሉን ተቀዳጅተው እንደገና ምን ለማግኘት? ምንስ ለመጨመር? ይሆን እንደገና ወደ ዓለማዊነት የሚመለሱት፡፡

### ተጨማሪ ድካም

የሠርግ ድካሙ ድግስ መደገሱ ወይም ደግሞ ሠርጉ አልደመቀም፣ ጠላው ቀጠነ፣ እንጀራው አረረ ተብሎ መተቸት ብቻ አይደለም አስከትሏቸው የሚመጣ ተጨማሪ ድካሞች አሉት፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ከሠርጉ ባልተናነሰ ሁኔታ ኑሮን የሚወጉ አሜኬላዎች ናቸው፡፡

1. ጥሎሽ

በጥንት ዘመን ሙሽሪት ወደ ቤቷ ከመምጣቷና ከሠርጉ በፊት ለቤተሰቦቿ ማጫ ይሰጣል፡፡ እንስሳት፣ገንዘብና ሌላም ነገር ሊሆን

ይችላል። አስፈለጊነቱም ሙሽሪት ወደ ቤቷ ስትመጣ ባዶ እጃን እንዳትገባ ቤተሰቦቿ ከሚሰጧት ስጦታ ጋር ጨምራ ጉጆዋን እንድታጸና በት ነው። ከዚህ ሌላ ለሙሽሪት በግሏ የምታጌጥበትና የምትዋብበት የወርቅ፣ የአንቁ ጌጥ ይሰጣታል። እያውብርም ለይስሀቅ ሚስት ለርብቃ ይህንኑ አድርጓል። ዘፍ 24:53

ጥሎሽ መስጠት ያለበት ሙሽራይቱ ስለሚያስፈልጋት ወደፊትም የእርሱ ስለሆነች እንጂ የተለየ የክብር መግለጫ ወይም ሀብት ማሳያ ስለሆን አይደለም። ነገር ግን በሠርጉ ጊዜ በብዙ ወጭዎች ኪሱ ስለሚራቆት ጥሎሽ ማስቀመጥ ካልቻለ እርሷ ብትዋብ የበለጠ ጥቅሙ ለእርሱ ነውና ከሠርጉ በኋላ ሊያደርግላት ይችላል። የግድ በሠርጉ ዕለት መፈጸም አለበት በሚል ፈሊጥ ሥጦታ ተውሰው ወይም ተበድረው፣ ገዝተው ያመጡና ሠርጉ ካለፈ በኋላ የተዋሱትን ሲመልሱ ወይም የተበደሩትን መክፈል ሲያቅታቸው በትዳሩ ላይ የሀዘን ድባብ ያጠላል። አንዳንድ ሰዎች እድሜያቸውን ያለትዳር ከሚፈጅበት አንድ ምክንያት ገደብ የለሹን የጥሎሽ ጥያቄ መመለስ ስለሚያቅታቸው ነው። ጥሎሽን እንደ ክብር ምልክት እንደፍቅርም መግለጫ ከተቆጠረ ብዙዎች የራሳቸውን መንገድ በመቀየስ በህግ ባይጋቡም ራሳቸው ድረው የሚኖሩበት ዓለም መፈጠሩ አይቀሬ ነው ጥሎሽ ተጽኖው ይህንን ያህል ከሆነ እስከ መጨረሻው ቢቀር ምንም ማለት አይደለም።

2. መልስ

እየተደረገ ያለውን ነገር በአንክሮ ለተከታተለው ነገ ምጽአት ይደርሳል ስለዚህ ያለህ ገንዘብ መጥፋቱ አይቀርምና ዛሬውኑ በታትነው የተባለ ነው የሚመስለው። ያን ያህል ድካም በደከሙና ያን ያህል ገንዘብ ባባከኑ በሁለተኛው ቀን ከሥራቸው ነቀሉ የሚያጠፋ ምንም ማንሠራራት የማይችሉበትን የውድቀት መንገድ ደግመው ይጀምራሉ። ኑሮአቸውን ማሸነፍ የሚችሉበትን መንገድ ስተው ኑሮ እነሱን የሚያሸንፍበት ቦታ ላይ ይቆሙና አጉል እልክ ይጋባሉ። በሠርግ ምክንያት ልትወጣ የደረሰችው ነፍስ ላይ መልስ ሲጨመርባት ጸጥ ማለት ትጀምራለች። ሰው ሁሉ ሠርጉን አድንቆ በመልሱ ጨፍሮ ቤቱ





እያጨበጨበ ሲገባ የመሸሮች መደበኛ ሥራ ትርፍና ኪሳራን ማስላት፣ የተሠበረ ዕቃን መክፈል ስለወደፊቱ መጨነቅና መጠበብ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ሠርግ ምን አልባት በጣም ጥቂት በጎ ጐን አለው ብለን እንገምት ይሆናል "የባሰ አለ አገርህን አትልቀቅ" አይደል መልስ ግን ለምን እንደሚደረግ የማይታወቅ፣ ምንም ጥቅም የሌለው እንዲሁ ባህል ስለሆነ ብቻ ከንቱ ልማድ እንዳይቀር የደስታውን ጊዜ ረዘም አድርጐ ጓዷን ለማራቆት የሚደረግ መብላትና መጠጣት መዝፈንና መጨፈር ነው።

3. ቅልቅል

ቤተሰብን ለማስተዋወቅ የበለጠ ለመቀራረብ አስፈላጊ እንደሆነ ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ አይታጡም። በርግጥ ቤተሰብ መተዋወቅ አለበት። ነገር ግን አሁንም እንደገና ተጨማሪ ድካም ካላስፈለገ በስተቀር ቤተሰብን ለማስተዋወቅ ይህን ያህል ድግስ ደግሶ እንደገና መዝፈንና መስከር አያስፈልግም ። ቤተሰቦቹ ልጆቻቸውን አሳልፈው የሰጡት እኮ ስለሚተዋወቁ እንጂ ዝም ብለው ለማያውቁት መንገደኛ አይደለም። በጋብቻው ዕለት ተመራርቀው ተሸኛኝተው ከዚያም በፊት የጋብቻው ሁኔታ እንዴት መከወን እንዳለባቸው ሲመካከሩ ኖረው እንደ አዲስ እንተዋወቅ ማለት "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" ነው። ልጆች የትዳር አጋሮቻቸውን ወላጆች ስለሚያከብሩ፣ ስለሚፈሩምና የባህል ጫናው ከፍተኛ ስለሆነ በጣም መቀራረብ አልተለመደም ይህን አይነጥላ ለመግፈፍ አስፈልጐ ከሆነ ሙሽሮችን ጠርቶ አንድ ቀን ምሳ በመጋበዝ እየመጣችሁ ጠይቁን ከእንግዲህ እንዳትጠፋ ብሉ በእግዚአብሔር ስም መርቆ ማሰናበት በቂ ነው።

# ምዕራፍ ስድስት

# ትዳር ከሠርግ በኋላ

ለብዙ ጊዜያት ሲጨነቁበት፣ ሲወጡበትና ሲወርዱበት የነበረውን የጋብቻ በዓል ካከበሩና በይፋ ካሳወቁ በኋላ ሙሽሮች እነርሱም እንደወላጆቻቸው የትዳርን ቀንበር ለመሸከም ወዲያውኑ ቤቴ ቤቴ ማለት ይጀምራሉ:: እግዚአብሔር የፈቀደው ትዳር በጥሩ የእጮኝነት ጊዜ ተመክሮበት እስከዚህ ጊዜ ከደረሰ ከዚያ በኋላ ያለውን ሕይወት በሚገባ ለመምራት አስቸጋሪ ነገር አይፈጠርም:: ይሁን እንጂ አዳዲስ ማህበራዊ ግንኙነቶችና ጋብቻው የሚያመጣቸው የትዳሩ አንድ አካል የሆኑ የተለያዩ ክስተቶች ይፈጠራሉ::

ሴቷ ሚስት፣እናት፣ የቤተሰብ ኃላፊ መሆንና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ከትዳሯ ይበረከትላታል:: ወንዱም እንዲሁ እርሱን የሚመለከት ሌላ ሥራ ይኖረዋል:: ሁሉም ነገር ግን በመረዳዳትና በመከባበር በመካከላቸው ንፋስ እንዳይገባ ፍቅራቸውን የሚያጠነክር ስለሆነ የሚናፈቅና የሚወደድ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከወትሮው ልዩ የሆነ መቀራረብና የሥሜት መተሳሰር ስለሚኖር ፍቅር የሚገለጥበትን የመጨረሻውን ርካታ ከተቀደሰው ምንጣፋቸው ከተባረከው መኝታቸው ያገኛሉ:: ይህንን የተቀደሰ ትዳር ለመበጥበጥ ጠላት በሌሊት እንክርዳድ ሊዘራ ይሞክራል:: ትዳር እስርቤት ነው እስኪባል ድረስ ሊወጡት የሚያስቸግር የፈተና መአት ይደረድራል:: ባልና ሚስት ግን ትዳራቸውን ዘላቂ ለማድረግ በመንገዳቸው ሁሉ ሰይጣንን በመቅደም እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት /በውስጣዊ ግንኙነት/ ወይም በማህበራዊ ግንኙነታቸው ፍጹም መግባባት ሲኖራቸው የግድ ያስፈልጋል::

1. ሩካቤ

ሩካቤን የፈጠረው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነው:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር መልካም አድርጐ የፈጠረውን ነገር ለክፉ ምኞትና ለሞት ለተሰጠ ነውር





መጠቀሚያ ማድረግ በራሱ ኃጢያት ነው:: ትክክለኛው የሩካቤ ሥርዓት የሚፈፀመው በጋብቻ ውስጥ በአንዲት ሴትና በአንድ ወንድ መካከል እንዲሆን ተደንግጓል:: በዚህ ሥርዓት እየተጓዙ ባልና ሚስት የፍቅራቸውን ደስታ የሚያጣጥሙበትና በልጆች በረከት የሚበለጽጉበትን ጣፋጭ ሕይወትን ከሩካቤያቸው ያገኛሉ:: የሥነ-አዕምሮ ባለሙያዎች ሩካቤ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ እንደማንኛውም ለመኖር የግድ አስፈላጊ ነገር ሁሉ የግድ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ:: በእርግጥ ሁሉም ሰው ወሲባዊ ፍላጐት እንዳለው የሚካድ ባይሆንም የመኖርና ያለመኖር ጥያቄን የሚያስነሳ ነገር አይደለም:: ቅዱሳን አበው በገዳም ንጽሕ ጠብቀው ሲኖሩ ተመልክተናልና:: የጋብቻም ዋናው አላማ ሩካቤ ብቻ ሳይሆን አብሮ በመኖር ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ተጨማሪ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችም መኖራቸው ነው::

እግዚአብሔር የባልና ሚስትን ግንኙነት የአንድነታቸው መገለጫ አንዱ ጉን እንዲሆን ተጠቅሞበታል በክርስቲያን ባለ ትዳሮች መካከልም የሚፈጸም ሩካቤ ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው የፍቅር መገለጫ የአንድነት ነጸብራቅ ነው:: ለምሳሌ:- እንስሳት ወሲብ ይፈጽማሉ:: በሥሜት ብቻ ተነስተው ፍትወታቸውን ለማርካት ያለምንም የፍቅር ግንኙነት ያደርጉታል:: አንድ ሰው ከአንዲት ሴት ጋር በመካከላቸው ፍቅር ሳይኖር ወሲብ ሊፈጽም ይችላል:: ወይም ደግሞ ምንም አይነት ጾታዊ ግንኙነት ሳይፈጠር ሰዎች በንጹህ ፍቅር ሊዋደዱ ይችላሉ:: የዚህ አይነት ግንኙነት ግን በጋብቻ ውስጥ ካለው ፍቅር ጋር አይወዳደርም የአንድነት መገለጫ ሊሆንም አይችልም:: የወንድና የሴትን ተፈጥሮአዊ ይዘት በሩካቤ ወቅት ያለውን የአካል አንድ መሆን ስንመለከት ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው የሚለውን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ንግግር ያጐለብተዋል::

ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በኤደን ገነት እያለ እግዚአብሔር "ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት" በማለት በሩካቤ ሰብአዊ



www.ethiopianorthodox.org

እርካታ እንዲያገኙና ልጆችንም እንዲወልዱ አዟቸዋል:: ለሰው ልጆች ደስታን እንዲፈጥርላቸው ከኃጢአት አንጽቶ በባልና በሚስት መካከል የሚፈጸመውን ግንኙነት በቃሉ አጽንቶታል::ኃጢአትን ባደፈጉ ጊዜ በገነት ኃጢአተኛ አይቀመጥምና አዳምና ሔዋን ተባረሩ:: ሩካቤ ግን ነውርና ነቀፋ የሌለበት የእግዚአብሔር በጎ ሀሳብ ስለሆነ ገና በገነት እያሉ ተሰጥቷቸዋል:: " ምንጭህ ብሩክ ይሁን ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ እንደተወደደች ዋልያ እንደተዋበችም ሚዳቆ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ በፍቅሯ ሁልጊዜ ጥገብ" ምሳ5:18

እሳት አጠቃቀሙን ካወቁበት በጣም የሚጠቅም አስፈላጊ ነገር ነው በአግባቡ ካልተጠቀሙበትን ቤትን ንብረትን የሚያጠፋ አካልን የሚያቆስል ክፉ ነው:: ሩካቤም እንደ እሳት ነው እንደሚገባ ቢጠቀሙበት በረከትን ያተርፋል/ልጆችን/ ያስደስታል፣ በፍቅር ያስተሳስራል:: እንደማይገባ ከተጠቀሙበት ግን እንደ ተለመለመ ግንድ ቅጠልና ቅርንጫፍ ሳያስቀር አንጨርጭሮ ያቃጥላል:: በዓለም ውስጥም የሚታየው በሽታ ረሀብ መቅሰፍት በአብዛኛው ገደብ ከሌለው ፍትወታዊ ወሲብ የሚመነጭ ቅጣት ነው:: ከጋብቻ ውጭ ግብረሰዶም /የተመሳሳይ ጾታ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከዘመድ ጋር ወሲብ መፈጸምና ከእንስሳትና ከአጽዋት ጋር ሳይቀር መገናኘት ሊበርድ የማይችል እሳት ወደ መሬት እየጠሩ የሚገኙ ነገሮች ናቸው::

በአንድአንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም ሥጋዊ ግንኙነት እንደ ህግ ተቆጥሮ በባህሉ ውስጥ ያለምንም መሸማቀቅ በኩራት ሲኖሩበት ይታያል:: ይህንን ፈቃድ የሚያገኘው ግን ባል ብቻ ነው:: በተለይ ሴቷ መካን ናት ብሎ ከታመነ ምንም ችግር አይኖረውም:: ባል መካን የሚሆንበትም አጋጣሚ ተዘንግቷል:: ማንም ሰው ቢሆን የማመንዘር ፈቃድ የለውም:: ሊገነዘቡትም የሚገባው ትልቁ ነገር ክርስቲያን በአምላኩ የሚጠየቀው ስለባህሉ ሳይሆን ስለመልካም ሥነ-ምግባሩ መሆኑን ነው:: ምክንያት ሊኖረው ይችላል ምክንያቱ ግን አያድነውም:: ከአዳምና ከሔዋን ምክንያተኝነት የምንማረው ብዙ ነገር አለ:: ምክንያቱ ለራሱ ሕሊና





በቂ ቢሆንም እንኳን ወይም ልጆችን ለማግኘት ካለው ከፍተኛ ፍላጎት ጉጉት በመነሳትም ቢሆን ሚስት ባሏን ወደ አመንዝራነት እንዲሔድ ፈቃድ አይደለችም:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይ አይደለም:: ስለመካንነት መጸለይ ሲገባ አማራጭ ሥጋዊ ጥበቦችን መጠቀም የሃይማኖት የለሽ ሰው ሥራ ነው:: እግዚአብሔር መሀሪ ነው ብሎ ማሰብ መልካም ነገር ሆኖ ሳለ እርሱ ፍጹም ተበቃይና ቀጭ መሆኑን መዘንጋት አለማስተዋል ነው:: አንድ ሰው ሌላን ሰው ቢገድለው ከዚያም ንስሐ ቢገባና ይቅርታ ቢጠይቅ የእርሱ ንስሐና ይቅርታ የሞተውን ሰው አያስነሳውም፣ ምንም አይጠቅመውም:: ለራሱ ይጠቅማል ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል ነገር ግን የሥጋ ቅጣቱን ይቀበላል:: ነብዩ እግዚአብሔር ዳዊት ሥለ ቤርሳቤህ ሲል ኦሪዮንን አስገደለው ከዚያም ተጸጽቶ ንስሐ ገባ እግዚአብሔርም ታረቀው:: ይሁን እንጂ ስላደረገው ነገር ቅጣቱን ተቀብሏል እስራኤል በእግዚአብሔር እጅ ወድቀዋል መንግስቱም አልጸና ብሎት ለሶስት ወር ያህል እየተንከራተተ በገዛ ልጁ ስቃዩን አይቷል:: 2ሳሙ 12:1-13 በኃጢአት የተገኘው ልጅም ከሞት አምልጦ ለምድር በረከት ሊሆን አልቻለም::

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ የደረሰበት የሞራል ኪሳራ ብቻ አይደለም:: ከገነት ተባሮ በምድር በሚኖርበት ጊዜ ክርስቶስ ነፃ እስከሚያወጣው ብዙ አላስፈላጊ የሆኑ የኃጢአት ልምዶችን አካብቷል:: በክርስቶስ የዘለዓለም ነፃነትን ካገኘ በኋላ እንኳን እነዚያ አጉል ልምዶች እያገረሹበት እንደገላቲያ ሰዎች እዚም ተደርጉበት ያዳነውን ጌታ ሳይመለከት በድንግዝግዝ ይጓዛል:: ገላ 5:1፣3:1 :: መመገብ መልካም ነው:: ከመጠን በላይ መመገብ ግን ለኃጢአት የሚያነሳሳ ክፉ ሥራ ነው:: በጋብቻ ውስጥ ሩካቤን መፈጸም መልካም ቅዱስና ንጹህ ነው ከተፈቀደው በላይ ወደሌላ ሔዶ ከትዳር ውጭ ግንኙነት መፈጸም ግን ዝሙት ነው:: ማንኛውም አይነት ፍላጎት በራሱ ኃጢአት አይደለም ኃጢአት የሚሆነው አፈጻጸሙ ከህግና ከሥርዓት የወጣ ከሆነ ነው:: ጾታዊ ፍላጎትም እግዚአብሔር

በመካከል ካስቀመጠው የተፈጥሮ መሳሳብ የተነሳ ይመጣል ያንን ፍላጐት እንዴት አድርጐ ማስተናገድ እንዳለበት እያንዳንዱ በትዳር ወስጥ የሚኖር ሁሉ ማወቅ ያለበት ቁም ነገር ነው።

ሀ - ፍላጐትን በግልፅ ማሳወቅ

የራሱን አካል ለማየት የሚጸየፍ ለመንካትም የሚፈራ ማንም የለም። ባል ሁሉነገሩ የሚስቱ ነው ሚስትም ሁሉ ነገሯ የባሏ ነው። በመሆኑም ሚስት ከባሏ ጋር ሩካቤ የመፈጸም ፍላጐት ሲያድርባት በተለያየ መልኩ ፍላጐቷን ልትገልጽለት ትችላለች። ይህም የሚስትነት መብቷ ነው። በድርጊት በንግግር ወይም በሁኔታዎች ሊሆን ይችላል። ዛሬ ከወትሮው ሁሉ እንዳማረበት፣ ብቻውን አብራው ልትሆን እንደምትፈልግ፣ እንደናፈቃት በማስታወቅ በግልጽ ፍላጐቷን ልትነግረው ይገባል። እንደ ውጭ ሰው ልትፈራው ስሜቷን እየጐዳች ባህሉን ለማክበር ወይም እንዲህ ያለውን ነገር ክርስቲያን ሴት አታደርገውም እያሉ ብቻ በራስ ላይ መጫወት ሃይማኖትን መጠበቅ አይደለም። ስሜት መቼና እንዴት ሊመጣ እንደሚችል አይታወቅም መቼም ይሁን መች በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ፍላጐቷን ማሳየቷ ነውር አይደለም እንደውም እውነተኛ አፍቃሪነቷን ይገልጽላታል። በእንቅልፍ ሰዓት ቢሆንም እንኳን ብትቀሰቅሰውና ስሜቷን እንዲጋራላት ብትጠይቀው አግባብ ነው። እናትና አባቷን ትታ አብራው የምትኖረው እርሱን ነውና ለእርሷ ከእርሱ የተሻለ ከሰው ወገን የሚቀርባት ሥሜቷንም የሚጋራላት ማንም የለም።

የወንድ ፈቃድ ወደ ሚስት እንደሆነ ሁሉ የሴቷም ፈቃድ ወደ ባሏ ይመለሳል። ከወለደችም በኋላ ወደ ተለመደው ሥርዓት ትመለሳለች። ሥሜት ሁልጊዜ በሕይወት እስካሉ መጠኑ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል እንጂ ይቀጥላል። ባልና ሚስትም ሳይተፋፈሩ በግልጽና በታማኝነት ለትዳር አጋሮቻቸው ብቻ ማሳወቃቸውና ለሩካቤ መዘጋጀታቸው ትክክለኛ ነገር እያደረጉ እንደሆነ እርግጠኝነት ሊሰማቸው ይገባል። አንድ ሰው ምግብ በልቶ ቤተክርስቲያን በጸሎት ቅዳሴ የማይገባው መግባት ስለሌለበት ነው። ጊዜውም





የአምልኮ ስለሆነ እንጂ መመገብ ኃጢአት ስለሆነ አይደለም። ሩካቤን ፈጽሞ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳይገባ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የሚከለክለውም ኃጢአት ስለሆነ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲቀረብ የበለጠ ንጹህ ሆኖ መቅረብ ሥለሚገባ፣ ያለምንም የህሊና ወቀሳ ኃፍረት ሳይሰማ እግዚአብሔርን ማገልገል እንዲቻል ነው። በእግዚአብሔር ፊት የከበረውን ነገር ለማከናወን ደግሞ በፊት ለፊት የተቀመጠውን የባህል ግርዶሽ በማንሳት በግልጽ መጠያየቅ ትክክለኛ መንገድ ነው።

ሚስት ባሏ ፍቃዱን ሁሉ እንዲፈጽም ዝግጁ ሆና በፍቅር እንደምታስተናግደውና በዚህም ለባሏ ያላትን መውደድ እንደምትገልጥለት ሁሉ የፈለገችውን ነገር እንዲያደርግላት መጠየቋ ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ እርሱ የእርሷ እንደሆነ እየመሰከረች ነው። በጾታዊ ስሜት መበደል ልቦናን ያሸፍታል። በመነጋገር መፍታት የሚቻለውን ትንሹን ነገር በይሉኝታ በመታሰርና ምንይሉኛል ብሎ መፍራት ትልቅ የልዩነት በር በመክፈት ትዳሩን ወደ መናጋት ይመራል። ከባሏ ጠይቃ ማግኘት የምትችለውን ነገር በፍርሃት ዝም ብላ ራሷን እየጐዳች ካሳለፈችው ባሏ በሚያስፈልገው ጊዜ ብቻ ሥሜቱን ያረካል። ካልነገረችው በስተቀር የእርሷን ፍላጐት አያውቅምና የእርሷ ፍላጐት በአግባቡ ሲያስተናግድላት አይችልም። በዚህ ወቅት የተዋትና የዘነጋት ለእርሷም ስሜት ግድ የሌለው ይመስላታል። ሥጋዊ ፈቃድ በሚነሳበት ጊዜ ታዲያ ፍርሃቱና ሆደ ባሻነቷ ተደማምረው ስለሚያስጨንቋት ከሌሎች ወገን የሚመጣውን የዝሙት ጥያቄ ለማስተናገድ አታንገራግርም። ሴቶች ዝም አሉ ማለት ስሜት የላቸውም ማለት አይደለምና ባሎች ይህንን በመገንዘብ በግልጽ ሊያወያዮዋቸው ያስፈልጋል። ጾታዊ ግንኙነት ሲያስፈልጋቸው የሚያሳዩትን እንቅስቃሴ በማጥናት ሳይጠይቋቸው ቀድመው ሁሉን ነገር ቢረዱአቸው የበለጠ አደረጉ። በሥሜት ለመርካት ብቻ ሳይሆን በትዳር ላይ ታማኝነታቸውን ጠብቆ ለመኖር ሲባል ሚስቶች በነገር ሁሉ ለባሎቻቸው ግልጽ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ለ - ቅድመ ዝግጅት

ባልና ሚስት በሚፈጽሙት ሩካቤ መደሰትና የሥሜት እርካታ ማግኘት አለባቸው፡፡ ከተፈጥሮ አንፃር ግን የሁለቱም ስሜት በአንድ ጊዜ ወደ ስሜት ጣሪያ አይደርስም፡፡ የሁለቱም ስሜት በአንድ ጊዜ ለሩካቤ ዝግጁ አይሆንም ይህንን ልዩነት ለማስተካከል በቀጥታ ወደ ሩካቤው ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

1. <u>በቂ ዕረፍት ማድረግ</u>፡- በሥራ ሲደክም የዋለ ሰውነት በሀሳብ ተወጥሮ የቆየ አዕምሮ ምንም ረፍት ሳያደርግ በቀጥታ ወደ ሩካቤ ቢገባ ግንኙነቱ የተሳካ አይሆንም፡፡ ስለዚህ በጊዜ ወደቤቱ በመግባት ራትን በሰዓቱ ተመግቦ ባልና ሚስት ከልጆችና አብረዋቸው ከሚኖሩ ሌሎች ዘመዶች ተለይተው ለብቻቸው ብመኝታ ክፍላቸው ሥለትዳራቸው ሥለ ፍቅራቸውና ሥለ ውሎአቸው እየተጫዋወቱ ራሳቸውን ዘና ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ የሚረብሻቸው ነገር እንዳይኖር መጣርና እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ሌላ አይነት ሰላምን የሚነሳን የጩኸት ድምጽ ከአቅራቢያቸው ማስወገድ መልካም ነው፡፡ ሕፃናት ልጆች የሚያስፈልጓቸውን ማግኘታቸውንና ቢቻል መተኛታቸውን ማረጋገጥ ቢችሉ የበለጠ የተመቸ ነው፡፡

2. <u>የሚያስፈሩ ነገሮችን ማስወገድ</u>፡- በሩካቤ ሥጋ ወቅት ከጤና ጋር፣ ሩካቤን ራሱን ከመፍራት፣ ጋር ወይም ደግሞ ልጆች መውለድ ካለመፈለግ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ፍርሀቶች አሉ፡፡ አንድ ሰው ሙሉ የአካል ብቃት ሳይኖረው፣ የጤና ችግር እያለበት ወደ ሩካቤ ቢገባ ከሚያገኙት ደስታ ይልቅ ፍርሀቱ ሥለሚያይል ራሱን ከመጉዳት በተጨማሪ የትዳር አጋራቸውን ብስጩና ነጭናጫ እንዲሆኑ ለፍቅራቸው ጥሩ ምላሽ እንዳላገኙ እንዲቆጥሩ ያደርጋል፡፡ የሰዎች አስተዳደግ የተለያየ በመሆኑ አንዳንድ ወጣቶች ሥለሩካቤ ይዘውት የሚመጡት የተለያዩ አስፈሪ አስተያየትና አስደንጋጭ ሥዕል አለ፡፡ ወደ ትዳሩ ከገቡ ሩካቤ አይቀርምና በዚህ ጉዳይ ባልና





ሚስት ሊመካከሩ ከዚያም በላይ የትዳር አማካሪዎችን የቀደሙ ባለትዳሮችን ርዳታ ሊጠይቁ ይገባል፡፡ ልጆችን መውለድ አስፈላጊ ቢሆንም ሰው ምን ያህል መውለድ እንዳለበት የተደነገገ ነገር ስለሌለ ከኑሮውና ከጤናው አንፃር የሚበቃውን ልጅ ራሱ ይወስናል፡፡ አንድ ሰው መውለድ የሚፈልገው ሁለት ልጅ ከሆነ እነርሱንም ከወለደ ከዚያ በኋላ በሚያደርገው ሩካቤ ሁሉ እንደሰጋ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የምታስተምረውንና ተፈጥሮ የለገሰችውን ወሊድ የመከላከያ መንገድ በመጠኑም በተቻለ መጠን ችግሩን ለመፍታት መሞከር በሩካቤ ውስጥ የሚፈጠረውን ፍርሃት በመጠኑም ቢሆን ይቀንሰዋል፡፡

3. <u>ሙሉ በሙሉ ዝግጁ መሆን</u>፡- ራስን ገዝቶ መግባባት ያለበት ሩካቤን ለማከናወን የመጨረሻው ክንውን ሥሜት ቀስቃሽ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ ነው፡፡ መሳሳም፣ መነካካት፣ የፍቅር ጨዋታን መጫወት፣ እርስ በራሳቸው አድናቆት መለጋገስና በሩካቤ የሚያገኙት ደስታ ማሰላሰል ለሩካቤው ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚፈጽም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተሳካና መግባባት ያለበት ነው ተብሎ በአብዛኛው ይታመናል፡፡

ሐ- የሥሜት መጠባበቅ

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የአዕምሮና የመንፈስ እርካታ መስጠቱ አሌ የማይባል ሀቅ ነው፡፡ ባለትዳሮች በግንኙነታቸው ወቅት እኩል ያለመርካት ችግር እንዳይፈጠርባቸው አንዳቸው ለሌላው ስሜት መጨነቅና መጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ በራስ ወዳድነት የራስን ሥሜት ብቻ መጠበቅ የሌላውን ደስታ ስለሚያስቀር እርስ በራሳቸው ሊግባቡና አንዱ የአንዱን ሥሜት ሊንከባከብለት ያስፈልጋል፡፡ አልፎ አልፎ ጋብቻ ወደፍቺ ከሚያመራበት ምክንያት አንዱ በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ የሥሜት አለመጣጣም ነው፡፡ በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ እርካታ ሳያገኝ የቀረው ወገን እንደ እቃ የተቆጠረና ለሌላው ስሜት ማርኪያ

የተፈጠረ መስሎ ስለሚሰማው በትዳሩ ደስተኛ አይሆንም። ሆደባሻና በትንሽ በትልቁ ንዝንዝ የሚያበዛ ትዳሩን የሚያቋርጥበትን መንገድ የሚፈልግ ይሆናል። ከትዳሩ ማግኘት ያለበትን ደስታ ያጣው በትዳር አጋሩ ግዴለሽነት እንደሆነ ስለሚያስብ የድብቅ ወሲብ /ዝሙት/ ለመፈጸም ሌላ አፍቃሪ ይፈልጋል።

ተፈጥሮ ራሱ በወንዶችና በሴቶች መካከል የወሲብ ፍላጎት መነሳሳትና መርካት በእኩል ሰዓት እንዲሆን አላደረገም ነገር ግን ባልና ሚስት ይህንን ልዩነት አንዱ ለአንዱ ባለው ከፍተኛ ፍቅርና ልዩ ስሜት ማመጣጠን ይችላሉ። ወንድ በማየት፣ በመስማት፣ በማሽተትና፣ በማንበብ ስሜቱ ይቀሰቀሳል። ሴት ደግሞ አካላዊ ንክኪ እስከሌለ ድረስ በአብዛኛው ስሜቷ አይቀሰቀስም። በአንጻሩ የወንድ ስሜት መጨረሻ ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችለው የወንዴ ዘሩ ከእርሱ የሚከፈለው በአጭር ጊዜ ሲሆን ሴቷ ግን የስሜት እርካታን የምታገኘው ከሌላው የሰውነት ክፍሏ ጋር በተያያዘ መልኩ ስለሆነ ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል። በሴቷ አካል ላይ ያሉ እጢዎች በግንኙነት ጊዜ ይወጠራሉ ከዚያም ወደ መጨረሻ ደረጃ ስትደርስ እየተኮማተሩ ይመጡና ከውስጣቸው ፈሳሽ ያመነጫሉ አፈ ማህጸኗ እየጠበበ ይመጣና ከወንዱ አካል ጋር ይጣበቃል በዚህ ጊዜ ሥሜቷ ይረካል ደስታንም ታገኛለች። ይህ ክንውን በቅደም ተከተል እስኪፈጸም ድረስ ባሎች የሚስቶቻቸውን እንቅስቃሴ በማጤን በሥጋዊ ግንኙነታቸው ደስተኞች እንዲሆኑ ሊረዷቸው ይገባል። መረዳዳት በሥራና በሀሳብ ብቻ ሳይሆን በሩካቤም ይገለፃል። በመሆኑም ወንዶች አጭር በሆነ ትጽበት የራሳቸውን ደስታ አግኝተው ሚስቶቻቸውን ከተቀቻቸው ያበሳጯቸዋል። ወንዶች በፍጥነት ወደ እርካታ ከደረሱ የሚስቶቻቸውን ስሜት ለመጠበቅ የሚያስችል የአካልም ሆነ የአዕምሮ ብቃት አይኖራቸውም ፍላጎታቸው ይቀንሳል ስለዚህ ትክክለኛው መፍትሔ እንቅስቃሴያቸውን በመቆጣጠር ስለሚስቶቻቸው ሲሉ ራሳቸውን በመግዛት ሴቷ እነርሱ እደረሱበት ደረጃ እስክትደርስ መጠበቅ ነው።





መ - ራስን አሳልፎ መስጠት

ሴት ልጅ እራሷን ሙሉ በሙሉ አሳልፋ የምትሰጠው በነፃ ሕሊናም የምትቀርበው ባሏ እንደሚያፈቅራትና እንደሚጠነቀቅላት 100% እርግጠኛ ሥትሆን ብቻ ነው። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ በትዳራቸው ደስተኛ ያልሆኑ ሚስቶች ባሎቻቸውን ሩካቤ በመከልከል የሚበቀሉበትና የሚያሰቃዩበት ሁኔታ ይስተዋላል ይህ ከመሰረታዊው የክርስትና ትምህርት ፈጽሞ የራቀ ነው። "ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት እንዲሁም ደግሞ ሚስት ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጅ። እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ስልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜውካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ራሳችሁን ስላለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ" 1ኛ ቆሮ 7:3-5 ፍቅር ማለት እስከ ሞት ድረስ መታመን ማለት ስለሆነ ሚስት ስለባሏ ባልም ስለሚስቱ ሲል ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍሲንም አሳልፎ መስጠት ቢያስፈልግ ይህንኑ በማድረግ ፍቅራቸውን ሊያፀኑ የተገባ ነው።

ሚስት ለባሏ ፍላጎቱን ልትፈጽምለት ስሜቱንም ሳትጎዳ ልትንከባከበው ይገባታል። ባልም ቢሆን የሚስቱን ፍላጎት መፈጸም ግዴታው እንደሆነ ማወቅ አለበት። ለጸሎት ወይም በሌላ መንፈሳዊ ምክንያት ሩካቤን ለተወሰነ ጊዜ ሲያቆሙ ተስማምተውበትና ሁለቱም አምነውበት መሆን አለበት። እዚህ እቤት ተለያይተው ቤተክርስቲያን ጸሎት ለማድረግ መሞከር ከንቱ ልፋት ነው። መባዕ ከማቅረብህ በፊት ወንድምህን በመጀመሪያ ይቅርታ ጠይቀው የተባለው ያለፍቅር ሁሉ ከንቱ ስለሆነ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ባልም ሆነ ሚስት ያለባቸውን የጤና ችግር በመነጋገር ለተወሰነ ጊዜ ሩካቤ ሊታቀቡ ይችላሉ። ነገር ግን ክርስትናን፣ መንፈሳዊነትን፣ ጸሎትን ፃመምን ምክንያት በማድረግ ራስን ማግለልና የትዳር ጓደኛን መጉዳት የጋብቻን ቃል ኪዳን እንደ ማፍረስ ይቆጠራል። ሚስት ለባሏ ባልም ለሚስቱ

ራሱን አሳልፎ የማይሰጥና የሚከላከሉ ከሆነ አለመጋባቱ የተሻለ ነው። ለርሱ የእርሷን በፍቅር የምትኖርበትን ሌላ እድል ማበላሸት የለበትም። እርሷም እንዲሁ። ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያለው ታሪክ በዘፍ 38 ላይ እንመለከታለን በዚሁ ምዕራፍ ላይ ክፉ ነገር ስላደረገ ስሜቱን እያረካ ዘሩን በውጭ ስለሚያፈስና ለወንድሙም ዘር እንዳይተካ ምቀኛ ስለሆነ እግዚአብሔርም እንደ ቀሰፈው እንገነዘባለን።

በትዳር ውስጥ ሩካቤ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጠው የኑሮ ክፍል ነው። ከሩካቤም በፊት ይሁን ከሩካቤ በኋላ የሚሰማት ህመም ካለ ወይም ደግሞ ለግንኙነታቸው ተስማሚ ነው ብላ የምታምነው አማራጭ ሀሳብ ካላት በድፍረት ሚስት ለባሏ ልታስረዳው ትችላለች። በደንብ ሊወዳትና ሊያፈቅራት በሩካቤም ልታስደስተው የምትችለው በምን አይነት መልኩ እንደሆነ ባል ለሚስቱ ቢገልጥላት ለእርሷ ያለውን ጥልቅ ሥሜት ያስረዳል ይልቁንም በሥህተታቸው ተራርቀው አብረው እስከ ሕይወት ፍፃሜያቸው ሊያኖሯቸው የሚችል ጥምረትን ይፈጥርላቸዋል። የተሻለ ነገር ለማግኘት አማራጭ ከመፈለግ ይልቅ ራስን የተሻሉና ብቁ አድርጐ ለማቅረብ መጣር ከቻሉ ያላቸውን ታማኝነት ከመግለጡም በላይ ለወደፊት እንዴት ብለው ተጣጥመው መኖር እንደሚችሉ መላ ያገኙበታል። በመጨረሻም በሩካቤያቸው ወቅት ስለነበረው ሁኔታ መወያየት እግዚአብሔርን ስለሰጣቸው" ደስታ ማመስገንና እርስ በራሳቸው አንዱ ለአንዱ ያላቸውን ፍቅር መግለጥ የሁሉ ነገር ማሰሪያ ነው..

2. ቤተሰባዊ ሕይወት

ከጋብቻ በፊት ባልና ሚስት እንደፈለጉ የመሆን ነፃነት አላቸው፡ ማንም በእያንዳንዳቸው ላይ ሥልጣን አልነበረውም ነበር። ሶስት ጉልቻ ከመሰረቱ በኋላ ግን ሁለቱም ከትዳር ህግ በታች ስለሚሆኑ እነርሱ እንደፈቀዱት ሳይሆን ትዳራቸው እንደፈቀደው መኖር ግድ ይላቸዋል። ጋብቻን ተከትለው የሚመጡ ኃላፊነቶችና ተጽዕኖዎች ስላሉ እነዚህን በአግባቡ ለመወጣት የአዕምሮ፣ የሞራልና የማቴሪያል ዝግጅት አስፈላጊ ነው። ቤተሰባዊ ሕይወት አስደሳችና አጓጊ የመሆኑን ያህል





ኑሮን በአግባብ መምራት ካልተቻለ የዚያኑ ያህል አስቸጋሪ ይሆናል። የተጠበቀውን ያህል እርስ በእርስ መዋሀድ ከጋብቻ በኋላ በሚፈለገው ፍጥነት አይመጣም። የጉላ የሀሳብ ልዩነቶች፣ የምርጫ ልዩነቶችና በቤት ውስጥ ባልና ሚስት ድርሻቸውን አለማወቅ የቤቱ የበላይ ለመሆን የሚገጥሙት እስጥ አገባ ትልቁ ውጥረት ነው። ሁለቱም የየራሳቸው አመለካከት ስለሚኖራቸው ይህንንም በትዳራቸው ውስጥ መተግበር ከፈለጉ ውጥረቱ ሊቀጥል ይችላል። ሥር ሰዶ ቅርንጫፍ እስኪያወጣ ለቁጣ ፈንታ ከሰጡት ደግሞ "የትይደርሳል የተባለው.... " እንደሚባለው ሊሆን ይችላል።

ሁለቱም የሚጋጩበትን የሀሳብ ልዩነት በማጥበብ ለጋራ ጥቅማቸው ነገራቸውን በማቀናጀት ወደ አንድነት መቅረብ አለባቸው። በትዳር ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር እንደሚጣሉትና ወዲያው እንደሚታረቁት ባለመስማማታቸው ጊዜ ቀላል ነገር ይገጥመናል ብሎ ማሰብ ደግሞ ሌላኛው ስህተት ነው። ግጭት ሲፈጠር ጥፋተኛ ጥፋተኝነቱን በማመን በቀስታ ድምጽ ማንም ሰው ሳይሰማ ሰላም ማውረድና ለትዳር ታማኝነትን በይቅርታ ማረጋገጥ የክርስቲያን የታረመ ሥነምግባር ነው። ይቅርታ የሚጠይቀውም ይቅርታ የሚያደርገውም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኛሉ። የዚህ አይነቱ መተሳሰብ በትዳር አብሮ ለመኖር ወሳኙ ነጥብ ነው። ለምን ግጭት ይፈጠራል? ጥልስ ለምን ተነሳ? ብሎ መከራከሪያ ነጥብ የሚያነሳ ማንም አይኖርም- ዋናው ነገር አለመግባባትን በውይይት መፍታትና ቂምን ማስወገድ ነው። ችግርን አፍነው ቢይዙት ግን በብስጭት እየተብሰለሰሉ በራስ ምታትና በደምብዛት መሰቃየት ለበቀል መዘጋጀት በመጨረሻም ትዳርን ፍች በሚባለው መቀስ ቆርጦ መጣል ነው።

ሀ. ባልና ሚስት

በባልና ሚስት መካከል ያለውን ውህደት በቤተክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ካለው አንድነት ጋር በማነፃጸር ቅዱስ ጳውሎስ ፍጹም አንድነቱን ያትታል። "እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሀት



www.ethiopianorthodox.org

የተገዛችሁ ሁኑ:: ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባልም የሚስቱ ራስ ነው:: ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ይገዙ:: "ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ......" ኤፌ 5:21-33 ይህ ምስጢር ታላቅ ነውና ክርስቲያናዊ ጋብቻ ምን ያህል ቅዱስና ንጹህ እንደሆነ መረዳት ተገቢ ነው:: ቤተክርስቲያንንም ክርስቶስንም መምሰል የሚያክል ድንቅ ጥበብ የለም:: በአምላክ ፊት ራሳቸውን በጸሎት በማስተሳሰር ሁለትም ሶስትም በስሙ በተሰባሰቡበት የሚገኝ ጌታ በትዳራቸው እንዲገኝ ጋብቻ የእግዚአብሔር ልዩ ሥጦታ ነውና እያንዳንዱ አካል በትዳሩ ውስጥ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በመወጣት የትዳሩ ዘላቂነት ያለነቀፋ እንዲቀጥል መጣር አለበት::

<u>የባል ኃላፊነቶች</u>

1. ሚስቱን መውደድ ይጠበቅበታል:: ይህም ከላይ እንደተጠቀሰው ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ራሱንም አሳልፎ እንደሰጣት ባልም ሚስቱን የሕይወት መስዋዕትነት እስከ መክፈል ሊወዳት ቤተክርስቲያን ወንዶች ለሚስቶቻቸው ልዩ እንክብካቤ እንዲያደርጉ ከእነርሱም እኩል እንደሆኑ እንዲያስቡ አበክራ ታስተምራለች በመካከላቸውም ምንም ተፈጥሮዓዊ የሆነ ልዩነት የለም:: ባርያም የለ ጌታም የለ ሴትም የለ ወንድም የለ ሁሉም በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነው::ስለዚህ ባል ራሱን በመካድ የእርሱ ማንነት መገለጫ ሚስቱ እንደሆነች አምኖ መቀበል አለበት::
2. ሚስቱን ማክበር አለበት:: " እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ...... ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል ከብራችሁ ኑሩ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል ደግሞ አብረዋችሁ የሕይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሯቸው:: 1ኛ ጴጥ 3:7





"ባለቤት ያቃለለውን አሞሌ በእዳ አይሸከመውም" ሚስቱን ቢያከብራት ተከብራ ታስከብረዋለች፣ ቢንቃትና ቢያዋርዳት ግን ተዋርዳ ታዋርደዋለች ለሚስት ትልቅ ክብር መስጠት የተስተካከለ የትዳር ቁልፍ ማግኘት ነው::

3. ለቤተሰቡ አስፈላጊውን ማሟላት አለበት:: አንዳንድ ባሎች ትዳር እንኳን እንዳላቸው በመርሳት ሲጠጡና ሲጨፍሩ አምሽተው የጠርሙስ ጓደኛ በመሆን ወደቤታቸው ይመለሳሉ:: በስካርና በቁማር ገንዘባቸውን ጨርሰው ራሳቸውን ከመጉዳታቸውም ሌላ ባለቤታቸውን ልጆቻቸው ለአደጋ ያጋልጣሉ:: በአጠቃላይ ቤተሰባዊ ሕይወት ይበጠበጣል:: ይህ ከክህደት የማይተናነስ ኃጢአት በመሆኑ ባሎች ከዚህ ሱስ ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው:: "ነገር ግን የእርሱ ስለሆኑ ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የከፋ ነው" 1ኛ ጢሞ 5:8
4. ልጆቹን ሥርዓት ማስያዝ አለበት:: ሕፃን ልጅ በቤት ውስጥ የሚያድገው በሚገባው ቋንቋ እየተነገረው ነው:: ምክር፣ ቁጣና ቅጣት ሊያስተምር በሚችል መልኩ ሊፈጸሙ ይችላሉ:: አንዳንድ አባቶች እናት ልጇን ሥርዓት ለማስያዝ ስትነሳ ጣልቃ በመግባት ልጅ ያለልጓም መረን ተለቆ እንዲያድግ ያደርጋሉ:: በዚህም ልጆችም አባታቸውን እንደሚያፈቅሩ ይናገራሉ:: ለምን እንዲህ እንዳደረጉ ሲጠየቁ መልሳቸው አባዬ አንድ ቀንም ነክቶኝ አያውቅም የሚል ይሆናል :: በእናትና በልጅ መካከል ቅራኔ ከመፈጠሩም በላይ በባልና በሚስት መካከል ልዩነት ያስከትላል:: ልጆችን በሥርዓት የማሳደግ ኃላፊነት ባሎችም ስላለባቸው ልጆቻቸውን ሳያስቀጡ ሥርዓት ማስያዝ አለባቸው:: "እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳጽ አሳድጓቸው እንጂ <u>አታስቆጧቸው</u>"

ኤፌ 6:4

5. ውሳኔ ማሳለፍ አለበት፡- በትዳራቸው ውስጥ ውሳኔ የጋራቸው ነው አንዳንድ ጊዜ ግን ሁለቱ ሊስማሙበት ያልቻሉት ነገር ቢፈጠር ሌላ ትርጉም ሳይሰጠው ለትዳራቸው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ይጠቅማል ብለው ያመኑበትን ሀሳብ በማስረዳት አሳማኝ በሆነ ምክንያት ውሳኔ ማሳለፍ ይችላል በሕይወቷ ላይ ጌታዋ እንዲሆን ሚስቱ ፈቅዳለታለችና ይህንን መብቱን በመጠቀምም ውሳኔውን ማሳወቅ እንዲፈጸምም ማድረግ አምባ ገነን መሆን አይደለም።

የሚስት ኃላፊነቶች

1. ለባሎቻቸው መጸለይ አለባቸው፡- በሰላም ወጥቶ እንዲገባ የማገኛዋም ሚስት ለባሏ ያላት በጎ ፍላጐት ነው። ይህን መልካም ምኞቷን በጸሎትና በምልጃ ወደ እግዚአብሔር እያቀረበች ሥለ ትዳራቸው ስምረት ዘወትር መጸለይ ከአስተዋይ ሚስት ይጠበቃል። በብዙ ሥራና ድካም ባሏ ለጸሎት መትጋት የማይችል ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ይህን ኃላፊነት በመውሰድ ወደፊትና እንዳይገቡ አጥብቃ ብትጸልይ መልካም አደረገች።

2. ባሎቻቸውን መውደድ አለባቸው፡-መዋደድ በመካከላቸው ሳይኖር ወደትዳር እንደማይገቡ የተረጋገጠ ነው። ከትዳር በኋላም ይህ መዋደድና መፈቀር እስከ ወዲያኛው መቀጠል አለበት "ቆነጃጅት የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ ባሎቻቸውን የሚወዱ፣ ልጆቻቸውን የሚወዱ፣ ራሳቸውን የሚገዙ ንጹሆች ለቤት የሚሰሩ በጎ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ ይሁኑ" ቲቶ 2:5

3. እኩልነቷን በሥራ ማረጋገጥ አለባት። እግዚአብሔር ሴትን በማንኛውም ነገር ከወንድ አሳንሶ አልፈጠራትም። እኩል ሕይወት ሥሜት ፣ፍቅርና ለሰው አስፈላጊ የሆነውን ነገር





ሁሉ እንደወንድ አጐናጽፏታል። ይህንን እግዚአብሔር የሰጣትን ፀጋ በክብር ይዛ የምትቆየው በመፎከርና በፖለቲካዊ አስተሳሰብ ሴት ከወንድ እኩል ናት በማለት ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ አስተሳሰብ በቤትና በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ወንድ በሚገባት ቦታ በሥራ ቀጥተኛ ተሳታፊ ስትሆን ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ፀጋ በተግባር ስትተረጉመው ነው። "ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ ......." ገላ 3:28

4. ባሏን ልትረዳው ይገባል፡- በተለያየ መልኩ ባሏን መረዳትና መንከባከብ ከሚስት ይፈለጋል። ከድካሙ እንዲያርፍ ከብስጭቱ እንዲበርድ፣ከከፋ ውሳኔው እንዲመለስ፣ በቀለኝነትን እንዲተው ለእርሱ የተሰጠች አንድና ብቸኛ አጋሩ ናትና በፍቅሯ ሕይወቱን ልትጠብቅለት ያሻል። በቤት ውስጥ እንደጣፋጭ ወይን፣ እንደሚያምር ወይራ፣ እንደሚያፈራም ለውዝ ሆና ለባሏ በመታየት ድካሙን ሁሉ አውልቃ ልትጥልለት ትችላለች። ቤቱን የሚወድ ሚስቱን የሚያፈቅር ልጆቹን የሚናፍቅ ሃይማኖተኛ ይሆን ዘንድ ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረግ የእርሷ ድርሻ ነው።

5. ልጆቿን መንከባከብ ቤተሰቡንም መምራት አለባት። ሴት ልጅ ተፈጥሮ ያደለቻትን ልዩ የእናትነት ፀጋ በትዳር ውስጥ ታገኘዋለች። በእርግጥም በዚህ ምድር ላይ ለእንስሳትም፣ ለአራዊትም ቢሆን እናትቶቻቸው የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታዎች ናቸው "እናት" ከሚለው ስም የበለጠ የሚያምርና የሚጣፍጥ ስምም በዓለም ላይ የለም። ልጆች ከእናቶቻቸው ጋር ያላቸው ፍቅር በማህፀን ይጀመራል ጡታቸውን እየጠቡ ያድጋሉ የእናት እንክብካቤው ፍቅር በተመላበት ሁኔታ እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ይቀጥላል። በመሆኑም አንዲት እናት ልጆቿን ፍቅር እየሰጠች ማሳደግና መልካም ዜጋ ማድረግ፣ ቤተሰቡንም የመምራት ኃላፊነት ከእግዚአብሔርና ከትዳሯ

የቀበሪከተላት ገፀበረከት መሆኑን አምና በመቀበል ለዘወትር ልትጠብቀው ይገባል።

6. ራሷን መጠበቅ አለባት። ብዙ ግዜ ሴቶች ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ የሥራ ጫናና ኃላፊነት ስለሚደራረብባቸው ራሳቸውን ጣል ጣል ማድረግ ያበዛሉ። በተለይ ከወለዱ በኋላ ሌላ ሰው እስከሚመስሉ ድረስ ይጎሳቆላሉ። ይህ ደግሞ የወንዱ ልብ ከቤት እንዲሸሽ መንገድ ነውና ሚስቶች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። እንደሚገባ መዋብና መሽለም ማጌጥ ንጽህናቸውን መጠበቅ ሰውነታቸውንና ፀጉራቸውን መንከባከብ የግድ ነው። ሁልጊዜ ተፈቃሪ ሆነው ለመዝለቅ በባሎቻቸው ፊት በተቻለ መጠን ቆንጆ ሆኖ መታየት ያስፈልጋቸዋል።

## ሰ. ልጆችና ወላጆች

አዲሱ ትውልድ የሀገር፣ የሃይማኖትና የቤተክርስቲያን ተረካቢ ነው። ታሪካዊት ሀገርን፣ የጸናች ሃይማኖትንና በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ቤተክርስቲያንን መጠበቅና ከአባቶቻቸው እንደተማሩት ለልጆቻቸው የማስተማርና የማስተላለፍ ኃላፊነት ወላጆች አለባቸው። በለጋ የሚጠብቅ ፍሬዋን ይበላታል ተብሎ እንደተፃፈው መልካም ፍሬ ለማግኘት መልካም ዘር መዝራት ያስፈልጋል። እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ መጠበቅ ያላስቀመጡትንና ያለፉበትን ለመንጠቅ መፈለግ ነው።

ልጆች በእግዚአብሔር ፊት የተወደዱና የተፈቀሩ መሆናቸው በተለያዩ ቅዱሳት መጽሐፍት ይልቁንም በታላቁ መጽሐፍ በልዩ ልዩ ምዕራፍና ቁጥር ተገልጦ እናነባለን። ሕፃናትን መጠበቅና መንከባከብ ለእግዚአብሔር አደራ ታማኝነትን ማረጋገጥ ነው። ምክንያቱም ወላጅ ልጆቹን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ለእርሱ እንዲያገለግሉት፣ እንዲደሰትበትና እንዲወርሰው ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን መምራት እስኪችሉ እንዲጠብቃቸውም ጭምር ከአደራ ጋር ነው። እንደዚሁም ሁሉ ቤተክርስቲያንም፣ ብትሆን ልጆቹን የመውለድ ብቻ ሳይሆን





የማሳደግም ኃላፊነት አለባት። እግዚአብሔር ሕፃናትን ውብና የሚወደዱ አድርጎ የፈጠራቸው በልጆች ላይ እጅግ በጣም ብዙ ልዩ ልዩ ዓላማ ስላለው ነው። ይህ የእግዚአብሔር ዓላማ ለሀገርም፣ ለቤተክርስቲያንም፣ ለወላጅም ዘርፈ ብዙ ጥቅምን ያስገኛል። በመሆኑም ሕፃናትን መንከባከብ ወጣቶችንም የሕይወት አቅጣጫቸው እንዳይበላሽ ማገዝ የእግዚአብሔር በጎ ዓላማ ግቡን እንዲመታ መተባበር ነው።

ስለ ጌታችንና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እድገት የተፃፈውን ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስንመረምር እንዲህ በሚል የተዋበ አገላለጽ ያንን ዘመን ያስታውሰናል። "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ያድግ ነበር" ሉቃ 2:52 በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት የበለጸጉ ህፃናት በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት በሞገስ ያድጋሉ። ለህፃናት ዳቦ፣ ልብስና መጫወቻ ብቻ አይደለም የሚያስፈልጋቸው። ፍቅር፣እንክብካቤ፣ ትምህርት፣በቁመት ከማደግ ጋር በአዕምሮ ማደግ፣ በሥጋ ከመግዘፍ ጋ በጥበብ መጥለቅ በታረመ ጸባይና በመልካም ሥነ ምግባር ሰውን የሚያከብሩ እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሆን ያስፈልጋቸዋል። በእርግጥም መሆን ያስፈልጋቸዋል። መስተዋል ያለበት አብይ ቁም ነገር የልጆች ባህሪ በአብዛኛው የሚወሰነው በቤት ውስጥ አስተዳደጋቸውና ከማህበረሰቡ በወረሱት ልምድ ላይ ተመስርቶ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም በትምህርትም በቅጣትም የማይስተካከል አጉል ግልፍተኛና እልከኛ የሚሆኑት መጀመሪያ ላይ ነገሩ ስለተበላሸ ነው።

ከሁሉም በፊት ልጆች ደስተኛ መሆንን ይመርጣሉ ስለነገም ምንም አይጨነቁም ነገ የአስር ብር ጫማ እገዛልሀለሁ ከምትለው ዛሬ የአምስት ሳንቲም ከረሜላ ብትገዛለት ደስተኛ ይሆናል። የበለጠ ደስተኛ የሚሆኑት ደግሞ ወላጆቻቸው በፍቅር የሚኖሩ ከሆነ ነው። ሰላም ባለበት ቤት ያደገ ሕፃን ሰላማዊነው። እናትና አባት ሲደባደቡ በኖሩበት ቤት የተወለደ ልጅ ግን ከእልከኛነቱ የተነሳ ለጉረቤት አስቸጋሪ ለቤት የጉን ውጋት ይሆናል። ይህንን ኃላፊነት አባትም እናትም እኩል

መሸከም አለባቸው:: አንዱ ለአንዱ ሊተወውና እኔ የለሁበትም ብሎ ሊዘነጋው የሚገባ ነገር አይደለም:: በምትፈልጉት የአስተዳዳግ መንገድ ልጆቻችሁን መቅረጽ ከፈለጋችሁ መጀመሪያ እናንተ ሰላማዊያን ሁኑ:: ከዚያም ለልጆቻችሁ የደስታ ምንጭ ስለምትሆኑ የምትፈልጉትን አይነት ለውጥ ማምጣት ትችላላችሁ::

በቤተክርስቲያን በሚዘጋጅ ልዩ ልዩ የህፃናት መርሀ ግብር ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ምግብ ስትመገቡ፣ ስትተኙ፣ ስትወጡና ስትገቡ እግዚአብሔር እንዴት እንደምታመሰግኑ ማሳየት፣ በክብረ በአላት ቀን ወደ ቤተክርስቲያን በመውሰድ ዐበል እንዲበጡ፣ ሥጋ ወደሙ እንዲቀበሉ መጣር ህፃናቱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል:: ጉበዝና ተፎካካሪ ተማሪ ይሆኑ ዘንድ የሚቻላችሁን ያህል ብታደርጉላቸው ባረ ቀባሪ ከመሆን አልፈው የሕይወታቸው ልዩ ባለውለታ አድርገው ስለሚቆጥሯችሁ ለእናንተ ተመልሰው እናትና አባት ይሆኑላችኋል:: በአሁኑ ወቅት ምነው እናቴ"በእንቁላሉ በቀጣሽኝ" እያለ ወላጅን የሚረግም ትውልድ የበዛው የሚያስፈልገውን እንክብካቤ አግኝቶ የተሻለ ሰው እንዲሆን ወላጆቹ ስላልረዱት ነው::

ልጆችን መንከባከብ ጊዜ ሲገኝ የሚሠራ ሳይገኝ የሚተው "ባጣቆየኝ" ነገር አይደለም:: አንዳንድ ወላጆች ሁሉን ነገር ወደ ሥራቸው በማድረግ ልጆቻቸውን ወልደው የመጣል ያህል ለሞግዚት ሰጥተው ኑሮዋቸውን ይመራሉ:: መጨረሻው ግን ጥፋት ነው:: ከወላጆቹ ፍቅር አግኝቶ ያላደገ ልጅ ለማንም ፍቅር አይኖረውም ፍቅር አግኝቶ አላደገማ:: ወላጆቹም ወላጆች ስለማይመስሉ በእርሱ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጥፋት አይጨነቁም:: ሕፃናትን መከርኘ ቀጥቶ ማሳደግ ለሀገርም ቢሆን ታላቅ ስጦታ ማበርከት ነው፡ አጭያሽ፣ጠጪ፣ማጅራት መች፣ በእደንዛዥ እፅ የተለከፈ፣ ብኩን ሆኖ የሚኖረው ወጣት ሀገሪቱን የሞላት ኃላፊነት የጐደለው ቤተሰብ ስለበዛ፣ ሳይዘጋጁ ልጆችን ስለሚወልድና በእድሉ ይደግ ብሉ ስለሚተወው ነው:: "ስንፍና በሕፃን ልብ ታስሮዋል የተግሳጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቃታል:: ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል በብትር





ብትመታው አይሞትምና:: በበትር ትመታዋለህ ነፍሱንም ትታደጋለህ" ምሳ 22:15

ከስህተታቸው እንዲታረሙ የተቀጡበትን ምክንያት በግልጽ ማሳወቅ ያስፈልጋል ዝም ብሎ መደብደብ ፋይዳ የለውም ጥፋቱንም ካላወቀ አይሻሻልም:: ጥፋቱ ካልተነገረው ከጥላቻ የተነሳ የተቀጣ ስለሚመስለው ቂመኛና እልከኛም ያደርገዋል:: ከስህተቱ ቢታረም ሁለተኛ እንደማይገረፍ ጨምሮ ማስረዳት ተገቢ ነው:: ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ወደ ቀደሞው የተለመደ አኗኗር መመለስ መዘንጋት የለበትም ኩርፊያ በፍጹም አያስፈልግም:: ልጆችን በምግብ መቅጣት ታላቅ ስህተት ነው:: ለጨንገራ በሽታ ለትርፍ አንጀትና ለሌላም አደጋ ያጋልጣቸዋል:: እናት ወይም አባት ልጅን ሲቀጡ አንደኛው ወገን ጣልቃ ለመግባት መሞከር ሁሉንም ነገር ማበላሸት ነው::

"የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" ምሳ 1:7 የጥበበኞችን ጥበብ መና ያደረገውን ይህንን ጥበብ ለልጆች ማስተማር በምድር ላይ ያለውን የመጨረሻውን እውቀት ማሳወቅ ነው:: እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ይቀምሱት ዘንድ እርሱንም ብቻ ተስፋ እንዲያደርጉ በሕይወታቸው ዘመን የተደረገላቸውን የእግዚአብሔር በጎ ስጦታዎች በማስታወስ ወላጆች ለልጆቻቸው ሊነግሯቸው ይገባል:: እግዚአብሔርን መፈራትን ገንዘብ አድርገው ካደጉ መንገዳቸው የቀና፣ ሥራቸው የተሠራ፣ ብርሃናቸው የበራ፣ ኑሮአቸው ሰላማዊ፣ ሕይወታቸው ጣፋጭ ይሆንላቸዋል::

## ከፁሉ ጋር በሰላም መኖር

ተፈጥሮ እራሷ በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተች ናት:: ሰው ብቻውን መኖር ቢያስብ እንኳን አይችልም የእግዚአብሔርም ቃል እንደሚያስረዳው ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም:: "ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻውን ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል" መክ 4፤4 በአዕምሮ የሚጉለምሰው፣ በሀዘኑ ጊዜ የሚጽናናው፣ በደስታው ጊዜ ሐሴት የሚያደርገው ከሰዎች ጋር በሚኖረው መልካም ማህበራዊ ግንኙ ነት ነው:: በዚህ ወቅት ታዲያ

ብርሃን ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን ቢቻል ከሁሉም ጋር በሰላም መኖር መልካም ነው። ከሁሉ ጋር ላይቻል ይችላል የሚቻለውን ማድረግ ግን ሰላም ወዳድነት ነው። "የሚያሳድዷችሁን መርቁ እንጂ አትርገሙ፣ ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፣ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ። እርስ በርሳችሁ በአንድ ሀሳብ ተስማሙ፣ የትዕቢትን ነገር አታስቡ ነገር ግን የትህትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ ለማንም ስለክፉ ፋንታ ክፉን አትመልሱ። በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ ቢቻላችሁ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ሮሜ 12፣14-18 ። "ጠላት እንዳይኖርህ ከፈለክ ማንንም አትብለጥ" ይባላል። በኑሮ ውስጥ ደግሞ መቀዳደምና የስኬት ልዩነት ይኖራል። ጠላት ላለማፍራት ሲባል ብቻ እጅና እግር አጣጥፎ ተቀምጦ በርሃብ መሞት ያስፈልጋል ማለት አይደለም። የተሻለ የኑሮ ስኬትን ስታገኝ ሌሎች በጠላትነት ይነሱብሀል እንዳይነሱብህ ካሰብክ አለመስራት ብቻ ነው ይህ ደግሞ ፈጽሞ አይቻልም። ስለዚህ በአንተ ላይ ብዙነገር ቢባል እንኳን አትጨነቅ አንተ ግን ስለ እነርሱ ምንም ስላላልክ ደስ ይበልህ "ጠላትን የማሸነፊያው ትልቁ መሳሪያ ወዳጅ ማድረግ ነው" ምን አልባት ልትቃወመው ልታሸንፈው የምትችልበት ሌሎች አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ ትክክለኛው መፍትሔ ግን በእግዚአብሔር ሰላም ከሁሉ ጋር መኖር ነው ጠላትህን ብታሸንፈው ታሳፍረዋህ ወዳጅ ብታደርገው ግን ፈጽሞ ትገለዋለህ ድል ካደረከው ጊዜ ሲያገኝ አንተን መልሶ ሊያጠቃህ የሚችልበት አጋጣሚ ሲፈጠርለት እንደገና ሊያሸንፍህ ይፈልጋል ወዳጅ ካደረከው ግን ከዚያ ወዲያ ካንተ ጋር ምንም አይኖረውም። የኤልሳዕን የሶሪያ ንጉስና የሰማሪያውን ንጉስ ታሪክ የሚያትተው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህንን ነጥብ አጉልቶና አስፍቶ ይናገራል። "..... ብዙ መብል አዘጋጀላቸው በበሉና በጠጡ ጊዜ አሰናበታቸው። እነርሱም ወደ ጌታቸው ሄዱ። ከዚያም በኋላ የሶሪያ አደጋ ጣዮች ወደ እስራኤል አገር አልመጡም"። 2ኛ ነገ 6፣8-23





በሃይማኖት መኖርና መንፈሳዊ ትምህርት መማር ማለት ራስን ለበጎ ነገር መቀየር ማለት ነው። "እናንተ የምድር ጨውናችሁ..... መልካም ስራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" ማቴ 5:13-16 የመንፈሳዊነት ታላቅ ደረጃ ሥለፍቅር ራስን አሳልፎ መስጠት ለሰዎችም ጥቅም መኖር ነው ወርቃማ ንግግር ተብለው ከሚታወቁት ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አንዱ እንዲህ ይላል፦ ለእናንተ ሊደረግላችሁ የምትፈልጉትን ለሌሎችም አድርጉ በእናንተ ሊደረግባችሁ የማትፈልጉትን በሌሎች ላይ አታድርጉ። በእውነትም ወርቃማ ህግ ነው።በቃ መጽሐፍ ቅዱስም ሲጠቃለል ከዘፍ ምዕራፍ 1 እስከ ራዕይ ምዕራፍ 22 ድረስ የሚያስተምረው አንድ ነገር ነው ሁሉም ያልፋል መልካም ሥራ ስርታችሁ እለፉ። የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ክርስቲያን በአህዛብ መካከል ሲኖር መልካም ነገርን በማድረግ እግዚአብሔር እንዲከበርና የእግዚአብሔርም በረከት ለእርሱ እንዲተርፈው ያደርጋል።

መንፈሳዊ ሰው ማለት ሌሎች ሰዎች ማየት የማይችሉትን ነገር ማየት እንዲችል መንፈሳዊ አይንን ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበለ ማለት ነው። ዓለማዊ ሰው ሀብታሙን፣ ታዋቂውን ጊዜ የሰጠውን ክፉ ሰው ይመለከታል። መንፈሳዊ አይን ያለው ሰው ግን ጊዜ የጣለውን፣ ቀን የጐደለበትን፣ የወደቀውን ሰው ይመለከታል "ወንድሞች ሆይ ሰው በማንኛውስ በደል እንኳን ቢገኝ መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየዋህነት መንፈስ አቅኑት። አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንደሁም የክርስቶስን ህግ ይፈጽም" ገላ6:1-2 ። የክርስቶስ ህግ ፍቅር ነውና ስለወንድሙ ሲል በጎ የሚያደርግ ህግና ነቢያትን ይፈጽማል። የሁሉ ነገር ፍፃሜ ፍቅር ነው። እምነትንም ተስፋንም ፍቅር ይፈጽማል።

ከትዳር በኋላ ባለው ኑሮ በቤት ውስጥ ከዘመዶች ጋር፣ ከማህበረሰቡ ጋር መጋራት የሚያስፈልግ ብዙ ነገር ይኖራል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ግጭቶች ውጥረቶች የሚከሰቱበትም አጋጣሚ አለ። በሀዘን

፣በደስታ፣ በእድር፣ በዕቁብ፣በመረዳጃና በተለያየ የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴዎች እንድትሳተፉ ማህበራዊኑሮ ያስገድዳል። በተቃራኒው ደግሞ ፍጹም ከሀሳባችሁ የራቀ የአመለካከት ልዩነትን የሚፈጥር እንቅስቃሴ ይደረጋል። በዚህ መንገድ ለመጓዝ ደግሞ ህሊናችሁ አይፈቅድ ይሆናል።በዚህ ወቅት ሃይማኖትን በማስቀደም ሌላውን ነገር ከህሊና የተነሳ እያከናወኑ በህብረተሰቡ ውስጥ ስትኖሩ ባህሉንና ሃይማኖቱን እያከበራችሁ በመንፈሳዊ ጥበብ በብልሃት መኖርና እርቆ አስተዋይም መሆን ራስን መጠበቅ ነው። ትናንት ዛሬ አይደለምና እንደ ትናንት አይኖርም ሁሉ ነገር ይለወጣል። ይህ ሲሆን ዘመድና ቤተሰብ ሚስትን ወይም ባልን ላለመረዳት ምክንያት አድርጐ ስለሚገምት ሰላምን አደፍርሶ ትዳሩን ለመበጥበጥ አድፍጦ ማዘገም ይጀምራል። እርቆ በማጠር የሚቻል ነገር ካለ በመለገስ በትዳር ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ በመከላከል የላካቸውን ሰይጣን ማሳፈር ይገባል።

"መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገር ያወጣል ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገር ያወጣል " ማቴ 12:35 ለክፉሰው ማንም መቃብሩን አይቆፍርለትም ራሱ ይቆፍራታል። ባጠመደው ወጥመድም ይወድቃል። ለመልካም ሰው ግን እግዚአብሔር እግሩን ከመሰናከል ይጠብቅለታል። መላእኩንም በፊት ለፊቱ ይልክለታል። ለክፉ ስለክፉቱ ክፉ ነገርን አትመልሱ ቢራብ አብሉት ቢጠማም አጠጡት፣ በራሱም ላይ የቁጭት እሳት ትከምራላችሁ። እውነተኛ ክርስቲያን ሥለ ክፉ ነገር ሁሉ በጎ የሚመልስ ነው። "እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኮልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንአትንም ሀሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ ጌታ ቸር እንደሆነ ቀምሳችሁ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ህፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ ... መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሰሩ" 1ኛ ጴጥ 2:1-6

በሃይማኖት ከማይመስሉ ጋር ወይም ከማንም ጋር ቢሆን እንኳ ሰው በመሆናቸው ብቻ አብረን በሰላም መኖር እንችላለን ክርስቲያን የሰላም መልዕክተኛ ነው እንደ አሁኑብ በሃይማኖት አይመስሉኝም ብሎ የጅል ጽድቅ ለማግኘት የተሳሳተ ወንድሙን አይገልም።





ይመክራል፣ይጸልይለታል በፍቅሩም ይጠራዋል። እግዚአብሔርም ይህንን ይወዳል። ለአህዛብ እንዲህ ማድረግ ከተገባ እርስ በራሳችንማ ዘረኝነትንና ብሔርተኝነትን አጥፍተን በመንግስተሰማያት አብረን ለመኖር እንድንችል ያለ ነውርና ያለነቀፋ በፍቅር መኖር አይገባንምን? "በክርስቶስም...ደስታዬን ፈጽሙልኝ በአንድ ሀሳብ ተስማሙ አንድ ፍቅር አንድ ልብም አንድ ሀሳብም ይሁንላችሁ....... እያንዳንዱ ለእርሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ ዘንድ የነበረው ሀሳብ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ይሁን" ፊሊ 2:1-5

# ምዕራፍ ሰባት

## ኢ.ክርስቲያናዊ የሆኑ ጾታዊ ክንውኖች

ጾታዊ ግንኙነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትውልድን ቀጣይ እንዲሆን የሚያስችል የአምላክ በጎ ሀሳብ ነው:: ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ዘለዓለማዊ ተደርጐ የተፈጠረው አነዋወሩ ሁሉ አዕምሮ ከሌላቸው እንስሳት የተለየ እንዲሆን ታስቦ ነው:: በተለይ መንፈሳዊ ሰው ከፍጥረታዊው ሰው በብዙ መንገድ ስለሚለይ አለምና ምኞቷ በእርሱ ዘንድ ሙት ናቸው:: ምድራችን በየዘመኑ ለአዕምሮ የሚዘገንኑ፣ ለጆሮ የሚቀፍ፣ ልትሸከም የታከታት የጾታ ነውር ሲፈጸምባት ይስተዋላል:: አንዳንዶቹ ጾታዊ ክንውኖች ይህንን ሰው ሊያደርገው ይችላል ወይ ብለን እስኪደንቀን ድረስ ጸያፍ ናቸው::

1. ግብረ ሰዶም

ምንም ሰብአዊነት የማይታይበት የተፈጥሮ ህግን የሚያዛባ፣ የእግዚአብሔርን የተስተካከለ የመፍጠር ሥራ ወደ ጐን የሚያደርግ ለባህሪያቸው የማይገባውን ነገር እያደረጉ ሴቶች ከማይመስሏቸው ከሴቶች ጋር የሚተኙበት፣ ወንዶችም ሴቶቻቸው እያሉ ከወንዶች ጋር የሚዳሩበት በዚህ ምድር ላይ ከሚፈጸሙ ኃጢአቶች ሁሉ የከፋው ቅሌት ነው:: እግዚአብሔርን አላከበሩምና ነፍሳቸው እየቀለጠች ይኖራሉ:: ጌታ ግን ሁሉንም የሚያደርግበት ጊዜ አለውና የሴሰኝነት ዋጋቸውን አያስቀርባቸውም::

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 19 ላይ የተገለጡት የሰዶምና የገሞራ ህዝቦች የዚህ ኃጢአት መስራችና አስተላላፊዎች ነበሩ:: የእግዚአብሔርን መላእክት እንኳን ሳይቀሩ በግብር ለማወቅ ሎጥን እጅግ አስጨንቀውት ነበር:: ሎጥ የእግዚአብሔር ሰው እንግዶቹን እንዲተውለት በመላዕክቱ ፋንታ ከወንድ ያልደረሱ ደናግላን ልጆቹን ሊሰጣቸው ፈቃደኛ ሆኖ ቢማፀናቸው እንኳን ሊቀበሉት አልፈለጉም:: ይልቁንም በኃይልና በጉልበታቸው ቤቱን ገንጥለው ሊገቡ ተነሱ:: ሁሉቱም መላእክት ከሰማይ እሳት አዝንበው አጠፏቸው ሸሽተው





እንዳያመልጡ እንኳን አይናቸው ታውሮ ነበር:: የግብረ ሰዶማዊነት መጨረሻ በሰማይም በምድርም መቅሰፍ፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሀነምን መጨመር ነው::

በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገራት በህግ ሳይቀር ተደንግጐ እንደማንኛውም መልካም ግንኙነት እየተቆጠረይገኛል:: ወንዶች በብዛት በሚኖሩባቸው ማረሚያ ቤቶች ባል ከሚስቱ ጋር የሚያደርገውን ሩካቤ ያህል ነፃነት እየተሰማቸው ይፈጽሙታል:: የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ከወጡ በኋላ ደግሞ ወደ ህብረተሰቡ መካከል በመዝለቅ ምንም በማያውቁ ህፃናት ላይ የወሲብ ጥቃት እየፈጸሙ የግብራቸው ተባባሪ ሲያደርጓቸው ይስተዋላል:: በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ፊልሞች፣ ዘፈኖችና ጽሑፎች ሥርጭቱን ለማፋጠን የጐላ አስተዋጽኦን አድርገዋል:: አሁን ደግሞ ወሲብ ቀስቃሽ የኢንተርኔት መልዕክቶች ችግሩን የሚያባብሱ ቤንዚል ሆነዋል::

በውጭው ዓለም ሁለት ወንዶች በአንድ ቤት የሚኖሩ ከሆነ አንደኛው የግድ ባል እንደሆነ ይታሰባል:: ለአንዳንድ ማህበራዊ ጉዳዮችም የቤቱ ኃላፊ መታወቅ ያለበት ከሆነ ከሁለት አንዱ አባወራ እንዲሆን ህጉ ሳይቀር ያስገድዳል:: የሴት ጓደኛ የለኝም ብሎ የሚናገር አንድ እድሜው ለአቅመ አዳም የደረሰ ወጣት ቢኖር በውስጠ ታዋቂ የወንድ ጓደኛ /ግብረሰዶማዊ/ አለኝ ማለት እንደሆነ ይታሰባል:: በሀገራችን ኢትዮጵያ ለጊዜው ገሀድ ወጥቶ አይታይ እንጂ በየቦታው እየተዘወተረ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል:: በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትም የሚያሳፍር ጉዳይ መሆኑ ከቀረ ሰነባብቷል:: ሴት መሆንን የሚመኙ ወጣት ወንዶች ከአለባበሳቸው፣ ከንግግራቸው፣ ከጸጉር አሰራራቸው አልፎ በጾታዊ ጉዳይም ተሳታፊ እየሆኑ መጥተዋል:: ሴቶችም ቢሆኑ እንዲሁ ማድረጋቸው አልቀረም ወንድ ለመሆንም ሲጣጣሩ ይታያል::

እንደ ሰደድ እሳት በስልጣኔ ተሸፍኖ እየወረረን ያለውን አመንዝራነት እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል በተለይ ሃይማኖቱንና ሀገሩን የሚያከብር፣ ባህሉን የሚወድ ዜጋ የበኩሉን አስተዋጽኦ



www.ethiopianorthodox.org

በማበርከት አጥብቆ ሊቃወመው ይገባል:: አሁን ባለው ፍጥነት ከቀጠለ ሁላችንንም ስለሚጎዳ ለተወሰኑ የመንግስት አካላትና የሃይማኖት ተቋማት የሚተው ነገር ሳይሆን በሰው ዘር ሁሉ ላይ የተቃጣ ታላቅ የሰብአዊነት ጦርነት መሆኑን ተገንዝቦ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ባይቻል እንኳን ሀገራችንንና ህዝቧን ለመጠበቅ ሁሉም ሰው የድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል::

2. ዝሙት

አስቀድሞ እግዚአብሔር ገና በህገ ልቦና በኦሪት ቃል ሳያጽፈውና ለሙሴ ሳይሰጠው አታመንዝር የሚለውን ህግ በአዳምና በሔዋን መካከል አስቀምጦት ነበር:: ከአንድ በላይ ማግባት ወይም ከትዳር ውጭ ሩካቤ ቢያስፈልግ ኖሮ ለአዳም ከሔዋን በተጨማሪ ሌላ ሴት ባዘጋጀለት ነበር:: እንዲህ አይነት ተግባር መፈጸም በሰውነት ላይ በደል መስራት ሥጋንም ማርከስ ስለሆነ በቃልኪዳኑ ታቦት ላይ ሳይቀር አታመንዝር በማለት የማይሻር የማይሻሻል ህግ መሆኑን አስታወቀ:: ዝሙትን የሚወዱ ርቃናቸውን ቆመው በአምላክ ፊት የተኮነነች ነፍስ ይዘው ይቀርባሉ:: የጽድቅ ልብስን አለበሱምና ሰውነታቸውን ላልተፈቀደ ፍትወት መገልገያ ስላደረጉት የአምላክ ክብር ይጎድላቸዋል ከሚመጣውም ፍርድ አያመልጡም::

ከጋብቻ በፊትም ይሁን በጋብቻ እያሉ ከትዳር ውጭ የሚፈጸም ማንኛውም ወሲባዊ ግንኙነት ዝሙት ነው:: ማመንዘር አካላዊ፣አዕምሮአዊ፣ሥነልቦናዊና መንፈሳዊ ጉዳቱ የጐላ ነው:: ትዳርን በንጽህና መጠበቅ ከተፈለገ ንጽህናውን የሚያሳጡትን በሮች በሙሉ መዝጋት የግድ አስፈላጊ ነው:: ምን አልባት በመካከላቸው በተለያዩ ምክንያት ለሩካቤ ዝግጁ የማይሆኑበት ጊዜ ቢኖር እርስ በርስ ግልጽ ውይይት በማድረግ ችግሩን ለመፍታት መጣር እንጂ በትዳር ላይ አመንዝራ ሆኖ መታየት የሞራል ውድቀት ከማስከተሉም በላይም በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው:: "በጉያው እሳትን የሚታቀፍ ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው በፍም ላይ የሚራመድ እግሮቹስ





የማይቃጠሉ ማን ነው ወደ ሰው ሚስት የሚገባም እንዲሁ ነው የሚነካም ሁሉ ሳይቀጣ አይቀርም":: ምሳ 6:27-29

ከትዳር ውጭ የሚፈጸም ዝሙት የሕይወትን አቅጣጫ ወደ አልተፈለገ መስመር የሚመራ በመሆኑ ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ታላቅ አደጋ አለው:: ወጣቶች ለራሳቸው ሲሉ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል:: በሽታ፣ አላስፈላጊ እርግዝና፣ ውርጃና ሌላም ተጨማሪ ሽክሞችን ያተርፋል:: በእግዚአብሔር ቃል መኖር፣ ለፈተና ከሚመች ቦታ ራስን ማራቅ፣ የዓላማ ሰው መሆንና የሕይወትን ትርጉም በአግባቡ መረዳት ግፊቱን መቋቋም ያስችላል:: የክርስቲያን አገሩ በሰማይ ነው ዝሙት ደግሞ ሰማያዊ ርስትን የሚያሳጣ እንቅፋት የሆነ ኃጢአት ነው:: ሚስቶች ለባሎቻቸው የማይታመኑ ከሆነ ባሎች ስለሚበሳጩ በመጠጥና በአደንዛዥ እጽ ተለክፈው አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ወደ ዝሙት ይገባሉ:: ባሎች ለሚስቶቻቸው ሥሜት ጥንቃቄ የጎደለውን ሩካቤ የሚፈጽሙ ከሆነ እነርሱም በበኩላቸው የጓሮውን በር ማንኳኳታቸው አይቀሬ ነው:: ትዳር የሁለቱም የጋራ ኃላፊነትን የሚፈልግ በመሆኑ ባሎችን ከቤት የሚገፋ ማንኛውንም ነገር በተቻለ መጠን ለመቅረፍ መሞከር የሚስቶች ኃላፊነት ነው:: ሰላማዊ ፍቅርን በመለገስ አስፈላጊ በሆነው ነገር ሁሉ ራሳቸውን በመጠበቅ ባሏ የሚመርጣት ተወዳጅ ሚስት ሆና መታየት ይኖርባታል:: ሴቶች የቤቱን ሥራ ሲያከናውኑ ልጆችን ሲንከባከቡ ሙሉ ትኩረታቸውን ትዳራቸውን ለማሸነፍ ስለሚያደርጉት ባሎች ከመበሳጨትና ለእኔ ጊዜ አልተሰጠኝም ብሎ ከማሰብ ይልቅ መግባባት በተሞላበት ውይይት ቢተራረሙ በእያንዳንዱ ነገርም ለሚስቶቻቸው ጥንቃቄ ቢያደርጉ የሚያንኳኩትን የጓሮ በር ከፍተው እንዳይወጡ በፍቅር የመዝጋት ኃይል ይኖራቸዋል::

የጋለሞታ ልብስ የለበሰች ነፍሳትንም ለማጥመድ የተዘጋጀች አንዲት ሴት አንድ ወጣትን አግኝታው ለዝሙት እንዴት እንዳባበለችው ጥበበኛው ሰለሞን ሲያብራራ:: ሴትየዋ ባለትዳር ሆና ሳለች በባሏ ላይ በደልን ለመፈጸም የእግሩን መውጣት የምትጠባበቅ

መሆኗን ይገልጣል " ና እስኪነጋ ድረስ በፍቅር እንርካ በተወደደ መተቃቀፍ ደስ ይበለን ባለቤቴ በቤቱ የለምና" ምሳ 7:18 በሚል በማር በተለወሰ አንደበት የራሳቸውን ኑሮ አፍርሰው ልጆቻቸውን በትነው ትዳራቸውን ፈተው የተለያዩ ማታለያዎችን እየተጠቀሙ በቃላት ጋጋታ፣በቆሸሸ ህሊናና አካል የተቀደሰውን ሰው ሊያረክሱት የሚፎሯሯጡት ለጊዜው እንደዝግባ ቢያድጉ እንኳን የእጃቸውን ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ። ቅዱስ ጳውሎስ በአጭር ቃል "በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያ አይነት ዝሙት በአህዛብ እንኳን የማይገኝ ነው" 1ኛ ቆሮ 5:1 በማለት ዘመኑ ዝሙት የነገሰበት መሆኑን ያስረዳል። አክሎም ምክሩን ሲለግስ "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን" እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም። ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንደሆነ አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሏልና ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው። "ከዝሙት ሽሹ" 1ኛ ቆሮ 6፣15-18 ይላል ዝሙት ሊሸሹት የሚገባ፣ ከያዘ የማይለቅ፣ ለሞት የሚያበቃ አደገኛ ሱስ ነው።

3. ውርጃ

ሌላ ተጨማሪ ሁለተኛ ጥፋት ነው። በመጀመሪያ ለውርጃ የሚገደዱበት ምክንያት እርግዝናው ህገ ወጥ በሆነ ወሲብ /ዝሙት/ የመጣ ስለሚሆን ነው። በሴሰኝነት መመላለሱ አንድ ነገር ሆኖ በኃጢአት "ስኬል" የሚሰቀል ይመስል ወደተሻለው በደል በማምራት ህፃኑ ገና ደም እያለ በመድሀኒት አቃጥሎ መግደል ታላቅ ወንጀል ነው። የምታስወርደው ሴት ብቻ ሳትሆን እንድታስወርድ የሚያስፈልጋትን እርዳታ የሚያደርግ /በገንዘብ፣በምክር/ እንዲሁም ውርጃውን የሚፈጽምላት ለሥራው ሥነ ምግባር የማይታመነው ሀኪምም ይሁን የሰፈር መድሀኒተኛ የሰው ነፍስ በማጥፋት ወንጀል ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ናቸው። እናስወጣለን ብለው ሲሯሯጡ የንስሐ ጊዜ እንኳን የማይተርፋቸው ገና በህፃንነታቸው ለአንዴና ለመጨረሻ





ጊዜ የሚያሸልቡ ብዙዎች ናቸው። ሕይወታቸው በሙሉ በመሰናክሉ ወደ ማይመለሱበት ይጓዛሉ።

የሴቶችን እኩልነትና ሰብአዊ መብት ለማስከበር ሲባል በአንዳንድ ሀገራት በህግ ተደንግጎ ውርጃን ፊትን የመታጠብ ያህል ቀላል አድርገውታል። በኢትዮጵያ ውስጥም ህጋዊ ይሆንላቸው ዘንድ የመንግስት ይሁን ለማግኘት የራሳቸውን አንድምታ በመደርደር አስፈላጊና ለሀገር ጠቃሚ እንደሆነ የሚወተውቱ እየተበራከቱ መጥተዋል። ለሀገር የሚጠቅመው ማስወረዱ ሳይሆን ወደዚህ ችግር የሚከተውን ዝሙትን ለማስወገድ መጣሩ ነው። ህገወጥነትን በተሻለ ህገወጥነት መሸፈን የህገወጦች ህገወጥ መሆን ነው። ዝሙትን በውርጃ ለመከለልም መሞከር ለምን የንስሐ ጊዜ እግዚአብሔር ሰጠኝ ብሎ በአመጽ በመጽናት መርጥ ይሆናል። እግዚአብሔር ስለዝሙታቸው ሲታገስ በአመፃ መንገድ ላይ መጽናትና የጨመረላቸውን የበረከት ጊዜ በውርጃ ማሳጠር ምን ያህል ታናሽነት ነው?

ምንም በማይታወቅበት ሁኔታ በህመምና በጉዳት ምክንያት ወይም ጽንስ ከሚገባው ቦታ ውጭ ከተጸነሰ ውርጃ ሊፈጠር ይችላል ይህ በእግዚአብሔርም ፊት እንደ ኃጢአት አይቆጠርም። በገዛ ፈቃድ ምድራዊ ሕይወቴን ላሰማበላሽት በሚል ፈሊጥ የሚፈጸም ውርጃ ግን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያሳጣል። በበጎ ህሊና በንፁህ አዕምሮ ለሚያስብ ሰው ውርጃ አስፈላጊ ነው ብሎ ማመን ከእብደት አይተናነስም። ውርጃ ህፃኑ በመወለዱ ምክንያት ከሚመጣው ችግር የበለጠ ስቃይ ያመጣል እንጂ የተሻለ መፍትሔ የለውም። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ይልቁንም ክርስቲያን አጽንኦት ሰጥቶ ሊያወግዘው የሚገባ ተግባር ውርጃ ነው።

4. ፍች

ጋብቻ የዘለዓለም ቃልኪዳን ከሆነ ፍች ደግሞ የእግዚአብሔር እቅድ ጨርሶ የሚያጠፉ ነቀርሳ ነው። ፍች በማህበራዊም ይሁን በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የተለያዩ ጉዳቶች አሉት። በሁለቱ ተጓዳኞች ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት በተጨማሪ በልጆችና በቀሪው ቤተሰብ ላይ ያለው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። በጥልቀት ከተመለከትነው ደግሞ

በሀገር ኢኮኖሚና በማህበራዊ ግንኙነት ላይ ሌላ አሉታዊ ጉን ማየት እንችላለን:: ሚስት ባሏ ከሞተባት የተፈታች ናት እርሱም እንዲሁ በሃይማኖት ምክንያትና በዝሙት ጠንቅ ለፍቺ የሚያበቃ ምክንያት ይኖራል:: በዚህ ሁኔታም ቢሆን ፍቺ እንደ አማራጭ የሚቀርበው በመጨረሻው ሰዓት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ከልጅነት ሚስት ጋር ደስ ይበልህ በማለት ቃል ኪዳን ተጠብቆ እንዲኖር ያስገነዝባል:: መንፈሳዊም ሥጋዊም ትርፍ የሌለው ነገር ቢኖር ፍቺ ነው :: እንዲያውም ድካምና ሥቃይ፣ አዲስ ጋብቻ፣ አዲስ ሰው፣ አዲስ ኑሮ መጀመር፣ በማረፊያ ሰዓት የሰሩትን ቤት አፍርሶ አዲስ ቤት ለመሥራት መነሳት አሰልቺ ቅዥት ነው:: ስለዚህ ለፍቺ የሚያበቁ ሁኔታዎችን አስቀድሞ በራቸውን መዝጋት ያስፈልጋል::

ሀ. <u>ችኩልነት</u>፡- በደንብ ሳይተዋወቁ ትዳርን ይጀምሩና ሰው ነው ብለው ያሰቡት ሰው ፍፁም ተቀይሮ አውሬ ይሆንባቸዋል:: ራሱን በመልካም ጭንብል ሸፍኖ ስለሚቀርብ ከንግግሩ በስተጀርባ እርሱነቱን አስቀድሞ መመርመር አስፈላጊ ነው:: ለተጨማሪ ግንዛቤ የእጮኝነት ጊዜን በመልካም ሁኔታ ማሳለፍ የሚለው ክፍልና ምዕራፍ 3 ላይ ነገሮችን በሒደት መመርመር የሚለውን ንዑስ ርዕስ ደግመው ያንብቡት ::

ለ. <u>የሰዎች ጣልቃ መግባት</u>፡- ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ዘመድ ማንም ይሁን ማን በትዳር መካከል ገብቶ ምንም ነገር እንዲል አይገባም:: ራሳቸው ባለትዳሮች ምክሩን ሲፈልጉ ወይም በመካከላቸው ችግር እንደተፈጠረ ሲያስረዱ ሰላም ለማስፈን በተቀደሰ ሀሳብ የጻድቅን ሥራ ሊሰሩ ይችላሉ:: ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ከባለቤት በላይ ለትዳር አሳቢ በመሆንና የሚስት ወገን ባልን እየኮነነ የባል ወገን ሚስትን እየኮነናት በትዳሩ ላይ ውጥረት መፍጠር አስፈላጊ አይሆንም:: ለባሏ የምትመቸውን ሚስት ለእኛ አልተመቸችንም ከሚል ራስ ወዳድነት በመነሳት አንዳንድ ወላጆች የሚያደርጉት ወይ ከእኛ ወይ ከሚስትህ ምረጥ የሚል ማስጠንቀቂያና ብጥበጣ ጨካኝነት ነው::





ሐ. ክፉ ወሬ :- ጥሩ መካሪና አሳቢ በመምሰል የራሳቸው እያረረ የሰው ሊያማስሉ የሚፈልጉ የኑሮ ካርታ የጠፋባቸው ግለሰቦች ሌላ የትዳር እንቅፋት ናቸው:: ሐሜት ሁል ጊዜም መኖሩ አይቀርም ዋናው ነገር በትዳር ላይ የሚቃጣ አደጋ መሆኑን ተገንዝቦ ንፋሱን መከላከል ነው:: መንፈሳዊነትን በተላበሰ ጥናት ለምን እንዲህ እንደተባለ መርምሮ በማወቅ ለሀሜት የሚያጋልጡ ነገሮች ካሉ ቀዳዳውን በመድፈን ለወደፊቱ ነቅቶ መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው:: ሚስት ከባሏ ውጭ የምታደምጠው ሌላ ወሬ ሊኖራት አያስፈልግም እርሱም እንዲሁ::

መ. መካንነት :- የኃጢያት ምልክት ተደርጐ ይቆጠርበት የነበረው የብሉይ ኪዳን ዘመን አልፎ በአዲስ ሕይወት በክርስቶስ በቱገኘው ነፃነት በሚኖርበት የሀዲስ ኪዳን ዘመን መካንነት ትዳርን የሚያፈርስና ለፍቺ የሚያበቃ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ መነሳት የለበትም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ይቻለዋልና በወደደ ጊዜ በልጆች ያከብራል:: ልጆች የእግዚአብሔር ሥጦታዎችና ገጸበረከቶች ናቸው ከቶ በሰው ፈቃድ አይመጡም አይኖሩም:: ራሔል የያዕቆብ ሚስት ልጅ ባልወለደችበት ወራት ያዕቆብን ልጅ እንዲሰጣት ጠየቀችው ይህ ካልሆነ እንደምትሞትም ገለጠችለት:: "ያዕቆብም ራሔልን ተቆጥቶ እኔ የሆድን ፍሬ በነሳሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን? አላት" ዘፍ 30:2 ስለዚህ እንዲሁ ቢወድ ማህጸንን የሚፈታ እግዚአብሔር ነው:: ባይወድም ግን የሚከለክል እርሱ ነው:: እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው ሰውን ከሰው ለመለየትና አንዱን ለመጉዳት ፈልጐ አይደለም:: ከሰው ሀሳብ ውጭ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶች አሉት:-

1. ተዓምራቱን ለመግለጥ:- ወደፊት ልጆችን በመስጠት ዘፍ 18፣13-15
2. የእምነታቸውን ጽናት ለማረጋገጥ በትዕግስት በሚቀበሉበት ጊዜ መዝ24፣3
3. በተፈጥሮ ላይ ብቸኛ ባለሥልጣን መሆኑ ለማስረዳት:- ሸክላ ሰሪ ሸክላውን እንደፈለገ እንደሚያደርገው ኢሳ 45፣9

4. ለእነርሱ ያዘጋጀው የሚባረኩበት የፀጋ ስጦታ ሌላ ለሆነ ኢሳ 56፥5
5. በተሻለ ነገር ሊጠቅም ሲፈልግ ሳሙኤልና መጥምቁ ዮሐንስን የመሰለ ልጅ በመስጠትና ሉቃ 1፥8 1ሳሞ 2፥1
6. በማይመረመረው የአምላክ መለኮታዊ አሰራር ምክንያት መካንነት ሊመጣ ይችላል፡፡

በሥጋዊ ጥበብ የሚጓዙ ሰዎች ቅድመ ጋብቻ የመካንነት ምርመራን በማድረግ በሴቷ ወይም በወንዱ ላይ ችግሩ ካለ የታሰበውን ትዳር ያፈርሳሉ፡፡ በክርስቲያን እጮኞች መካከል ይህ አይደረግም፡፡ መሰረታዊውን የሃይማኖት ትምህርት በቀጥታ ይቃወማል፡፡ እንዲህ የሚያደርግ ክርስቲያን ካለ በእርግጥም እምነት የለውም ክርስቲያንም አይደለም፡፡ ሃይማኖት ያለው ሰው የሚደገፍበት ለዘመናት የፀናውን እግዚአብሔርን ነውና አምላክ ሁሉን ነገር እንደሚፈጽምለት ያውቃል፡፡ ያም ባይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ብሎ ዝም በማለት የጌታውን ማዳን ተስፋ ያደርጋል፡፡ እንዲህም ይላል "እርሱ እግዚአብሔር ነው የፈቀደውን ነገር ያድርግ" ሐዋ 21:14 መ.ሳ 1ኛ 3:18

ሐና የሳሙኤል እናት እግዚአብሔር እንዴት እንዳሰባት ከእግዚአብሔር ቃል እናነባለን፡፡ መጽናናት አልወደደችም ነበር ልጅ የላትምና፡፡ በዚህ ምክንያት የተነሳ በቤተመቅደስ መካከል እንደ ኃጢአተኛ ስለተቆጠረች ከመስዋዕቱ እንዳትካፈል ተከለከለች፡፡ ዝም ብላ እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ በማድረግ በሌሊትና በቀንም አብዝታ ጮኸች እግዚአብሔርም ጽናቷን አይቶ ተአምራቱን ገለጠና ከሰባት ልጆች በሚበልጥ ልጅ በሳሙኤል ባረካት፡፡ "ልቤ በአምላኬ ፀና .......... መካን የነበረችው ሰባት ወለደች ወላዲቱም መውለድ ተሳናት" በማለት እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቀይር አሰምታ ተናገረች መሳ.1ኛ 2 ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18:1-13 በንጽጽር ተመልከቱት፡፡

ዘካርያስ ባረጀበት ወራት መልአኩ መጥቶ ጸሎቱ እንደተሰማ አበሰረው ዘካርያስ የሚሰማውን ማመን አቅቶት ነበር፡፡እግዚአብሔር





ግን ዘሩን ባረከና የኤልሳቤጥን ማህፀን ከፍቶ አምላኩን የሚያጠምቅ ዮሐንስን የሚያክል ልጅ ሰጠው፡፡ እግዚአብሔር በብሉይም በሀዲስም የዘመናት ድንቅ አምላክ ነውና ዛሬም ቢሆን በሥራው የማይሰንፍ ብርቱ በመሆኑ በትዳራችሁ የጐደለውን ከመለመን ውጭ ተስፋ መቁረጥ አይሆንም አይደለም እግዚአብሔር በጭራሹ ተስፋ የሚቆረጥበት አምላክ አይደለም፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን ጠለቅ ብለን በመግባት ያባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ስንመለከት እግዚአብሔር ለፀጋ ዘአብና ለእግዚእሃርያ ያደረገው ድንቅ ነገር ከአዕምሮ በላይ እንደሆነ እናያለን፡፡ ጣዖታትን የሚያጠፋ፣ አህዛብን የሚያጠምቅ ፣ ወንጌልን የሚሰብክ፣ ለሃይማኖቱ የሚሞት ፣ጸሎተኛ ጻድቅ እንደሰጣቸው እንረዳለን አምላከ ተክለሃይማኖት ዛሬም በሥራው ቸልተኛ አይደለምና በትግስት ለሚጠብቁት በበረከት ይመጣላቸዋል፡፡

## 5. <u>ማስተርቤሽን /Masturbation/</u>

ራስን በራስ በወሲብ ማርካት/Masturbation/ ኃጢአት ነውን?

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ጥቂት ስለ "ማስተርቤሽን" ምንነት እንመለከታለን፡፡ "ማስተርቤሽን" ወይም ራስን በራስ በወሲብ ማርካት ማለት፡- ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች የመራቢያ አካላቸውን በመነካካት ጾታዊ ስሜት እንዲሰማቸውና የስሜት እርካታ እንዲያገኙ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው፡፡ በተለያየ ሀገርና አካባቢ የተለያየ ሥም ይዞ እናገኛለን፡፡ በአንዳንዶች ዘንድ "ሴጋ" በመባል ይታወቃል የሊቀ "ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር" የተሰኘው መጽሐፍ ደግሞ "ቀላጭነት" በማለት ይገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ "ማስተርቤሽን " ማለት ከተፈጥሮ ስርዓት ውጭ በሆነ መንገድ በራስ ላይ ወሲብ መፈጸም ማለት ነው፡፡

ወደ ተነሳንበት አብይ ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ ማስተርቤሽን ኃጢአት ነው አይደለም የሚሉ የተለያዩ ወገኖችን እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ አዕምሮ ያለው ሰው በነፃ ህሊናው ስለዚህ ነገር ቢመረምር ሕሊና አይዋሽምና እያደረገ ያለው ምን እንደሆነ ማንም ሳይነግረው ይረዳል፡፡ ማስተርቤሽን የሚጠቀሙ ሰዎችን ብትጠይቋቸው ምንም



www.ethiopianorthodox.org

ነፃነት እንደሌላቸው፣ የወንጀለኝነት ስሜት እንደሚሰማቸው፣ ይልቁንም ፈጣሪ ዝሙት ፈጽማችኋል ብሎ ሊቀጣን ይችላል ብለው እንደሚጨነቁ ያወጓቸዋል:: ከዚህ አንፃር ሌላ ምስክርነት የሰዎች አስተያየትን ሳንሻ "ማስተርቤሽን " ኃጢአት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል "ትንሹ ፈራጅ" /ህሊና/ ካልፈረደብህ "ታላቁ ፈራጅ እግዚአብሔር " አይፈርድብህም:: በማንኛው ነገር ሕሊና ነፃ ካላደረገ እግዚአብሔር የራስን ሕሊና ተጠቅሞ እንደሚፈርድ ወይም ራሱ በራሱ ላይ እንዲፈርድ እንደሚያደርገው የቤተክርስቲያን ሊቃውንትና መጻሕፍት ያስተምራሉ:: "የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የዘነጋ ሰው የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል" 3ኛ መቃ 6:12

ስማይን ብትጠይቀው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ይነግርሃል ፀሐይንም ብታማክራት የፈጠራት ማን እንደሆነ ትመሰክራለች:: በአጠቃላይ ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ህልውና ከመናገሯም በተጨማሪ የተፈጥሮ ሰዓትን በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ እንዴት መከወን እንዳለበት ታስገነዝባለች:: ከዚህ ጽንሰ ሀሳብ ተነስተን ስለ ሰው ተፈጥሮ ፣ ስለ እያንዳንዱ ብልቶቹ፣ ስለሥራ ድርሻቸው ስናጤን የዐይን ሥራ የአይን፣ የጆሮም ሥራ የጆሮ ሆኖ እናገኘዋለን:: ስለዚህ በእጅ እንዳስሳለን ሥራ እንሠራለን እንጅ ወሲብ አንፈጽምም ማለት ነው:: በምላሳችን እንናገራለን እንጂ አንሰማም:: ይህንን የተፈጥሮ ህግ ጥሰን እግዚአብሔር ባልፈቀደው መንገድ ብንሔድ ህገ ወጥ ድርጊት መፈጸም መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ህግን ያፈረሰ ደግሞ ኃጢአት አደረገ:: ስሜታቸውን መግራት በማይችሉበት ወቅት አንዳንድ ሰዎች የተለያዩ መላምቶችን በመዘርዘር በራሳቸው ማስተዋል ብቻ በመደገፍ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ለምኞታቸው ማስፈጸሚያ ሲያደርጉት ይፈልጋሉ:: ሀሳባቸውንም ሲያብራሩ ኃጢአት ኃጢአት የሚሆነው በሌሎች ወገኖች ላይ ጉዳት ሲያደርስ ነው እንጂ ሌላውን እስካልጐዳ ድረስ ኃጢአት አይደለም ይላሉ:: እዚህ ጋር የተዘነጋ ነገር አለ:: የመጀመሪያው ነገር እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነውና በራሱ ላይ ከገደብ ያለፈ ነፃነት የለውም:: ምን አልባት





የሚከለክለው ላይኖር ይችላል:: በተጨማሪም እንደ ክርስትና ትምህርት እያንዳንዱ ክርስቲያን ከጥምቀት ተወልዶ በሥጋ ወደሙ ይከብርና በሜሮን ይታተማል ከዚያ በኋላ የክርስቶስ አካል ነው:: በመሆኑም የክርስቶስን አካል የጋለሞታ አካል እንዲያደርግ አልተፈቀደለትም:: በራሴ ላይ የፈለኩትን አደርጋለሁ ማለትም አይቻልም:: ብልቶቹም የአመጻ የጦር ዕቃ መሆን የለባቸውም ሮሜ 6:13

ለምሳሌ አንድ ሰው እኔ በራሴ ላይ ሥልጣን አለኝ ሌላ ሰው አልነካም ስለዚህ ታንቄ እሞታለሁኝ ቢል እንደ ነፍስ ገዳይ አይቆጠርምን? ለዚህም ነው ቤተክርስቲያን ከፍትሀተ ጸሎት ሳይቀር የምታግደው ::

በእርግጥ ሰው ነፃ ፈቃዱን ተጠቅሞ የፈለገውን ሊፈጽም ይችላል::መታወቅ ያለበት ግን ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ለንስሐ ፍሬ ያዘጋጃል ወይስ ወደሞት ይመራል የሚለው ጉዳይ ነው:: 1ኛቆር 10:23

<u>ማስተርቤሽን የሚያይለው ሰዎች በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ነው?</u> በአሜሪካን ሀገር የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ማስተርቤሽን በጣም የሚያይለው በወጣቶችና በጎልማሶች ላይ ነው:: ከዘመናት በፊት የሚታመነው ማስተርቤሽን የሚጠቀሙ ወንዶች ብቻ እንደሆኑ ነበር:: በአሁኑ ሰዓት ከወንዶች ባልተናነሰ ቁጥር የሴቶችም መጠን ጨምሮ ይገኛል:: እድሜያቸው እስከ 22 ዓመት የሚደርስ ከ 97% በላይ ወንዶችና ከ 91% በላይ ሴቶች የዚህ ሱስ ተጠቂ ናቸው:: እጅግ አስደንጋጩ ዜና ደግሞ እነዚህ ጥናቱ ከተደረገባቸው ግለሰቦች ከ97% በላይ የሚሆኑት ጥብቅ የተለያየ ሃይማኖት ተከታታዮች መሆናቸው ነው:: በእኛም ሀገር ይህንን ያህል የተጋነነ ቁጥር ያለው ተጠቃሚ ባይኖርም እጅግ በሚያስጋ ፍጥነት እየተራባ መሆኑን የሚጠቁሙ ብዙ ፍንጮች በየጊዜው ይታያሉ::

በአፍላ ወጣትነት ወቅት ወሲባዊ ስሜት ከመጠንከሩም በላይ አልፎ አልፎ የመረበሽ ብሎም የህመም ስሜት የሚፈጥርበት ጊዜ

አለ:: ወጣቶች ታዲያ ይህንን ውስጣዊ ውጥረት ለመቀነስ ሆን ብለው በገዛ እጃቸው የመራቢያ አካላቸውን በመነካካት የደስታ ስሜትን ለመፍጠር ሲሯሯጡ እንመለከታለን ምክንያቱም በመራቢያ አካል ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ሆርሞኖች አሉ:: እነዚህ ሆርሞኖች ደግሞ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ በማስተርቤሽን እርካታ እንደሚያገኙ ጠቋሚ መልዕክትን ያስተላልፋሉ:: ብዙዎች ለዚህ መልዕክት ተገዢ በመሆን ተግባራዊ ያደርጉታል::

አንዳንድ ጊዜ ምንም ባልታሰበበት ወቅት የወሲብ ስሜት ሊቀሰቀስ ይችላል:: ወጣት ወንዶች በሚበሳጩበት፣ በሚደሰቱበት፣ በሚያዝኑበትና በሚቆጡበት ጊዜ በሰውነታቸው ውስጥ ያለ ነርቫቸው ሁሉ ይነቃቃል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ጾታዊ አካላቸው ጋር ግንኙነት ያላቸው ነርቮች ስለሚነቃቁ ወሲባዊ ስሜታቸው ሊጠነክር ይችላል:: ወጣት ሴቶች ደግሞ በተለይ የወር አበባቸውን ከማየታቸው በፊት ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ወይም ከአዩ ጥቂት ቀናት በኋላ ኃይለኛ የወሲብ ፍላጐት ያስቸግራቸዋል:: ይ ሊሆን ግድ ነው:: የማደግ፣ለትዳርና ለሩካቤ የመድረስ ምልክት ነው:: አስከፊው ነገር ግን ይህ ስሜት በሚሰማቸው ጊዜ ምን እየተሰማቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ ሲሉ ብልቶቻቸውን በመነካካት ራሳቸውን በራሳቸው ማርካት መጀመራቸው ነው:: ይህንንም የእለት ተዕለት ሥራቸው ያደርጉትና አሳሳቢ ወደሆነ ችግር ውስጥ ይገባሉ::

ውስጣዊው ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በላይ ግን አስቸጋሪው ውጫዊው ተጽዕኖ ነው:: አንድ ሰው ወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን መመልከት፣ የፍቅር መጽሐፍትንና ጋዜጦችን ማንበብ፣ ስለተቃራኒ ጾታ የሚያቀነቅኑ ሙዚቃዎችን መስማት የሚያዘወትር ከሆነ ወደ ማስተርቬሽን ተጠቃሚነት የማይመጣበት ምንም ምክንያት የለውም:: እንዲያውም አዕምሮውን በእነዚህ ድርጊቶች ሞልቶ እርፌ ልቀመጥ ቢል እንኳን ይቸገራል:: እየተመላለሰ እረፍት የሚነሳውን ምናባዊ ትዕይንት ለማስታገስ ሲል በራሱ ላይ ራሱ ወሲብን ይፈጽማል:: ይህም የተበላሼ ሰው ሲሰክር ነገሮችን ሁሉ እንደሚረሳው ሁሉ





ለዚህም ሰው እንደማስታገሻ መድኃኒት የሆነለት ይመስለዋል::የሚታየው ፣የሚነበበው፣የሚሰማው ነገር አንዳንድ ጊዜ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን እንደመንፈሳዊ ሰው ሁሉንም በቃለ እግዚአብሔር መመዘን ተገቢ ነው::

ብቸኝነትን የሚመርጡና በሀሳብ የሚብከነከኑ ሰዎች ከሌሎች ጋር ነፃና ግልጽ ውይይት ስለማያደርጉ ማስተርቤሽንን እንደ ጓደኛና እንደ መዝናኛ ይጠቀሙበታል:: የብቸኝነት አጽናኛቸው ብቸኛውና ደስታን የሚፈጥርላቸው ነገር እንደሆነ ያስባሉ:: አስገራሚው ነገር ግን ማስተርቤሽን ፈጸሙም አልፈጸሙም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ለመገናኘት የሚያደርጉት ፍላጐት የማይቆም መሆኑ ነው:: ይልቁንም አንድ ወንድ ወይም አንዲት ፀሴት ራስን በራስ የማርካትን ዘዴ ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ ከተቃራኒ ጾታ የሚገኘውን ርካታ ለማነፃፀር ስለሚፈልጉ ከሌሎች ማለትም ማስተርቤሽንን ከማይፈጽሙ ሰዎች ቀድመው በዝሙት ይወድቃሉ:: ይሔ ደግሞ ሌላ ጥፋት ነው::

በአጮኝነት ፣በቃልኪዳንና በፍቅር የሚኖሩ ሰዎችን የሚመለከቱ ወጣቶች ለጊዜው የእነርሱ የፍቅር ግንኙነት በተለያየ ምክንያት ያልሰመረ ከሆነ ያጡትን ነገር ያገኙ እየመሰላቸው የሚወዱትን ሰው እያሰቡ ሰውነታቸውን በመነካካት ማስተርቤሽንን የሚፈጽሙ አልታጡም አይጠፉም:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲህ አይነቱ ድርጊት ኃጢአት ነው:: ወደ ሴት አይቶ የተመኘ ሁሉ አመነዘረባት .. ማቴ 5:28 ይላልና በእርግጥም ጊዜ ቦታና ገንዘብ ያገዱት ይሆናል እንጂ ሁኔታዎች ቢመቻቹለት ዝሙትን ከመፈጸም ወደኋላ አይልም:: በእነዚህና በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሲኮን ማስተርቤሽን ሊፈጸር ይችላል:: መጨረሻው ግን እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ማህበራዊ ተጽዕኖዎችን ከመፍጠሩም በላይ በትዳር ላይ የሚፈጠረው ቀውስ ወደ ፍቺ ያመራል::

በመጠኑም ቢሆን ከላይ ስለማስተርቬሽን ምንነት፣ ኃጢአት ስለመሆኑና እንዴት ሊከሰት እንደሚችል ለማየት ሞክረናል:: ይህም እንዲህም ሆኖ በአንዳንዶች ዘንድ ማስተርቤሽን ይህንን ያህል

አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ግን እጅግ አሳሳቢና አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ሰዎች በራሳቸው ዓለም ውስጥ ያለደስታ በጭንቀት ብቻ እንዲኖሩ የሚያደርግ በመሆኑ የዚህ ችግር ተጠቂ የሆነ ሰው በትዳሩ ላይ የሚገጥመው ቀውስ በቃላት ከሚገለጠው በላይ ነው፡፡

1. በተራከቦ ጊዜ ደካማ ያደርጋል፡

ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ እንመለከተዋለን፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የልብ ድካም ሲይዘው በልቡ ላይ ያሉት ጡንቻዎች በአግባቡ ስራቸውን ስለማያከናውኑ ባልታሰበ ጊዜ ለሞት ሊዳረግ ይችላል፡፡ ምክንያቱም በተለያየ ምክንያት ሥራቸውን ማከናውን ያልቻሉት የልብ ጡንቻዎች የደም ስርጭት ሒደቱን መቆጣጠር ስለማይችሉ ልብ ሥራውን እንደወትሮው አያከናውንምና የልብ ድካም ይዞታል ይባላል፡፡

እንደዚሁም ሁሉ አንድ ሰው ወይም አንዲት ሴት ራሳቸው በራሳቸው ላይ ወሲብ በሚፈጽሙበት ጊዜ ጾታዊ አካላቸውን መነካካታቸው የግድ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ላይ እያሉ ወደ ስሜት ጣሪያ ሲመጡ ምንም በማያውቁበት ሁኔታ ብልቶቻቸውን በጣም ይጨብጡና ከመጠን በላይም ይሻቸዋል ይህ ልማድ እየተደጋገመ ሲመጣ ጾታዊ አካላቸውን የሚወጥሩት ላይ ያለው ስሜት ቀስቃሽ ጡንቻዎች እየተዳከሙ ይመጡና የመዝለፍለፍ ባህሪ ያሳያሉ፡፡ አልፎ አልፎ ስሜታቸው ባይጠፋም እንኳን በሚፈለገው ውጥረት ለሩካቤ ዝግጁ አይሆኑም፡፡ ለሩካቤ ዝግጁ ቢሆኑም እንኳን ቶሎ ብለው ስለሚደክሙ የትዳር ጓደኛን ወደ ሰቀቀንና ወደሀዘን ይከታሉ ይህ ደግሞ ለትዳር መፍረስ በቂ ምክንያት ነው፡፡

2. ራስ ወዳድ ያደርጋል፡-

አዘውትሮ "ማስተርቤሽን" የሚፈጽም ሰው እጅግ ሲባዛ ራስ ወዳድ ነው፡፡ ሚስቱ ብትታመም ፣ብትወልድ፣ብታረግዝ፣ወይም ለሩካቤ ዝግጁ ባትሆን ስለእርሷ ምንም አይጨንቀውም፡፡ ሴቷም ብትሆን እንዲሁ፡፡ ምክንያቱም ከትዳራቸው የሚያገኙትን ነገር ከራሳቸው እንደሚያገኙ ያውቁታል ትዳራቸው በራሱ የተሟላ የትዳር ትርጉም





/በሀሳብ፣በስሜት፣በዓላማ ..... አንድ መሆን/ ይጐለዋል፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የኑሮ ጓደኛ መሆን ይቻል ይሆናል እንጂ የትዳር ጓደኛ መሆን አይቻልም፡፡

በተራክቦ አለመጣጣም ለትዳር መፍረስ እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል "ማስተርቤሽን" የሚያዘወትር ሰው ሁል ጊዜ ስለራሱ ብቻ ስለሚያስብ ሚስቱን ወይም ባሏን እንደ እቃ ነው የሚጠቀሙባቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ለስሜታቸው ቅርብ ስለሆኑ የራሳቸውን ደስታ ካገኙ በኋላ ስለሌላው አይገዳቸውም፡፡ በዚህ የስሜት ሥቃይ ውስጥ ሆኖ መቀጠል የሚፈልግ ማንም የለምና ትዳር ይበጠብጣል፣ልጆች ይበተናሉ በአጠቃላይ በቤተሰባዊ ማህበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የችግር ድባብ ያጠላል፡፡

3. አደገኛ ሱስ ይሆናል

የዚህ ልማድ ሌላው አሳሳቢ ነገር ለመተው አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡ አንዳንዴ በጾም በፀሎት ሲበረቱ፣ ከንስሐ አባቶቻቸው ጋር ሲመካከሩ ለተወሰነ ጊዜ ይወገዳል፡፡ ይሁን እንጂ ቆይቶ ከአመት ወይም ከስድስት ወር በኋላ እንደገና ይመለሳል፡፡ መስዋዕትነት ከፍለው ያስወገዱትን ነገር እንደገና ከተመለሰ ጨርሶ ለማጥፋት የከፋ ትግል ያጋጥማል፡፡ በዚህ ጊዜ አቶመዋለሁ ተብሎ የሚዘናጉለት ጉዳይ አይደለም እንደቀልድ እንደተጀመረ በፍፃሜም እንደ ቀልድ ማቆም ከባድ ነው፡፡ ድርጊቱ እየተመላለሰ ተከሰተ ማለት ከላይ የገለጽናቸው ነገሮች እንደገና በትዳር ውስጥ መጡ ማለት ነው፡፡ በቋፍ ያለውን ትዳር በምንም ድጋፍ ለማቆም ያስቸግራል፡፡

በድግግሞሹ ምክንያት አሰልቺ ስሜት ስለሚፈጠር በተሸናፊነት መንፈስ ነገሩን እንደመልካም ከመቀበል ውጭ አማራጭ የማጠፉበትም ጊዜ አለ፡፡ ሱስ የሆነ ነገር ደግሞ እግዚአብሔርን በአግባቡ ማምለክ እንዳይቻል ስለማያደርግ ከተለመደው የክርስትና መንፈስ ያወጣል፡፡ ኃላፊነትን መሸከም ሲያቅት ወደታላቅ የሞራል ውድቀት ውስጥ ቀስ በቀስ ይገባል፡፡ ከዚህ ውድቀት ለመነሳት ብቸኛው መፍትሔ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ከፍሎ ዕርግፍ አድርጐ

መተው ነው። አድለኛ ሆኖ ካልጀመሩ ግን በተማሩት የሃይማኖት ትምህርት ጸንቶ መቆምና ራስን መግዛት ነው። በርግጥ ከባድ ነው ጌታ ግን ያስችላል። ከስሜት ጋር ተቆራኝቶ ሰላም የሚነሳውን ይህንን ክፉ አባዜ ከሕይወት ውስጥ አውጥቶ ለመጣልና ራስን ነፃ አድርጎ ትዳርንና ቤተሰብን ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ከተነሳችሁ እግዚአብሔር ለሰውነታችሁም ይዋጋል። የልባችሁንም መሻት በጊዜው ይፈጽማል። በተግባር ልታከናውኗቸውና ልትለማመዷቸው የሚገቡ አንዳንድ የመፍትሔ ሃሳቦችን መከታተል ከአደጋ ቀጠናው ለመውጣት ጠቃሚ ነው።

**ማስተርቤሽንን እንዴት ማቆም ይቻላል?**

እጅግ በጣም አደገኛ ሱስ ነው እንደማንኛውም አልኮልና አደንዛዥ እጽ ሲላቀቁት የሚከብድ ሱስ ያስይዛል። ይሁን እንጂ መላቀቅ የማይችሉት ቁራኛ ወይም ቆተፈጥሮ ግዴታ ነው ማለት አይደለም። አዕምሮን በአሸናፊነት መንፈስ ማነቃቃት ከተቻለና በድፍረት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሸቀንጥሮ ለመጣል ከወሰኑ በእግዚአብሔር እርዳታ ሁሉም ነገር መስመር የማይዝበት ምንም ምክንያት የለም። ሐዋርያው ቅ.ጳውሎስ "ብቻ ለሥጋ ፈንታ አትስጡ ..." ገላ 5:13 በማለት የሚመክረው በነገሮች ላይ ቆራጥ ከሆኑና ምክንያት ካልደረደሩ ማንኛውንም ውጊያ በእግዚአብሔር ኃይል ማሸነፍ እንደሚቻል ሲያረጋግጥ ነው። ሐዋርያው በማከልም "....ራሴ የተጣልኩ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምኩ አስገዛዋለሁኝ" በማለት ከሚመጣው ፍርድ ለማምለጥ ብራሱ ላይ የወሰደውን የፈቃድ ቅጣት ያስረዳል። ከዚህ አንግር ህሊናን፣ ነፍስናሥጋን ከሚያቆሽሸው ነውር ራስን ለማዳን በብርቱ መታገል ተገቢ ነው። ከታች የተዘረዘሩትን ወደ ተግባር መለወጥ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ ይሆናል።

**1. በተቻለ መጠን ራስን ነፃ ማድረግ**

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ማስተርቤሽንን የሚፈጽሙት ከጭንቀት ለመሸሽ ከውስጣቸው የሚፈጠረውን ግፊት ለማስታገስ ነው። ከችግሩ ለመላቀቅ ርኩሰትን እንደ አማራጭ መፍትሔ መውሰድ እርቆ





ካለማስተዋል የሚመጣ ነው። ምክንያቱም ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊያስገኝ አይችልም። ከዚህ ይልቅ የሚያስጨንቅን ሁሉ ለእግዚአብሔር መስጠት፣ ራስንም ነፃ አድርጎ በጸሎትና በምልጃ የሚያስፈልግን ነገር ለፈጣሪ ማስታወቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ጥበብና እውቀት ነው። 1ኛ ጴጥ 5:7 ፊሊ 4:4-6 ጸሎት ኃይልን ታደርጋለችና ራስን ከፈጣሪ ጋር ባለ መልካም ግንኙነት ውስጥ መሰወር መቻል የመፍትሔውን እርምጃ ማፍጠን ነው።

የሰው ሕይወት አስቸጋሪ ሰልፍ ሊሆን ይችላል። በዚያ ላይ አውሎ ነፋሱ ይነፍሳል ወጀቡ ይበረታል መርከቧ ወጣለች ፈታኙ ቀርቦ ፈተናውን ያበዛል። ነገር ግን ይህም ቢሆን ያልፋል ጭንቀትን ማብዛት የሚፈይደው አንዳች ነገር የለም ማንም ተጨንቆ ጥቁር ፀጉሩን ነጭ ማድረግ አይችልም። ወይም በቁመቱ ላይ ጥቂት እንኳን መጨመር አይቻለውም "ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው።" ሰቆ.ኤር 3፣26 ማዳኑን በመታመን በኃይለኛው በእግዚአብሔር ተደግፎ ራስን ነፃ ማውጣት ለሚያምን ሰው ቀላል ነው። ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል።

2. እርቆ ማጠር፡- ራስን ለፈተና በሚመች ቦታ አስቀምጦ አትፈትነኝ ማለት ጭንቅላት ላይ ሸጉጥ ደግኖ ቃታውን እየሳቡ እግዚአብሔር ያድነኛል በሚል ቀልድ አምላክን መፈታተን ነው። ይልቁንም የመጀመሪያም የመጨረሻም ጅልነት በእንዲህ አይነት ነገር ራስን ማታለል ነው። ማስተርቤሽንን ለመከላከል በስሜት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮችን ማራቅን የተሳካ የለውጥ እርምጃ ነው። በዕርግጥ እናንተ ብታርቋቸው እንኳን በየማስታወቂያ ሰሌዳው በትራንስፖርት ስትጓዙ፣ከሰዎች ጋር ስትሆኑ ልታገኟቸው ትችላላችሁ። ዓለምና መላዋ ለሞት የተሰጠች በመሆኗ ሁልጊዜ የምትጽፈው፣ የምትገጥመው፣ የምታዜመው፣ የምትተውነው ዝሙትን ስለሚያባብሉ ነገሮች በመሆኑ ጉዞዎቻችሁን ውስብስብ ሊያደርግባችሁ ይችላል። ይሁን እንጂ



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወት ለድርድር አይቀርብም "ሳይቃጠል በቅጠል" እንደሚባለው እንደ ተላላፊ ወረርሽኝ በሽታ በሩቁ መሸሽ ነው::

ብቻችሁን በምትሆኑበት ጊዜ በተለይም ሌሊት እንቅልፍ በማይወስዳችሁ ወቅት ሀሳቦች እየተመላለሱ ማስተርቤሽንን እንድትፈጽሙ ይገፋፉችኋል:: እግዚአብሔርን በቀንም በሌሊትም ማሰብ ተጽእኖውን ለመቋቋም ያስችላል:: "በመኝታዬም አስብሃለሁ....." መዝ6:6 ብሎ ነብዩ እግዚአብሔር ዳዊት ያስገነዘበው ምክር ዘወትር ሊዘነጋ አይገባም:: ተነስቶም በጸሎት በመትጋት፣ የብቸኝነትን መንፈስ አባሮ እግዚአብሔርን በመጥራት ጓደኛ ማድረግ፣ ልጠፋ ነው ብሎም መማፀን ለክርስቲያን የመንፈስ ብርታትን ይጨምራል:: ስለእግዚአብሔርና ስለድንቅ ስራዎች ስታሰላስሉ የሰይጣንን ሀሳብ ታስወግዳላችሁ::

3. ፍላጐቱ እንዳያገረሽ መጣር

ማስተርቬሽንን የመፈጸም ልምድ የነበረው አሁን ግን የተወ አንድ ሰው በድንገት ወሲባዊ ፍላጐትን የሚያነሳሳ ነገር ቢመለከት ወይም ቢሰማ በፍጥነት ወደ ቀደመ ልማዱ እንዲመለስ የሚገፋፋ ሥሜት ሊፈጠርበት ይችላል:: ታዲያ በዚህ ጊዜ ራስን ከዚህ ፍጹም ተቃራኒ በሆነ ሥራ መጥመድ ወሳኝ ነው:: የመንፈስ ፍሬ ሁሉ ፍጻሜ የሆነውን ራስን መግዛት ገንዘብ ማድረግ የሁሉም ነገር ድል ነው:: ራሱን የሚገዛ ወጣት የሚያደርገውን ሁሉ በአግባቡ ስለሚያከናውን ከስህተት ይጠበቃል:: አዕምሮ ያለፈውን እያስታወሰ ደስታ እንደምታገኙ ሊመክራችሁ ቢፈልግም እንኳን ስርየት የለሽ ፀፀትን ካዘለ ወንጀል የሚገኝ ደስታ እንደሆነ ለልቦናችሁ ልትነግሩት ይገባል:: ከዚያ ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ደስታውን አለማግኘት ሰላምና ደስታ ነው::

ይሔ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎም እንደገና ሊያገረሽ የሚችልባቸው ሰዎች ይኖራሉ:: እነዚህ ሰዎች ህይወታቸው ሁሉ እዚህ ጋር ቆመ ከእንግዲህ ወዲህ ተስፋ የላቸውም ማለት ግን አይደለም:: ወይም በትግሉ እንደተሸነፉ አይቆጠርም:: ይልቁንም





በማስተዋል ለምን እንደገና እንዳገረሸ መንስኤዎቹን በመመርመርና ቀዳዳዎቹን ለመድፈን መነሳት ሌላ የመፍትሔ አቅጣጫ ነው::ችግሩ የትጋር እንዳለ ከታወቀ እርምት ለማድረግ አይከብድም:: በአንድ ጊዜ ቀጥ አድርጎ ማቆም ቢከብድም ድግግሞሹን በመቀነስ ቀስ በቀስ ዳግመኛ እንዳይመለስ አድርጎ ከነሥሩ ነቅሎ መጣል ይቻላል::

4. መንፈሳዊ ልምዶችን ማዳበር:-

የወንጌል ቃል የሚያስተምረው ሰው ሁሉ ለኃጢአት የሞተ ለጽድቅ የበረታ ይሆን ዘንድ ነው:: ይህንን በብቃት ለማከናወን እንዲረዳው ማንኛውም ሰው በገዛ ሥጋውና በእያንዳንዱ ብልቶቹ ላይ የማዘዝ ሙሉ ሥልጣን /ችሎታ/ ሊኖረው ይገባል:: "እንግዲህ በምድር ላይ ያሉ ብልቶቻችሁን ግደሉ" እነዚህም "ዝሙት፣ርኩሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞት ....." በማለት ይዘረዝራል:: ሐዋርያው እንደሚያስረዳው ፍትወት ማለት ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ ማመንዘር ማለት ነው:: አንዳንድ ሊቃውንት "ስልሗላነት" ብለው ይጠሯታል:: ፍትወት ለማይረባ ምኞት ተላልፎ የመስጠት ምልክት ነው ቅ.ጳውሎስ ቀጥሎም ሲያስረዳ የሚከተለውን ይገልፃል "ስለዚህም እግዚአብሔርን ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው:: ሴቶቻቸውም ለባህሪያቸው የሚገባውን ሥራ ለባህሪያቸው በማይገባው ለወጡ እንዲሁም ወንዶችም በወንዶች ነውር አደረጉባቸው በስህተታቸው የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው" ሮሜ 1:20-28 በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊገለጥ የተፈለገው በዝሙት እየተቃጠሉ ባልተለመደው ነውር ውስጥ ፍትወት ማከናወን በተለይም "ማስተርቤሽንን" መፈጸም ግብረ ሰዶማዊነትን የሚያጠናክር መሆኑን ነው::

አንዳንድ መንፈሳዊ ልምዶችን ማዳበር ከዚህ ክፉ ነገር ለመላቀቅ የምታደርጉት ጥረት ይደግፉችኋል:: ሰዎች ብዙውን ጊዜ ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙ በመኝታ ክፍላቸው፣በመጸዳጃ ቤታቸው፣

ገላቸውን በሚታጠቡበት ጊዜ ነው፡፡ ነገረ እግዚአብሔርን ዘወትር አለመዘንጋት፣ቸርነቱንም ማሰብ በተለይ ድርጊቱን ለመፈጸም ስትዘጋጁ ሥለ መንፈሳዊነት መጨነቅ አንድ ተግባራዊ ልምምድ ነው፡፡ በተጨማሪ አንድ ሰው ከመተኛቱ በፊት መንፈሳዊ መጽሐፍትን፣ ጋዜጦችን፣መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልማድ ሲኖረው ለመከሩ፣ ሊያስተምሩና ሊያጽናኑ የሚችሉ መዝሙሮችን ቢሰማ ይልቁንም ጸሎት የሁሉ ነገር መቋጫ የመንፈሳዊነት እስትንፋስ ነውና በጸሎት ቢተጋ ደረጃ በደረጃ ችግሩ እየተቀረፈለት ይመጣል፡፡

ወደ መታጠቢያውም ይሁን ወደ መጸዳጃው ሲያመራ ራሱን ማሳመን ይገባዋል፡፡ ለራሱ እንዲህ ይበል "እስከ ዛሬ ያደረኩት ይበቃኛል በቃ ከእንግዲህ ወዲህ አልሞክረውም ነፍስና ሥጋዬን፣ ህሊናና ልቦናዬን ከርኩሰት ጠብቄ አምላኬን አስደስተዋለሁ" ዘወትርም እንደ ሃይማኖት ጸሎቱ አድርጐ ይደጋግመው ለራሱ የገባውን ቃል ለመጠበቅ ከተጣጣረ ለውጡን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይመለከተዋል፡፡

5. የሰዎችን ተሞክሮ መተግበር

ሰዎች በልዩ ልዩ ነገሮች ላይ የራሳቸው የሆነ የሕይወት ተሞክሮ አላቸው፡፡ ከዕድሜ፣ ከትምህርት፣ ከእነርሱ በፊት ከነበሩ ሰዎች፣ ከቤተክርስቲያን ወይም ከሌላ ቦታ ያገኙት ሊሆን ይችላል፡፡ የሕይወት ውጣ ውረድ ብዙ ነገር ሥለሚያስተምር በአጋጣሚ እያስጨነቃችሁ ያለው ችግር በአንድ ወቅት በእነርሱም ላይ ተከስቶ ይሆናል፡፡ ካልሆነም እንዲህ አይነት ልምድ ያላቸው ሰዎች በቅርብ ሊያውቁ ይችላሉ ታዲያ ለዚህ አሳሳቢ ችግር እንዴት ብለው መፍትሔ እንዳገኙለት በማማከር ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡ ሌላው ሰዎችን ማማከር የሚጠቅመው የማስተርቤሽን ልማድ ያለበት ሰው የችግሩ ተጠቂ መሆኑን ለመናገር እጅግ በጣም ይፈራል፣ ያፍራልም ተጽዕኖውን ተቋቁሞ ለሰዎች ለማማከር ከተዘጋጀ ግን ምን ያህል በድርጊቱ ተጸጽቶ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሕይወቱ ለማውጣት ቁርጥ ውሳኔ እንደወሰነና ለመጣል አስፈላጊ የሆነውንም መስዋዕትነት እየከፈለ መሆኑን ያስረዳል ይህም የመፈወስ አንዱ ጉን ነው፡፡





በተጨማሪም ሁለተኛ በዚህ ነውር ውስጥ ገብቶ ላለመታየት፣ ትናንት ላማከረው ሰው ዛሬም እዚያው ጭቃ ውስጥ ነኝ ላለማለት ሲል እንኳን ፈተናውን ለመቋቋም ጠንክሮ ይሰራል፡፡ አንዳንዴ በነገሮች በግልጽ ለመነጋገር ያደግንበት ባህል ተጽዕኖ ቢኖረውም የተሻለ መፍትሄ ለማግኘት ስለሚያገለግል የመመካከር ልምድ ማዳበርና በፍጥነት ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ነፃ ያወጣል፡፡

እነዚህን ሁሉ ሞክራችሁ ካልተሳካላችሁ የጽሞና ጊዜ ይኖራችሁ ዘንድ ያስፈልጋልና በሱባኤ ለእግዚአብሔር ማሳሰብ ሌላው መፍትሔ ነው፡፡ ጌታ ረድቶአችሁ ችግሩ ከተወገደ በራስ የመተማመን መንፈሳችሁ ይመለሳል፣ ራሳችሁን በጥሩ የሥነ ምግባር መሰረት ላይ ትመሰርታላችሁ፣ ንፁህ ህሊና ስለሚኖራችሁ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት ትፈጥራላችሁ፣ አዕምሮዋችሁን የሚያቆሽሸው ነገር ስለተወገደ በልጅነት መንፈስ እግዚአብሔርን ለማምለክ የበቃችሁ ትሆናላችሁ መንፈሳዊነትና የእግዚአብሔርም በረከት በእናንተ ላይ አብዝቶ ይገለጣል፡፡

---------------- ተፈጸመ ---------

# በሰላመ እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org